# የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

# የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔዎች መጽሔት

ቁጥር 4

የካቲት 2014 ዓ.ም

# የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔዎች መጽሔት

**ስልክ፡-** +251-01124-2328

- +251-01122-3322

**ፋክስ** ፡- +251-01124-2328/04

**ፖስታ**፡- 20212/1000

**ድረገጽ፡-**http://www.hofethiopia.gov.et/

**ፌስቡክ፡-**
**https**://www.facebook.com/hofethiopian/

**ዩትዩብ፡-**
https://www.youtube.com/channel/

**ትዊተር፡-** https://twitter.com/hofethiopia

**ፍለከረ**፡-
**https:**//www.flickr.com/photos/houseof

Federation of Ethiopia/

**አብራችሁን ስለሆናችሁ ደስተኞች ነን!**

**አዘጋጆች**

**ብርቱካን መለሰ**

**ሙልዬ ወለላው**

**ያውቃል በቀለ**

**ኤዲተሮች**

**ሞገስ ጀንበር**

**ምሕረት ተስፋዬ**

**ማውጫ** **ገፅ**


የኢ.ፌዴሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ አገኘሁ ተሻገር መልእክት፣...... 5

የሕገ መንግሥት ትርጉምና የውሳኔ አፈጻጸም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ/ር ሰማ ጥሩነህ መልእክት ........ 7

1. ምርጫን በተመለከተ የተሰጡ የሕገ መንግሥት ውሳኔዎች ........ 9

1.1አመልካች፡- የኢ.ፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ተጠሪ፡- የለም ........ 9

1.2 አመልካች፡- የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ)፣ ተጠሪ፡- የለም ........ 14

2. በጋብቻ፣ በግልና በቤተሰብ መብቶች ዙሪያ የተሰጡ የሕገ መንግሥት ውሳኔዎች፣...... 26

2.1አመልካች፡- ወ/ሮ ኢያልነሽ ሞገስ ደመቀ፣ ተጠሪ፡- አመልማል አሳዬ ........ 26

2.2 አመልካች፡- ወ/ሮ ትሁኔ ጥሩነህ፣ ተጠሪ፡- አቶ እንዳለማው ጌታሁን ........ 32

2.3 አመልካች፡- አቶ መሠረት ታየ፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዛብሽ ገላው ........ 38

2.4 አመልካች፡- ወ/ሮ ብርቱካን ኩማ ዘለቀ፣ ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ (2 ሰዎች) ........ 42

2.5 አመልካች፡- ወ/ሮ ሃይማኖት ሰብስቤ፣ ተጠሪ፡- አቶ አሸናፊ ዓለሜ ........ 47

2.6 አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ብርሃኔ ዮሴፍ (2 ሰዎች)፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ የውብዳር ከበደ.. 51

2.7 አመልካች፡- ወ/ሮ ሸዋዬ ሙላት፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ አረጋሽ ባዲ ........ 57

3. የንብረት መብትን አስመልክቶ የተሰጡ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች ........ 63

3.1አመልካች፡- ወ/ሮ አሚና አብዱልቃድር፣ ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ከድር መሃመድ(4 ሰዎች) ........ 63

3.2. የጉዳዩ አቅራቢ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ተጠሪ፡- የለም ........ 69

3.3 ይግባኝ ባይ፡- ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ፣ ተጠሪ፡- የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ........ 78

3.4 አመልካች፡- አቶ ክፍለ ጽዮን በርሄ ገ/ማርያም፣ ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ተሾመ አባመጋል(2 ሰዎች) ........ 84

3.5 አመልካች፡- ቄስ ወ/ጊዮርጊስ ኪዳኔ፣ ተጠሪዎች፡- እነ አቶ መረሳ ወ/ማርያም(2 ሰዎች) ........ 88

4. **የገጠር መሬት አጠቃቀም አስመልከቶ የተሰጡ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች** ........ 93

4.1አመልካች፡- አቶ ጀማል ሰይድ፣ ተጠሪ፡- አቶ ገራድ ጉዲሳ ቡሽራ........ 93

4.2. አመልካቾች፡- እነ ከተፎ ገ/የስ (2 ሰዎች)፣ ተጠሪ፡- ወጣት በሱፍቃድ አየለ........ 98

4.3. አመልካች፡- አቶ አብዱራህማን ኡርጌሳ፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሐሊማ ቶላ ..................... 102

5. **ፍትሕ የማግኘት መብትን አስመልክቶ የተሰጡ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች** .......... 107

5.1 አመልካች፡- ፺ አለቃ ግዛው ደንቤ ሳልልህ፣ ተጠሪዎች፡- እነ ኮሚቴ ኦፍ ኢንተለጀንስ ኤንድ ሴኪዩሪቲ ሰርቪስ ኦፍ አፍሪካ (CISSA)(2 ሰዎች) ......................... 107

5.2 አመልካች፡- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት፣ ተጠሪዎች፡- እነ የኢፌዲሪ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን(2 ሰዎች) ............................................ 115

5.3 አመልካች፡- አቶ ጌታቸው ተድላ ኃ/ጊዮርጊስ፣ ተጠሪዎች፡- እነ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8(2 ሰዎች) ............................................................................ 120

6. የኪራይ ውልን አስመልክቶ የተሰጠ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ .................................... 126

6.1 አመልካች፡- አቶ አብርሃም ኃ/ጊዮርጊስ፣ ተጠሪዎችዎች፡- እነ አቶ መሃሪ መኮንን (4 ሰዎች) ..................................................................................................... 126

7. የንግድ ጉዳይን አስመልክቶ የተሰጠ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ .................................... 130

7.1 አመልካች፡- አቶ ንጉሤ ሀድጎ፣ ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል አቃቤ ሕግ .................... 130

8. የጡረታ መብትን አስመልክቶ የተሰጠ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ................................ 136

8.1 አመልካች፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ ተጠሪዎች፡- እነ አቶ እርገጤ መድበው ጆፌ (22 ሰዎች) ....................................................................... 136

## የኢፌዴሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ አገኘሁ ተሻገር መልእክት፣

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62(1)፣ 83(1) እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 4(1) መሠረት ሕገ መንግሥቱን የመተርጎምና ሕገ መንግሥታዊ ክርክር ሲነሳ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

ምክር ቤቱ ሕገ መንግሥቱን እንዲተረጉም ሥልጣን የተሰጠበት ቀዳሚውና መሠረታዊው ምክንያት የምክር ቤቱ አደረጃጀት ከሌሎች ሀገራት በተለየ ሁኔታ ብሔርን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ማዕከል ያደረገና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 61 ቁጥር 2 መሠረትም እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ቢያንስ አንድ ተወካይ እንዲኖረው በመደረጉና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሕገ መንግሥቱ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ነጻ ፈቃድና ስምምነት ውጤት ነው ከሚል እምነት የመነጨ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሕገ መንግሥት የመተርጎም ሥልጣኑ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ወይም ለሕገ መንግሥት ልዩ ፍርድ ቤት ቢሰጥ ዳኞች ግልጽ ያልሆኑ ድንጋጌዎችን በሚተረጉሙበት ጊዜ የራሳቸውን ፍላጎትና ምርጫ ሊያስገቡበት ይችላሉ ከሚል ሃሳብ በመነሳት ነው፡፡

እንደሚታወቀው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥትን የመተርጎም ሥልጣኑን በብቃት እንዲወጣ ሙያዊ እገዛ የሚሰጥ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ አጣሪ ጉባኤው ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ያለው ሲሆን፣ በሚያደርገው ማጣራት መሠረት ሕገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ የመጨረሻውን ውሳኔ የመስጠቱ ሥልጣን ግን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ይሆናል፡፡

ምክር ቤቱ ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ "ፍርድ እንዳይጓደል፣ ድኻ እንዳይበደል" እንደሚባለው ከዜጎችና ከተቋማት የሚመጡለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም

አቤቱታዎችን በመመርመር ሕገ መንግሥቱን በመቃረን የተሰጡ ውሳኔዎችን ለማስተካከል ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔዎች በሁሉም ዘንድ ዕውቅና ኖሯቸው ተፈጻሚ እንዲሆኑ በማሰብ ለዚሁ ዓላማ በሚያዘጋጀው መጽሔት አሳትሞ ለሚመለከታቸው አካላት ሲያሰራጭ ቆይቷል፡፡ ይህ ቁጥር 4 የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔዎች መጽሔትም አንዱ ማሳያ ነው፡፡

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርግ በዚሁ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶች፣ ፍርድ ቤቶች፣ የፍትህ ሚኒስቴር፣ የዴሞክራሲ ተቋማትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ምክር ቤቱ በየጊዜው የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በሥራዎቻቸው ሂደት ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው በዚሁ አጋጣሚ አደራ እላለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

## የሕገ መንግሥት ትርጉምና የውሳኔ አፈጻጸም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ/ር ሰማ ጥሩነህ መልእክት

የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62/1/ ላይ ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን እንደተሰጠው በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሚቀርቡለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም የውሳኔ ሐሳቦችና በይግባኝ ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔ ያሳልፋል፡፡ ምክር ቤቱ እስካሁንም ድረስ በርካታ የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔዎችን በመወሰን የዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን ለማስፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡

ምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የውሳኔ አፈጻጸም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ እና በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ስር ራሱን የቻለ ዳይሬክቶሬት በማቋቋም ሥራውን እየሠራ ይገኛል፡፡ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የአሠራርና የአባላት ስነምግባር ደንብ ቁጥር 3/2013 አንቀጽ 73 መሠረት የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ከዳይሬክቶሬቱ የሚያገኘውን የሙያ ድጋፍ መሠረት በማድረግ የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታዎችን በመመርመር ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ ምክር ቤቱ ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግባቸው ውሳኔ ያሳለፈባቸውን ጉዳዮች በድጋሚ በመመርመርና ለጥናትና ለውይይት ምሁራንን በመጋበዝ ግብዓት ካሰባሰበ በኋላ ቋሚ ኮሚቴው እንደገና ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

ይህ ሁሉ ጥረት የሚደረገው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ማንኛውም ሰው፣ ማኅበር ወይም ቡድን ፍትሕ የማግኘት መብት አለው የሚለውን ድንጋጌ ተፈጻሚ በማድረግ ዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን ይበልጥ ለማስፋት ነው፡፡ የዜጎች በየደረጃው ፍትሕ የማግኘት መብታቸው እየሰፋ ሲመጣ እውን እንዲሆን የምንመኘውን የሕገ መንግሥት የበላይነት ለማረጋገጥ ያስችላል የሚል ከፍተኛ እምነት ያለ በመሆኑ ነው፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚወስናቸው ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች በሁሉም ዘንድ ዕውቅና ኖሯቸው ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለማስቻል እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች በጆርናል መልክ እያሳተመ ተደራሽ እያደረገ ቆይቷል፡፡ እስካሁን ተከታታይ ሦስት ሕገ መንግሥታዊ መጽሔቶች አሳትሞ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጨ ሲሆን አራተኛው ቅፅ ተዘጋጅቶ እነሆ ለሕትመት በቅቷል፡፡

ቅፅ አራት ሕገ መንግሥታዊ መጽሔት 23 የሕገ መንግሥት ውሳኔዎችን የያዘ ሲሆን እነዚህ ውሳኔዎች 6ኛው ዙር ሀገር አቀፍ ምርጫን፣ ጋብቻ በሁኔታ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ ኢሕገመንግስታዊ ስለመሆኑ፣ የንብረት መብትን፣ ፍትሕ የማግኘት መብትን፣ የገጠር መሬት ይዞታን የመጠቀም መብትንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የተመለከቱ ናቸው፡፡

በመጨረሻም እነዚህ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔዎች የመጨረሻና አስገዳጅ በመሆናቸው በሁሉም ዘንድ ዕውቅና አግኝተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማስቻል በዚህ ሕገ መንግሥታዊ መጽሔት ላይ እንዲታተሙ መደረጉ ጠቀሜታው ከፍ ያለ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እየገለጽኩ መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ ከወዲሁ እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

1. ምርጫን በተመለከተ የተሰጡ የሕገ መንግሥት ውሳኔዎች

የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

ሰኔ 03 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ/ቁ. 83/12

1.1አመልካች፡- የኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ተጠሪ፡- የለም

የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 28 ቀን 2012 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽፎ ባቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መነሻነት ነው፡፡ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሊቀርብ የቻለው በኢትዮጵያ ምርጫ በሚደረግበት የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ የተገደደችበት ወቅት ሲሆን በሥልጣን ላይ ያሉት የመንግሥት አካላት ሚና እና ኃላፊነት በቀጣይ ምን ይሆናል? ምርጫውስ መቼ መካሄድ ይኖርበታል? የሚሉትን ጥያቄዎች ሕገ መንግሥቱ በግልጽ ባለመደንገጉ ምክንያት ነው፡፡

የቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ይዘት በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ምርጫ ማካሄድ ስላልተቻለ ሕገ መንግሥቱ ደግሞ የዋና ዋና የመንግሥት ሥልጣን አካላት (የሕግ አውጪ እና ሕግ አስፈፃሚ) በየአምስት ዓመቱ በሚደረግ ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫ

መሠረት በሚካሄደው የሥልጣን ርክክብ ላይ የሚመሠረት በመሆኑ አሁን ሀገሪቱን በመምራት ላይ የሚገኙት የመንግሥት አካላት የሥልጣን ዘመን ላይ ሁኔታው ምን እንድምታ አለው የሚልና ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለሕዝብ ጤና ስጋት መሆን ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ ምርጫው መከናወን ያለበት በምን ያህል ጊዜ ነው የሚል ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩን መመርመር ከመጀመሩ አስቀድሞ ጉዳዩን ተቀብሎ የማየት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጉዳዩን ለጉባኤው መላክ ይችላል ወይስ አይችልም? በሚሉት ነጥቦች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ጉባኤው ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት እንዲቻል ሁለት ጭብጦችን ለይቷል፡፡ የለያቸው ጭብጦች የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰትና ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ተጽእኖውን ለመቀነስ በታወጀው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ምክንያት የምክር ቤቶች እና የአስፈፃሚው አካል ሥልጣን የሥራ ዘመንን አስመልክቶ የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበውን ጥያቄ ለመመለስ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 54(1) 58(3) እና 93 እንዴት ይተረጐማሉ? የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰትና ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ተጽዕኖ ለመቀነስ በታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ምክንያት ምርጫ የሚደረግበትን ጊዜ አስመልክቶ የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበውን ጥያቄ ለመመለስ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 54(1)፣ 58(3) እና 93 እንዴት ይተረጐማሉ የሚሉ ሲሆን በእነዚህ ጭብጦች ላይ ምርመራ አካሂዷል፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በአንቀጽ 84(1) መሠረት ጉዳዩን ተቀብሎ የመመርመር ሥልጣን ያለው መሆኑን ስምምነት ላይ የደረሰ ሲሆን ጉባዔው ሕገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የፍርድ ክርክርን አስታከው የሚመጡ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን ወይንም ሕገ መንግሥቱን የሚጋፉ አዋጆችን መመልከት ብቻ ሳይሆን ሕገ መንግሥታዊ የትርጉም ሥርዓትን ሊያሰፉ የሚችሉ አንኳር ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ትንተና እና የውሳኔ ሀሳብ በመስጠት ጉባዔውንም ሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ሕገ መንግሥቱ ቀድሞ ታሳቢ እንዳደረገው የሕገ መንግሥት ትርጉም ሥርዓትን የማሳደግ ኃላፊነት አለው፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የትርጉም ጥያቄውን ማቅረብ የሚችል መሆኑን በተመለከተም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84(1) እና በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

አዋጅ ቁ.798/2005 አንቀጽ 3(2) መሠረት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄውን ለማቅረብ ይችላል የሚል ብይን ሰጥቷል፡፡

ጉባኤው ለቀረበለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የውሳኔ ሀሳብ ከመስጠቱ በፊት ከግለሰቦችና ከተቋማት 34 የሙያ አስተያየቶች በጽሑፍ ተቀብሎ ጽሑፎችን በመዳሰስ በግብዓትነት ተጠቅሟል፡፡ በተጨማሪም ሦስት መድረኮችን በተለያየ ጊዜያት በማዘጋጀት ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎችና ጠበቆች ማኅበር፣ 10 የሕገ መንግሥት ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ ሕገ መንግሥቱ በሚረቀቅበትና በሚጸድቅበት ጊዜ ተሳትፎ ከነበራቸው 4 ሰዎች፣ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከሕብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት፣ ከጤና ባለሙያዎች ማኅበር ከኮቪድ 19 የሳይንስ አማካሪ ካውንስል አስተያየት የመስማት /Hearing/ ሂደት ስለማከናወኑ የተላከልን ሰነድ በማስረጃነት ያመላክታል፤፤ ሂደቱም ልዩ ልዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የቀጥታ ስርጭት ሽፋን እንዲኖር በማድረግ የሀገራችን ሕዝቦች እንዲከታተሉት ተደርጓል፡፡ ሂደቱ በሀገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያው ፈር ቀዳጅና ታሪካዊ ሊባል የሚችል ሲሆን ጉባኤው ለፈጠረው ግልጽና አሳታፊ መድረክ ከፍተኛ ምስጋና ሊቸረው የሚገባ መሆኑን፣ እንዲሁም ጉባኤው ቀጣይ ተመሳሳይ ጉዳዮች ሲቀርብለት ይበልጥ አሳታፊ በሆነ መልኩ ባለድርሻ አካላትን በስፋት የማሳተፍ ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ብሎ ምክር ቤቱ ያምናል፡፡

እንደሚታወቀው 6ኛ ዙር ሃገራዊ ምርጫ በያዝነው በጀት ዓመት በተያዘለት መርሐግብር መሠረት መካሄድ እንዳለበት መንግሥት በልዩ ልዩ መድረኮች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማለትም ለሕዝቡ፣ ለተፎካካሪ ፓርቲዎችና ሌሎች አካላት ጭምር አስቀድሞ ቁርጠኝነቱን ግልጽ በማድረግ መግባባት ላይ መድረሱ ይታወሳል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም ምርጫውን ለማስፈጸም የቅድመ ምርጫ ዝግጅት ሥራዎችን ሲያከናውን ከቆየ በኋላ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳውን ይፋ ማድረጉ ይታወቃል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ማንም ቀድሞ ባላሰበውና ባልገመተው ሁኔታ በሀገራችንና በዓለም ላይ የኮሮና ቫይረስ ተከስቶ በርካታ ሕዝብን እየገደለና የስርጭት አድማሱን እያስፋፋ ይገኛል፡፡ ከዚሁ የወረርሽኝ ስጋት የተነሳ 53 ሀገራት ምርጫን ጨምሮ መንግሥታዊ እቅዶቻቸውን በማቋረጥ የሕዝባቸውን ሕይወት ለመታደግ እና ወረርሽኙን ለመከላከል ዘመቻ ከፍተዋል፣ ከ100 በላይ የሚሆኑ አገሮች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማውጣት ተገደዋል፡፡ የኢፌዲሪ መንግሥትም የሕዝቡን የደኅንነት አደጋ ለመቀነስ ሲል የአስቸኳይ

ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012ን አውጇል፡፡ አዋጁ በሕገ መንግሥት ከሰፈሩት አንቀጽ 1፣ 18፣ 25 እና 39 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ውጪ ያሉ ለሕዝቡ ደኅንነት ሲባል የተወሰኑ የዴሞክራሲ መብቶችን ይገድባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጉባኤው የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የሕገ መንግሥቱን ዓላማና ግብ እንዲሁም መርሆዎች መሠረት በማድረግ መርምሯል፡፡ ጉባኤው የተከተለው የሕገ መንግሥት አተረጓጎም መርሆዎች የጉባኤው አባላት የቀረበውን ጥያቄ ለመመርመር የተሻለ ሆኖ ያገኙትን የሕገ መንግሥት አተረጓጎም ዘዴ ዓላማ ተኮር እና መዋቅራዊ (Purposeive/structural) የሚባለውን የትርጉም ዘዴ ሲሆን የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውም የሚከተለውን የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 54(1)፣ 58(3)፣ 67(1) እና 72(3) ላይ የተደነገገው የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን ከአንቀጽ 93 እንዲሁም ከሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች፣ ዓላማዎችና ግቦች ጋር በማገናዘብ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የሕዝብ ጤና ስጋት ሆኖ ባለበትና የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ፀንቶ በሚቆይባቸው ጊዜያትና ከተነሳም በኋላ አዲስ ምርጫ ተካሂዶ የሥልጣን ርክክብ እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የክልል ም/ቤቶች እና የፌዴራልና የክልል አስፈፃሚ አካላት የሥራ ዘመን እንዲቀጥል በማለት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84(1) መሠረት የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚከተለውን የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

የኮቪድ 19 ስርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 እንዲታወጅ ምክንያት የሆነው ወረርሽኝ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የጤና ድርጅቶች የሚያወጡትን መረጃ መሠረት በማድረግ የኢፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር እንዲሁም የሕብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት እና የሳይንሱ ማኅበረሰብ አካላት ወረርሽኙ የሕዝብ ጤና ስጋት አለመሆኑ ካረጋገጡበትና ይህም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ከዘጠኝ ወር እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ምርጫው እንዲካሄድ በማለት የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከም/ቤቱ አፈ ጉባዔ ከላይ የተጠቀሰው ጉዳይ ተመርቶለት በጥልቀት የመረመረ ሲሆን አራት የአጣሪ ጉባኤ አባላት ከቋሚ ኮሚቴ አባላት ለተነሱ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴው ያጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ በመደገፍ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

በመሆኑም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግሥቱን አጠቃላይ መርሆዎችንና ዓላማዎችን በመፈተሽ በሕገ መንግሥቱ ላይ ግልጽ የሆነ ድንጋጌ ባለመኖሩ የምርጫውን ጊዜ ለማራዘም ባለመቻሉ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በበቂ ትንተና እና አሳማኝ ምክንያቶች ላይ ተመሥርቶ ተገቢውን ጊዜ ወስዶ በጥልቀት መርምሮ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ምክር ቤቱ በሚገባ ተወያይቶበት በአብላጫ ድምጽ ተቀብሎ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ የኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ተመርምሮ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት የውሳኔ ሀሳቡን በመቀበል ለክልል ምክር ቤቶች እንዲሁም ለአስፈጻሚው አካላት ደርሷቸው በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽሙ እንዲደረግ በማለት ምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

## የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

## 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 1ኛ አስቸኳይ ጉባዔ

## ነሐሴ 30 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ/ቁ. 87/12

### 1.2 አመልካች፡- የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ)፣ ተጠሪ፡- የለም

የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 20/12/2012 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽፎ ባቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መነሻነት ነው፡፡ የጥያቄው ይዘትም፡-

"በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62/1/ ሕገ መንግሥትን የመተርጎም ሥልጣን የተሰጠው የፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተውና በከፍተኛ ደረጃ እየተዛመተ፣ ገዳይነቱ እየጨመረ በመጣው ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ምርጫውን ማድረግ ስለማይቻል በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሪፖርት ላይ ተመሥርቶ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ካቀረበ በኋላ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሰጠው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት ምርጫው እንዲራዘም ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም መስጠቱ ይታወቃል፡፡

ይሁንና ለሕዝብ ጤና ደኅንነት ቅድሚያ በመስጠት ወረርሽኙ በሕዝብ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስና ስርጭቱንም ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁ እየታወቀ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም ምርጫውን በጊዜው ማካሄድ

እንደማይችል በገለፀበት፣ የምርጫው ሁሉን አቀፍነት፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተና በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን የሚገልፅበትና ለምርጫው ዋስትና የሚሰጥ ሕገ መንግሥታዊ ተቋም በማይሳተፍበት፣ በወረርሽኙ ምክንያት መራጩ ሕዝብ በነጻነት ተንቀሳቅሶ ምርጫውን ለማካሄድ በማይችልበትና የፖለቲካ ድርጅቶችም በነጻነት ተንቀሳቅሰው የፓርቲያቸውን ፖሊሲና ፕሮግራም ለመራጩ ሕዝብ ማስተዋወቅ አዳጋች በሆነበት ወቅት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት 6ኛውን ዙር ምርጫ በክልሉ ለማካሄድ በመወሰንና ክልላዊ የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም የምርጫ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሆነና ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ሕገ መንግሥቱን ከተቃረነ ተፈጻሚነት እንደሌለው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(2) ማንኛውም ዜጋ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በተያያዘም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50(8) መሠረት ለፌዴራል መንግሥት የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር ያለበት መሆኑ እና የሕገ መንግሥት የበላይነት የሚደነግገው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ማንኛውም ሕግ ወይም የመንግሥት አካል ውሣኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም እኛ በትግራይ ክልል የምንቀሳቀስ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ) በትግራይ ክልል ምርጫ ላይ ለመሳተፍ እቅድና ዝግጅት የነበረን ቢሆንም ምርጫው በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን በተሰጠው አካል በመራዘሙ ሕገ መንግሥቱን በማክበር በሕገ ወጡ የትግራይ ክልል ምርጫ ላለመሳተፍ ወስነናል፡፡

የፌዴራል መንግሥትም የሕገ መንግሥቱን የበላይነት ለማስከበር ተገቢውን እርምጃ መውሰድና በሕወሓት መሪነት እየተካሄደ ያለው ሕገ መንግሥቱንና የምርጫ ሕጉን የጣሰ የምርጫ እንቅስቃሴ እንዲቆም ማድረግ አለበት፡፡

ስለሆነም የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉምና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ሕገ

መንግሥታዊ ሥልጣን በመጋፋት ከሕግ ውጭ ምርጫን ለማካሄድ ወስኖ እየተንቀሳቀሰ ስለሆነ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምርጫ ለማካሄድ የወሰነው ውሳኔ፣ ያቋቋመው ክልላዊ የምርጫ ኮሚሽን እና እያደረገ ያለው የምርጫ እንቅስቃሴ ኢ.ሕገ መንግሥታዊ መሆናቸው በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ተጣርቶ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሯል፡፡ ጉባዔው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆን፣ አለመሆኑን እና አመልካች የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ) ባለጉዳይ ሆኖ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ማቅረብ የሚችል መሆን፣ አለመሆኑን ጉባዔው ወደ ዋናው ጉዳይ ገብቶ ከማየቱ በፊት እነዚህን ነጥቦች መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጉዳዩን ተቀብሎ ለመመርመር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን በሚመለከት የኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84(1) እንደሚከተለው ይነበባል፤

"የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሠረት ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል" ይላል፡፡

ከላይ ከተገለጸው ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ጉባዔው ማንኛውንም ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ያለው መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምርጫ ለማድረግ ወስኖ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 351/2012 በማውጣት እና የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም እያደረገ ያለው የምርጫ ዝግጅትና እንቅስቃሴ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች ያቀረበው ጥያቄ ምርጫን በሚመለከት የፌዴራል መንግሥት እና ክልሎች ያላቸው ሥልጣን ከሕገ መንግሥቱ አንጻር በመመርመር ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ በመሆኑ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጉባዔው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 መሠረት ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ወይም የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ ሥልጣን አለው፡፡

የአመልካች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የማቅረብ መብትን አስመልክቶ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84(2) ስር ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌውም እንደሚከተለው ይነበባል፣

“በፌዴራል መንግሥትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳይ ሲቀርብለት ጉባዔው ጉዳዩን መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፡፡”

በተመሳሳይ ሁኔታ የአጣሪ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 5 ከፍርድ ቤት ውጭ የሚቀርቡ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄዎች የሚመለከት ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 3 ስር በፌዴራል መንግሥትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከሕገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በባለጉዳዩ ለጉባዔው ሊቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

ከላይ ከተገለጸው የሕገ መንግሥቱ እና የአዋጁ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው የሕግ ሕገ መንግሥታዊነት ትርጉም ጥያቄ በፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዩ መቅረብ እንደሚችል ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84(2) እና በአዋጁ አንቀጽ 5(3) የተገለጸው “ባለጉዳይ” የሚለው አገላለጽ አመልካችን የሚመለከት መሆን እና አለመሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ማቅረብ አንዱ ፍትሕ የማግኘት መብት ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ አወሳሰን የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 37 ፍትሕ የማግኘት መብትን ከጉዳዩ ጋር አያይዞ መመልከት ተገቢነት አለው፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) መሠረት “ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው” በማለት ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 ስር ደግሞ “በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፡-

ሀ) ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ) ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው” ይላል፡፡

ከዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ ከተረጋገጠው ፍትሕ የማግኘት መብት ለመጠቀም የጉዳዩ አቅራቢ የሆነው ሰው ውሳኔ ወይም ፍርድ እንዲሰጥበት በሚጠይቅበት ጉዳይ ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆን እንዳለበት ነው፡፡

ወደ ቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ስንመለስ ጥያቄ አቅራቢው በምርጫ ተወዳድሮ በክልል ሥልጣን ለመያዝ የፖለቲካ ዓላማ ይዞ በትግራይ ክልል የሚንቀሳቀስና ሥልጣን ላይ ካለው መንግሥት ጋር ተወዳድሮ ሥልጣን ለመያዝ ተፎካካሪ ፓርቲ ሆኖ እያለ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ ባልቻለበት ሁኔታ ምርጫው ቢደረግ በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠለትን የመመረጥ መብት የሚያሳጣው በመሆኑ አመልካች መብት ወይም ጥቅም አለው፡፡ በዚህ መሠረት ጥያቄ አቅራቢው በክልሉ የወጣው የምርጫ ሕግ፣ የተቋቋመው የምርጫ ኮሚሽን እና አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱን በመቃወም የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ለማቅረብ መብት አለው፡፡

በአጠቃላይ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 መሠረት ጥያቄ አቅራቢው ባለጉዳይ ሆኖ የመቅረብ መብት ያለው መሆኑ እና ጉባዔውም ጉዳዩን ተቀብሎ ለመመርመር ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩ በጉባዔው ሊታይ የቻለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከዚህ ቀደም 6ኛው ሀገራዊ ጠቅላላ ምርጫ በተመለከተ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ላይ የመጨረሻ የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም አሁን በዚህ መዝገብ የቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በክልሉ ምርጫ ለማካሄድ የምርጫ ሕግ ማውጣቱ፣ የምርጫ ኮሚሽን ማቋቋሙን እና ሌሎች የምርጫ እንቅስቃሴዎች ማድረጉን የተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር ጥያቄዎችን የያዘና ጥያቄውም የቀረበው በሌላ አካል በመሆኑ ነው፡፡

**በቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ላይ በጉባዔው የተለዩ ዋና ዋና ጭብጦች እና ትንታኔዎች፣**

ከጥያቄ አቅራቢው አቤቱታ ለመረዳት እንደተቻለው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ባለማክበር እና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን በመጋፋት ከሕግ ውጭ ምርጫን ለማካሄድ የወሰነው ውሳኔ፣ ያቋቋመው ክልላዊ የምርጫ ኮሚሽን እና

እያደረገ ያለው የምርጫ እንቅስቃሴ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናል የሚል ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ጉባዔው የሚከተሉትን ሁለት ዐበይት ጭብጦችን የለየ ሲሆን ጭብጦቹም፣

ሀ) በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት የምርጫ ሕግን የማውጣት ሥልጣን የተሰጠው ለማን ነው?

ለ) በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት መሠረት ጠቅላላ ምርጫን የማስፈጸምና የምርጫ ቦርድ የማቋቋም ሥልጣን የማን ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ጉባዔውም ከላይ በተለዩት ሁለት ዐበይት ጭብጦች ስር ለውሳኔ ሀሳብ አሰጣጥ እንዲመች ሌሎች ንዑስ ጭብጦችን ለይቶ ቀጥሎ ባለው አግባብ ተንትኗል፡፡

**የምርጫ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በተመለከተ፣**

በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 1 መሠረት ኢ.ትዮጵያ ፌዴራላዊ እና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የመንግሥት አወቃቀር እንዳላት ተደንግጓል፡፡ የፌዴራል ሥርአቱ ዝርዝር መገለጫዎች በሕገ መንግሥቱ የመግቢያ ክፍል እና አንቀጽ 50 እስከ 52 ላይ ተደንግጓል። በዚሁ መሠረት የኢ.ትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥት እና በክልሎች ተዋቅሯል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39(1) እና (3) መሠረት ደግሞ ማንኛውም የኢ.ትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን፣ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት የሚመለከት ነው፡፡ ክልሎች ይህንን መብት ተግባራዊ የሚያደርጉት በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡትን የፌዴራልና የክልል ሥልጣን ክፍፍል ባከበረ መልኩ መሆን ይገባዋል፡፡

በክልል እና በፌዴራል መንግሥት መካከል ከተደረጉት የሥልጣን ክፍፍሎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሕግን የማውጣት የሥልጣን ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ የኢ.ትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ከሚወስኑበት አንዱ በመረጡአቸው ተመራጮች መተዳደር ነው፡፡ ይህን የሥልጣን ምንጭ የሆነውን ምርጫ የሚፈፀመውና የሚተገበረው በምርጫ ሕግ ነው፡፡ ይህን የምርጫን ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል፡፡

በክልል እና በፌዴራል መንግሥት መካከል የሚደረግ ሕገ መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍል በሦስት መንገድ እንደተቀመጠ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51፣ 52፣ 55 እና ከሌሎችም መረዳት ይቻላል፡፡ ለፌዴራሉ መንግሥት በግልፅና በዝርዝር የተሰጡ ሥልጣኖች ያሉ ሲሆን ለክልሎች ደግሞ በግልፅ የተሰጡ ሥልጣኖች እንዲሁም በጋራ ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሎች የተሰጡ ያሉ ሲሆን በግልጽ ለፌዴራል መንግሥት እና ለክልሎች ያልተሰጡ ሥልጣኖች የክልሎች ሥልጣን እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሠረት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51 እና 55 ስር የተዘረዘሩት ሥልጣንና ኃላፊነቶች በጥቅሉ ለፌዴራል መንግሥት ማለትም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዝርዝር የተሰጡ ሥልጣኖች ናቸው፡፡ እነዚህ ሥልጣኖች ለፌዴራሉ መንግሥት በግልፅና ለብቻው የተሰጡት በመሆናቸው ክልሎች በእነዚህ ዝርዝር ሥልጣኖች ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን የላቸውም፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51(15) እንደተደነገገው የፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ውስጥ አንዱ ምርጫን የሚመለከት ሕግ የማውጣት ሲሆን ድንጋጌው እንደሚከተለው ይነበባል፤

“በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡትን የፖለቲካ መብቶች ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዲሁም ምርጫን በሚመለከት ሕጎችን ያወጣል” ይላል፡፡ በሌላ በኩል የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55(2) (መ) ደግሞ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት “በዚህ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን የፖለቲካ መብቶች አፈጻጸምን እንዲሁም ምርጫን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ያወጣል” በማለት ተደንግጓል፡፡

ከእነዚህ ሁለት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ምርጫን በሚመለከት ሕግ የማውጣት ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነት በፌዴራል መንግሥት ውስጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡ ይህ ምርጫን በሚመለከት ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ለፌዴራሉ መንግሥት በዝርዝር ከተሰጠው ሥልጣን ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ምርጫን በሚመለከት የክልል መንግሥታት ወይም የክልል ምክር ቤቶች ሕግ ማውጣት አይችሉም፡፡

የኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓት በመከባበር ላይ የተመሠረተ የፌዴራል ሥርዓት መሆኑን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50 (8) ላይ ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌውም ሲነበብ፡-

"የፌዴራሉ መንግሥት እና የክልሎች ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ የተወሰነ መሆኑን፣ ለፌዴራሉ መንግሥት የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር አለበት፡፡ ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በፌዴራሉ መንግሥት መከበር አለበት" በማለት ይደነግጋል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በግልፅ እና በዝርዝር ለፌዴራሉ መንግሥት የተሰጡትን ሥልጣኖች ክልሎች ሊያከብሩት እንደሚገባና በሕገ መንግሥቱ ለክልሎች በአንቀጽ 52 መሠረት የተሰጡት እና የተተውትን ሥልጣኖችን የፌዴራሉ መንግሥት ሊያከብራቸው ይገባል፡፡

በሕገ መንግሥቱ በክልሎችና በፌዴራል መንግሥቱ መካከል የሥልጣን ክፍፍል ቢደረግም እንዲሁም አንዱ የአንዱን ሥልጣን የማክበር ኃላፊነት ቢኖርባቸውም በሁለቱ መካከል ሥልጣንን በሚመለከት ክርክር ወይም አለመግባባት ሊነሳ እንደሚችል ይገመታል፡፡ ለዚህም ሲባል ሕገ መንግሥቱ እንዲህ ዓይነት አለመግባባቶችና ክርክሮች ሲነሱ ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሚቀርብበትንና የፌዴሬሽን ምክር ቤትም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበትን ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሆነና ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት እንደሌለው ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገ መንግሥቱን የማስከበር ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህንኑ የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌ በመቃረን የሚወጣ ሕግን መርምሮ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነትም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡

የክልሉ ምክር ቤት ይህን የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌ በግልፅ በሚቃረን መልኩ በክልሉ ተፈጻሚነት የሚኖረው የምርጫ ሕግ ማውጣቱ በሕገ መንግሥቱ በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት መካከል የተደረገውን ሕግ የማውጣት ሕገ መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍል የሚቃረን ነው፡፡ ስለዚህም አሁን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበበት እና በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት የወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012 በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ለፌዴራል መንግሥት ብቻ በዝርዝር የተሰጠውን የምርጫ ሕግን የማውጣት ሥልጣን ባለማክበር የወጣ በመሆኑ ሕገ መንግሥቱን ይጥሳል፡፡

**ምርጫን የማስፈጸም ሥልጣንን በተመለከተ፣**

በመቀጠል መመርመር ያለበት ሁለተኛው ጭብጥ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት መሠረት ምርጫን የማስፈጸም ሥልጣን የማን ነው? የሚለው ነው፡፡

ከላይ በጭብጥ አንድ ስር እንደተመለከተው ምርጫን የተመለከተ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51(15) እና 55(2(መ) መሠረት የፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ሲሆን የምርጫ ቦርድን የማቋቋም እና ምርጫን የማስተዳደር ሥልጣንም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 102 ስር በተደነገገው መሠረት የሚመራ ነው፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 102 በግልጽ እንደተደነገገው በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻ እና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሟል፡፡

በዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ መሠረት ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነው የምርጫ ቦርድ እንደ ሌሎቹ ሕገ መንግሥታዊ ተቋማት ራሱን ችሎ ነጻነቱ ተጠብቆ በሕገ መንግሥቱ በመቋቋሙ የተነሳ ምርጫን የተመለከቱ ጉዳዮችንም የማስተዳደር ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 103 (5) ስር የፌዴሬሽን ምክር ቤት የምርጫ ክልሎችን ለመወሰን መሠረት የሚያደርገው በሕገ መንግሥቱ የተቋቋመው የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ ተመሥርቶ መሆኑ ምርጫን ከማስተዳደር አኳያ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የምርጫ ቦርዱን አባላት አሰያየም በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 102(2) ላይ መደንገጉ የምርጫ ቦርድ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ ሀገራዊ ተቋም እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሀገራዊ ተቋም የተመሠረተው በሀገሪቱ የሚካሄደው አጠቃላይ ሀገራዊ ምርጫ በቦታ ያልተገደበና በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ጊዜ ወይም ወቅት ለማካሄድ ነው፡፡

የምርጫ ቦርድን ከማቋቋም ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ዋናው ጉዳይ ክልሎች በዚህ ረገድ በሕገ መንግሥቱ ያላቸውን ሥልጣን የተመለከተ ነው፡፡ ከላይ ስለ ሥልጣን በተመለከተው ክፍል እንደተገለጸው ምርጫን የተመለከተ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የፌዴራል መንግሥቱ መሆኑ በግልጽ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51(15) እና 55(2(መ)) ላይ የተደነገገ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 52 ስለ ክልሎች ሥልጣን በተደነገገበት አንቀጽ ስር ምርጫን የተመለከተ በክልል ደረጃ ሊቋቋም የሚችል አካል ስለመኖሩ ሥልጣን ያልተሰጠ እና ለክልሎች ያልተተወ ነው፡፡ ስለዚህ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 102 መሠረት

ከተቋቋመው ምርጫ ቦርድ ሌላ ክልሎች በሌላቸው ሥልጣን በክልል ደረጃ የምርጫ ቦርድም ሆነ የምርጫ ኮሚሽን የማቋቋም ሕገ መንግሥታዊ መሠረት የላቸውም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012ን በማውጣት በክልል የምርጫ ኮሚሽን ማቋቋሙ ሕገ መንግሥቱን ይጥሳል፡፡

በዚህ ጭብጥ ስር ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ሌላው ጉዳይ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምርጫ ለማካሄድ የመወሰኑና የምርጫ እንቅስቃሴ የመጀመሩን ሕገ መንግሥታዊነት የተመለከተ ነው፡፡ ከላይ በጭብጥ አንድ ስር እንደተገለጸው የምርጫ ሕግን የማውጣት ሥልጣን የፌዴራል መንግሥቱ መሆኑንና ምርጫን የማስፈጸም ሥልጣንም የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በመሆኑ በክልሉ የወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012ን መሠረት በማድረግ ክልሉ የሚያከናውናቸው ምርጫን የተመለከቱ ውሳኔዎች እና እንቅስቃሴዎችም ሕገ መንግሥታዊ አይደሉም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ ቀደም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም 6ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ አስመልክቶ ያሳለፈውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 6ኛውን ሀገራዊ ጠቅላላ ምርጫ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ባለበት ሁኔታ በዓለም አቀፍና በሀገራችን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ምርጫውን ባወጣው መርሃ ግብር መሠረት ማካሄድ የማይችል መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔ እንዲተላለፍ ለኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው መሠረት ምክር ቤቱም በጉዳዩ ላይ ሥልጣን ለተሰጠው ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በቀረበው የትርጉም ጥያቄ ላይ አጣሪ ጉባዔውም ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ተቀብሎ የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በውሳኔውም የኮቪድ 19 ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የሕብረተሰብ ጤና ስጋት አለመሆኑ በሚመለከታቸው አካላት ከተረጋገጠ ጀምሮ ምርጫው ከ9 (ዘጠኝ) ወር እስከ 12 (አሥራ ሁለት) ወር ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲካሄድ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ምርጫ ተደርጎ የሥልጣን ርክክብ እስከሚደረግ ድረስ የፌዴራል እና የክልል ምክር ቤቶች እና አስፈጻሚ አካላት ሥልጣናቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ ወስኗል፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ይህንን የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔ ለመስጠት ያስገደደው ምክንያት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሀገሪቱ መከሰቱ እና ይህን ተከትሎ የአስቸኳይ ጊዜ

አዋጅ በመታወጁ ምክንያት ነው፡፡ የውሳኔው ዋና ዓላማም የሕዝብን ጤንነት በመጠበቅ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ የምርጫ መስፈርቶችን ማለትም ሁሉ አቀፍ፣ ነጻ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በምስጢር የሚሰጥበት ሥርዓት የሚያሟላ ምርጫ ማካሄድ እንዲቻል ነው፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ አጠቃላይ ውጤት የሚኖረው መሆኑንና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖችም ውሳኔውን የማክበርና የመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 11 (1) እና 56(2) ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም ይህ የምክር ቤቱ ውሳኔ የአስገዳጅነት ውጤት ያለው እና በማናቸውም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ላይ ተፈጻሚ ነው፡፡ ሆኖም የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከላይ የተጠቀሰውን የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግሥት ትርጉም አስገዳጅ ውሳኔ የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ ያለበት ቢሆንም በሕገ መንግሥቱ ሕግ የማውጣትም ሆነ የማስፈጸም ሥልጣን ሳይኖረው የምርጫ ጉዳይ ላይ ምርጫ ለማካሄድ መወሰኑና የምርጫ እንቅስቃሴ መጀመሩ ሕገ መንግሥታዊ እና ሕጋዊ መሠረት የለውም፡፡

የኢፌዲሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በትግራይ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር መርምሮ የሚከተሉትን የውሳኔ ሀሳቦች በሙሉ ድምጽ አቅርቧል፡፡

1) የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ያወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012 ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51(15) እና 55(2)(መ) ጋር ይቃረናል በማለት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 መሠረት የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

2) የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012ን መሠረት አድርጎ የምርጫ ኮሚሽን ማቋቋሙ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 102 ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጠውን ሥልጣን ይጥሳል በማለት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 መሠረት የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

3) የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፣ አስፈጻሚ አካላት እና የምርጫ ኮሚሽን ምርጫን በሚመለከት ያወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012 ያሳለፏቸው ውሳኔዎች እና የፈጸሟቸው ተግባራት ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረኑ

በመሆናቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት እንዳልተደረጉ የሚቆጠሩ፣ የማይፀኑ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ናቸው በማለት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 መሠረት የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና ማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከኢፌዲሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ከሕገ መንግሥቱና ሕገ መንግሥቱን ተከትለው ከወጡ አዋጆች ጋር በማገናዘብ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ጉዳዩን በመምራቱ ቋሚ ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያየበት በኋላ ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት ምክር ቤቱ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ የትግራይ ክልል ያወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012፣ የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም የሚያደርገው የምርጫ እንቅስቃሴ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51(15)፣ 55(2)(መ) እና 102 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ሆኖ አግኝቶታል፡፡ በመሆኑም ምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በመቀበል በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

2. በጋብቻ፣ በግልና በቤተሰብ መብቶች ዙሪያ የተሰጡ የሕገ መንግሥት ውሳኔዎች፣

---

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ/ቁ. 49/10

---

## 2.1አመልካች፡- ወ/ሮ አያልነሽ ሞገስ ደመቀ፣ ተጠሪ፡- አመልማል አሳዬ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 ለፍርድ ቤቶች የተሰጠ ሕግ የመተርጎም ሥልጣን እና አንቀጽ 55 ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠን ሕግ የማውጣት ሥልጣንን መሠረት አድርጎ የቀረበ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ነው፡፡ ለጥያቄው መሠረት የሆነው ክርክር የተጀመረው በአዲስ አበባ መስተዳድር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የጉዳዩ ይዘትም የአሁን አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የአቶ አገኘሁ ፈንቴ ሚስት መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ፍ/ቤቱ ሚስት ናቸው በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ተጠሪ ባቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ አመልካች የሚች አቶ አገኘሁ ፈንቴ ሚስት አይደሉም፡፡ ሚች እና አመልካች የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ልጆች የወለዱ መሆናቸው የማይካድ ቢሆንም ነገር ግን በ1977 ዓ.ም ተጣልተው ተለያይተው አመልካች ወደ ሌላ አካባቢ በመሄድ ሌላ ባል አግብተው ብርሃኑ አበበ የተባለ ልጅ ወልደው የራሳቸውን ሕይወት እየኖሩ ነበር፡፡ ሚች ደግሞ ከአመልካች ጋር ከተፋቱ በኋላ ከ1980 ዓ.ም ጀምረው ከእኔ ጋር በመጋባት እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ሳንለያይ አብረን ኖረናል፡፡

አመልካች በዚህ 26 ዓመት ጊዜ ውስጥ ጋብቻ አለኝ፣ ሚስት ነኝ ብለው በሟች ላይም ሆነ በእኔ ላይ ክርክር አንስተው አያውቁም፡፡ የባልና ሚስትነት ንብረት ክርክር በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት በክስ ካልተጠየቀ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ስለሰጠበት ውሳኔው ሊፈርስ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከሟች ጋር በ1977 ዓ.ም በተፈጠረ ችግር ምክንያት ከቤት ሸሽተው መውጣታቸውን እና ለብቻቸው በሚኖሩበት ጊዜ ከሌላ ሰው ልጅ መውለዳቸውን አምነው ነገር ግን ልጅ መውለዴ ከሟች ጋር የነበረኝን ጋብቻ ስለማያፈርሰው ውሳኔው የሚፈርስበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች ከሟች ጋር ተለያይተው የራሳቸውን ሕይወት መኖራቸውና ሟችም ተጠሪን ወ/ሮ አመልማል አሳየን በማግባት የራሳቸው ሕይወት በመመሥረት መኖራቸውን፣ አመልካችም ይህንኑ የሚያውቁ መሆኑ ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ ለመፍረሱ አስረጂዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል በ13/11/2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ ተሰርዞ የአሁኑ አመልካች ወ/ሮ አያልነሽ ሞገስ የሟች አቶ አገኘሁ ፈንቴ ሚስት አይደሉም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ በማፅናት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በመጨረሻ ያየው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች የሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ መተርጎም ሰበብ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ አይደለም በማለት በርካታ መከራከሪያዎች በማቅረብ በየደረጃው ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አቤት ብልም ተቀባይነት አላገኘሁም በማለትና የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የሰፈረው የልዩነት ሃሳብ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡

የልዩነት ሃሳቡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/20938 ባልና ሚስት ተለያይተው የሚኖሩና የየራሳቸው ሕይወት መሥርተው ከተገኙ ፍች እንደፈጸሙ ይቆጠራል በማለት በሕገ መንግሥት አንቀጽ 79/1/ ለፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ሕግን

የመተርጎም ሥልጣን ያለፈና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተለይቶ የተሰጠውን ሕግ የማውጣት ሥልጣን የሚጋፋ ነው፡፡

በመሆኑም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 መሠረት ጋብቻ የሚፈርሰው በሞት ወይም የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ፣ በጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን እና በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ብቻ እንደሆነ ከተደነገገው የማያሻማ ግልጽ ድንጋጌ ውጪ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 20938፣ እንዲሁም በዚህ ውሳኔ የሰጠውን "የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባልና ሚስት በአካል ተለያይተው ከኖሩና የየራሳቸውን ኑሮ ከመሠረቱ ጋብቻቸው ፈርሷል በማለት ለጋብቻ መፍረስ ብቸኛ ምክንያት ናቸው ተብለው በሕግ ከተደነገጉት ሦስት ምክንያቶች ውጪ አራተኛ ምክንያት በመፍጠር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 79 ለፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ሕግ የመተርጐም ወይም የዳኝነት ሥልጣን በላይ መሥራቱን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 20938 የሰጠው ውሳኔ ተከትለው አመልካች ከሟች አገኘሁ ፈንቴ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ፈርሷል በማለት የሰጡት ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጋፋ ስለሆነ ትርጉም ይሰጠኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ጉዳይ ለጉባዔው ቀርቦ በጉዳዩ ላይ ጥናት ተደርጎ እንዲቀርብ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በጉባዔው ጽሕፈት ቤት በኩል ሰፊ ጊዜ የወሰደ ጥናት ተደርጎ በተደረገው ጥናት ላይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ውይይት እንዲያደርጉበት ከተደረገ በኋላ ጉባዔው በጥናቱ መሠረት  ጉዳዩን መርምሮታል፡፡

አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተያይዘው ከቀረቡትና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተካሄዱትን ክርክሮችና የተሰጡትን ውሳኔዎች ከሚያሳዩት ማስረጃዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በእነ ሸዋየ ተሰማ ጉዳይ በሰ/መ/ቁ. 20938 ሚያዚያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሰጠው ውሳኔና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች በዋናነትም ከኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት ጋር በማገናዘብ ጉባዔው መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ከቀረበው ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሕገ መንግሥታዊነቱ ላይ የቅሬታ አቤቱታ የቀረበበትና ለዚህ አቤቱታ መነሻ ለሆነው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ

ፍርድ ቤት ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) በሚደነግገው መሠረት እንደማጣቀሻ የሕግ ትርጉም ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ይሄውም በእነ ወ/ሮ ሸዋየ ተሰማ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20938 ሚያዚያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሲሆን የዚህ ውሳኔ ጥቅል ይዘቱ "….. ተጋቢዎች ምንም እንኳን ቀደም ብሎ የተፈጸመ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት መቀጠል አለመቻላቸው እና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸውን ሕይወት መጀመራቸው ተረጋግጦ እያለ ፍቺ መፈጸሙን አንደኛው ተጋቢ አላስረዳም በሚል ውሳኔ መስጠት ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎም አይደለም፣ … በመሆኑም የአሁኗ መልስ ሰጪ ቀደም ሲል የፈጸሙትን ጋብቻ መሠረት በማድረግ ብቻ ሚስት ናቸው ብሎ መወሰኑ ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎም አይደለም፡፡" የሚል ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት ይህ አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) በተደነገገው መሠረት የስር ፍርድ ቤቶች እንደ አንድ የሕግ ድንጋጌ በመጥቀስ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እየሰጡበት ይገኛል፡፡

ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 ለፍርድ ቤቶች ከተሰጣቸው የዳኝነት (ሕግን የመተርጎም) ሥልጣን በመውጣት ጋብቻ የሚፈርስበትን 4ኛ (አራተኛ) ምክንያት የሚያስቀምጥ ሕጋዊ ድንጋጌን የሚደነግግ ሲሆን ይህም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51 እና 55 ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን ሕግ የማውጣት ሥልጣንና ተግባር የሚጋፋ ውሳኔ ነው፡፡

ሕግ አውጪው አካል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 ላይ ጋብቻ የሚፈርስባቸው 3 (ሦስት ምክንያቶች) መዘርዘሩና በተለይም በአንቀጽ 82 ላይ የጋብቻን ፍቺ የመወሰን እና የጋብቻው በፍቺ መፍረስ የሚያስከትለውን ውጤት የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው ብሎ መደንገጉ የራሱ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህም ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የተጋቢዎችን የንብረት ክፍፍልና የህፃናትን የአስተዳደግ ሁኔታ አገናዝቦ ውሳኔ መስጠት ያለበት ፍርድ ቤት ነው ከሚል ምክንያት የተነሳ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ በሕግ አውጪው እንደምክንያት የተወሰደው ጉዳይም በሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 ላይ ሴቶችን እና የሕጻናትን ሕገ መንግሥታዊ መብት ለማስጠበቅ የጎላ ድርሻ ያለው ይህን መሰል ሕገ መንግሥታዊ መብት ወደ ጎን በመተው ከሕግ

አውጪው ዓላማ ውጭ በሆነ መልኩ የባልና ሚስት ፍች በፍርድ ቤት ሳይረጋገጥና ፍርድ ቤት የሁለቱን ተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እና የህፃናት ጉዳይ ዓይቶ ተገቢውን ውሳኔ ሳይሰጥበት ተጋቢዎች ተለያይተው በመኖራቸው እና የራሳቸውን ሌላ ሕይወት ጀምረዋል በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻው እንደፈረሰ መቁጠር የሕጉን ዓላማ የሳተ ይሆናል፡፡ በሌላ መልኩ እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ተጋቢዎች በቸልተኝነት ጋብቻቸውን ከፍርድ ቤት ዕውቅና ውጭ በፍች መልክ እንዲያቋርጡ መንገድ የሚከፍትና ሕገ ወጥነትን የሚያበረታታ ተግባር ነው፡፡

የቤተሰብ ሕጉ አንግቦ የተነሳውን ይህን መሠረታዊ መርህ ወደ ጎን በመተው ጋብቻ ከፍርድ ቤት ውጭ በተጋቢዎቹ ተለያይተው መኖር ብቻ ሊፈርስ ይችላል የሚለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቋም ሕገ መንግሥቱን እና ይህን ተከትሎ የወጣውን የቤተሰብ ሕጉን መሠረት ያላደረገ ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 2189/02 ላይ የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 64931 ላይ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ነው፡፡

ስለዚህ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 64931 ላይ በቀን 15/07/2003 የተሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር፣ በአንቀጽ 51 የፌዴራል መንግሥት ሥልጣንና ተግባር እና በአንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ፡፡ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡ ከሚሉት ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84(1) እና በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት ያጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሃሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየ በኋላ የውሳኔ ሃሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባዔውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/4/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚሰጠውን የሕግ ትርጉም ሕግ ሆኖ በሀገሪቱ ሁሉ ባሉ ፍርድ ቤቶች ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ ግን ባልና ሚስት ጋብቻቸው በፍርድ ቤት ሳይፈርስ ለ10 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ተለያይተው የየራሳቸውን ኑሮ እየኖሩ ከሆነ በሁኔታ እንደፈረሰ ይቆጠራል በሚል የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በቤተሰብ ሕጉ ላይ ከተቀመጡትና ጋብቻ ከሚፈርስባቸው ምክንያቶች ውጭ ከመሆኑም በላይ ከጋብቻው መፍረስ ጋር ተያይዘው የሚመጡ የፍች ውጤቶችን ማለትም የጋራ ልጆቹን አስተዳደግ፣ በጋብቻ ወቅት የተፈሩ የጋራ ሀብት ክፍፍልን በሚመለከት ምን ሊሆን እንደሚገባ ባልተመለከተ ሁኔታ እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕግ አውጪው አካል የወጣውን ሕግ መተርጎም እንጂ በሕግ ላይ የሌለን ነገር በትርጉም ሰበብ ሕግ ማውጣት ከሥልጣኑ ውጪ በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ የፀናውንና በመጨረሻ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም የተባለው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50/5/፣ አንቀጽ 55 እና 79/3/ ጋር የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

### የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

### 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

### ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ/ቁ. 77/12

## 2.2 አመልካች፡- ወ/ሮ ትሁኔ ጥሩነህ፣ ተጠሪ፡- አቶ እንዳለማው ጌታሁን

**የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 15 ቀን 2009 ዓ.ም ለጉባዔው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ አቤቱታውም በፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 131616 የተሰጠው ውሳኔ ላይ የተጠየቀ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲሆን ጉዳዩም የባልና ሚስት የንብረት ክርክርን ይመለከታል፡፡

የጉዳዩ ፍሬ ሀሳብ አመልካች በቀን 12/02/2008 ዓ.ም ተጠሪ ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በማቻከል ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መሥርተን ልጅ ወልደን አብረን ስንኖር በደረሰብኝ ህመም ምክንያት ወደ ጸበል እና ህክምና በመሄድ በሽታዬን በማስታመም ላይ ሳለሁ ተጠሪ እኔን መንከባከብ ሲገባው ጋብቻችን ሳይፈርስና ሀብት ንብረት ሳንከፋፈል በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመደረብ ሌላ ሴት በማግባት የጋራ ሀብቴን፣ የእርሻ መሬቴንና መኖሪያ ቤቴን ከነጓሮ አትክልቱ በግላቸው ይዘው እየተጠቀሙ፣ እኔ ግን በችግር እየተሰቃየሁ ቆይቼ ህመሜ ሲሻለኝ ጋብቻችን

በፍርድ ቤት መፍረሱ ተረጋግጦ የሀብቴን ድርሻ እንዲያካፍለኝ በመ/ቁ/13024 ጠይቄ ፍ/ቤቱም ጋብቻው መፍረሱ ተረጋግጦ የንብረት ጥያቄን በተመለከተ እንደገና ዘርዝሬ ለመጠየቅ እንድችል መብቴን ጠብቆልኝ ወስኗል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ 78 ዚንጎ ቆርቆሮ፣ አትክልት፣ ባህርዛፎች እና 10 የንብ ቀፎ ድርሻዬን እንዲያካፍሉኝ በማለት የንብረቱን መጠን እና ዓይነት በመዘርዘር ክሳቸውን ለፍ/ቤቱ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ በወቅቱ ከአመልካች ጋር ስንለያይ ያለንን ንብረት ተካፍለን ስለ ተለያየን አመልካች የቀራቸው ምንም ሀብት የላቸውም፡፡ አለኝ ካሉም በወቅቱ መጠየቅ የነበረባቸው ሲሆን ጋብቻችን ፈርሶ ከተለያየን 18 ዓመት ስለሆነ ይህ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ እንዲሆንልኝ በማለት መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በበኩላቸው ባደረጉት የቃል ክርክር ከተጠሪ ጋር ከተለያየን 13 ዓመት ስለሆነ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ እንዲፈርስ እና ንብረት እንዲከፋፈሉ በዚህ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 በተጠሪ ላይ ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም አመልካች እና ተጠሪ ከተለያዩ ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ ጋብቻው በሁኔታ ፈርሷል፡፡ አመልካች የንብረት ክርክርን በተመለከተ በሌላ ሁኔታ ተጠሪን መጠየቅ ይችላሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች በዚህ ችሎት የንብረት ክፍፍል ጥያቄን ቢያቀርቡም ነገር ግን አመልካች ከተጠሪ ጋር ከተለያየ 13 ዓመት መሆኑን ሲገልፁ ተጠሪ ደግሞ 18 ዓመት መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን ይህ ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ ከተለያዩ ከ10 ዓመት በላይ መሆኑን ስለሚያመላክት አመልካች ያቀረቡት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔም እስከ ፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በትእዛዝ ፀንቷል፡፡

አመልካችም ይህ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብቴን ጥሷል በማለት ለጉባዔው ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት ያነሱት ቅሬታም፣ የጋራ ንብረት የሆነው መሬትና ንብረት ተጠሪ እጅ ሊቆይ የቻለው በከባድ ህመም ታምሜ ለፀበልና ህክምና ወደ ሩቅ ቦታ ሄጄ እያለ ፍ/ቤቶቹ ይህንን ሳያጣሩ ተጠሪ ያቀረቡትን ማስረጃ ብቻ መሠረት በማድረግ ጋብቻው በሁኔታ የፈረሰ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሳኔ መስጠታቸው የአመልካችን ከይዞታ ያለመነቀል፣ በመሬት የመጠቀም እና በጋብቻ ውስጥ የተፈራው

ንብረት ከተጠሪ እኩል የመጠቀም ሕገ መንግሥታዊ መብት የሆኑትንና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 23፣ 35(2)(7) እና 40 የተደነገገውን የጣሰ በመሆኑ የፍ/ቤቱ ውሳኔ የሕገ መንግሥት ትርጉም ተሰጥቶት እንዲታረምልኝ በማለት ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አመልክተው ጉባዔው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እና የምክር ቤቱን ባለሙያዎች አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

በዚሁ መሠረት አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍርድ ቤት ውሳኔ የሕገ መንግሥት ጥሰት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም፣ በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ በፍርድ ቤት ፈርሶ የጋራ ንብረታቸውን እንዲካፈሉ በወረዳ ፍርድ ቤት ክሳቸውን አቅርበው ነበር፡፡ ፍ/ቤቱም በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በሁኔታ ስለፈረሰ ፍ/ቤቱ የሚያፈርሰው ጋብቻ የለም፣ ነገር ግን የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ አመልካች በሌላ ሁኔታ መጠየቅ ይችላሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚሁ መሠረት አመልካችም አሁን ቅሬታ የቀረበበትና በወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13725 ላይ ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ መፍረሱ በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ ስለተረጋገጠ አመልካች እና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩትን ንብረት ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግን አመልካች ያቀረቡት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ከተጠሪ ጋር ከተለያዩ ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ የወሰነ ሲሆን አመልካችም ይህ ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር ይቃረናል በማለት ለጉባዔው አቤቱታ ማቅረባቸውን ምክር ቤቱ ተረድቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ፍ/ቤቱ በወረዳ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 13024 ላይ ጋብቻቸው በሁኔታ ፈርሷል በማለት መወሰኑ፣ አሁን ቅሬታ የቀረበበት መዝገብ ቁጥር 13725 ላይ ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ ከተለያዩ ከ10 ዓመት በላይ ስለሆነ የአመልካች የንብረት ክፍፍል

ጥያቄ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በይርጋ ይታገዳል በማለት መወሰኑ የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ የንብረት መብታቸውን ይጥሳል ወይስ አይጥስም የሚለው ነጥብ ተመርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ አመልካች እና ተጠሪ ከ10 ዓመት በላይ ተለያይተው ስለቆዩ የነበራቸው ጋብቻ በሁኔታ የፈረሰ ስለሆነ በፍርድ ቤት የሚወሰን ፍች የለም በማለት የወሰነው ውሳኔ በፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 20938፣ 17937፣ 32308 እና 31891 ላይ ተመሳሳይ የሕግ ትርጉም በመስጠት ከወሰነው ውሳኔ ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ የተወሰነ መሆኑን ቅሬታ ከቀረበበት እና በመጨረሻ ፀንቶ ካለው ውሳኔ ላይ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ ሕግ አውጪው አካል በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 86 ስር እንደ ተቀመጠው ጋብቻ የሚፈርስባቸው 3 (ሦስት) ምክንያቶች ማለትም፣ 1ኛ ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ፣ 2ኛ ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን፣ 3ኛ የፍች ውሳኔ በፍርድ ቤት ሲሰጥ እንደሆነ መዘርዘሩና በተለይም በክልሉ የቤተሰብ ሕግ ከአንቀጽ 89 እስከ 95 እና በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 82 ላይ የጋብቻን ፍቺ የመወሰን እና ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የሚያስከትለውን ውጤት የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው ብሎ መደንገጉ የራሱ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህም ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የተጋቢዎችን የንብረት ክፍፍልና የህፃናትን የአስተዳደግ ሁኔታ አገናዝቦ ውሳኔ መስጠት ያለበት ፍርድ ቤት ነው ከሚል ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ ከሕገ መንግሥቱ ዓላማ ውጭ የባልና ሚስት ፍች በፍርድ ቤት ሳይረጋገጥና ፍርድ ቤት የሁለቱን ተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እና የህፃናት ጉዳይ አይቶ ተገቢውን ውሳኔ ሳይሰጥበት ተጋቢዎች ተለያይተው በመኖራቸው እና የራሳቸውን ሌላ ሕይወት ጀምረዋል በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻው እንደፈረሰ መቁጠር የሕጉን ዓላማ የሳተ ነው፡፡

በሌላ መልኩ እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ተጋቢዎች በቸልተኝነት ጋብቻቸውን ከፍርድ ቤት ዕውቅና ውጭ በፍቺ መልክ እንዲያቋርጡ መንገድ የሚከፍትና ሕገ ወጥነትን የሚያበረታታ ተግባርም ነው፡፡

ስለዚህም አመልካች በዋነኛነት ባለቤታቸው ከሆኑት ከአሁን ተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ በፍርድ ቤት እንዲፈርስ የጠየቁበት ምክንያት የጋብቻ መፍረስ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ እንዲወሰንላቸው እና በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት የንብረት መብታቸው እንዲከበርላቸው ለመጠየቅ መሆኑ እየታወቀ ባልና ሚስት በሕግ የሚፀና ፍቺ መፈጸማቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ ባይኖርም በአካል ተለያይተው ከኖሩና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸው ሕይወት መሥርተው መኖር መጀመራቸው ከተረጋገጠ ጋብቻቸው ከ10 ዓመት በኋላ እንደፈረሰ ይቆጠራል በማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በማቻከል ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50(5)፣ አንቀጽ 55 እና 79(1) ጋር ይቃረናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር. 13725 ላይ የአመልካች የጋራ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ተወስኖ በፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፀናውን ውሳኔ በተመለከተ አመልካች በክርክራቸው ከ13 ዓመት በፊት ማለትም በ1995 ዓ.ም በከባድ ሁኔታ ታመው ከህመማቸው ለመዳን ጠበል እና ህክምና ከመሄድ በስተቀር አግብተው ሌላ ትዳር በመመሥረት የግል ኑሮ መኖር እንዳልጀመሩ ከተጠሪ ጋር ለመለያየትም ሀሳብ እንዳልነበራቸው እና በችግር ብቻ ተለያይተው እንደ ቆዩ ፍ/ቤቱን አስረድተው ተከራክረዋል፤ ነገር ግን ፍ/ቤቱ አመልካች እና ተጠሪ ከ10 ዓመት በላይ በችግርም ይሁን ያለችግር ስለተለያዩ ብቻ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል፣ በጋብቻ ውስጥ የተፈራው የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ጥያቄ ደግሞ በይርጋ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ቀሪ ሆኗል በማለት በሕግ በግልፅ ያልተቀመጠውን ትርጉም በመስጠት መወሰኑ ሕገ መንግሥታዊ የሆነውን የአመልካችን የንብረት መብት በሚያስቀር ሁኔታ የተወሰነ ውሳኔ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡

የዚህ ውሳኔ ውጤት ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ ጋብቻ የሚፈርስበት ከ3ቱ መስፈርቶች ሌላ 4ኛ መስፈርት ከመፍጠሩም ባሻገር አመልካች ከተጠሪ ጋር ባል እና ሚስት ሆነው በጉልበታቸው ከጋብቻ ቀን ጀምሮ እስከ ተለያዩበት ቀን ድረስ ያፈሩትን ንብረት

እንዳይጠቀሙ የሚገድብ ውሳኔ በመሆኑ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 40 ስር ‹‹ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል፣ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው›› የሚለውን የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌ ይቃረናል፡፡ በተጨማሪም ፍ/ቤቱ አመልካች እና ተጠሪ ከተጋቡበት ቀን ጀምሮ ተለያይተው መኖር እስከጀመሩበት ቀን ድረስ በጋራ ያፈሩትን ንብረት አጣርቶ እኩል እንዲካፈሉ መወሰን ሲገባው በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በማለት የአመልካችን የጋራ የንብረት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ማድረጉ ከላይ የተጠቀሰውን ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን ይቃረናል፡፡

በመሆኑም አመልካች ጋብቻ ከመሠረቱበት ቀን ጀምሮ ከተጠሪ ጋር እስከተለያዩበት ቀን ድረስ ያፈሩትን ንብረት ለመከፋፈል መብት እያላቸው ይህንን መብት በሚያስቀር ሁኔታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማቻከል ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 እና 13725 ላይ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል፣ የንብረት ጥያቄ ደግሞ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስላልቀረበ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የተሰጠውና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 131616 የፀናው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50(5)፣ አንቀጽ 55 እና 79(1) እንዲሁም ከአንቀጽ 40(1)(7) ጋር ስለሚቃረን ውሳኔው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

ሚያዝያ 22 ቀን 2010 ዓ.ም

የመ/ቁ. 41/10

2.3 **አመልካች፡- አቶ መሠረት ታየ፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዛብሽ ገላው**

የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም ለጉባዔው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ጉዳዩ የንብረት ክርክርን መነሻ ያደረገ ሲሆን፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የማቻክል ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከቁስ ታየ ምሕረቴ ጋር በነበራቸው የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በአማኑኤል ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ ከኢ.ትዮጵያ ንግድ ባንክ በጨረታ ገዝቼ ስመ ንብረቱን በስሜ ያዞርኩት አንድ ክፍል ቤት እንደዚሁም የግሌ የነበሩ የቀንድ ከብቶች የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ናቸው በሚል የወረዳው ፍርድ ቤት በመወሰኑ በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ መብቴ ስለተነካ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ወደ ክርክሩ ገብቼ ተከራክሪያለሁ፡፡

በዚህ ክርክር ቄስ ታየ ምሕረቴ በሰጡት መልስ አምነው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ግን አከራካሪዎቹ ንብረቶች ከጋራ ንብረት ወጪ ተደርጎ የተገዙ በመሆኑ የቀድሞ ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪ ከቄስ ታየ ምሕረቴ ጋር በነበራቸው የጋብቻ የንብረት ክፍፍል ክርክር በአማኑኤል ከተማ ቀበሌ የሚገኝ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጨረታ ገዝቼ ስመ ሀብቱን በስሜ ያዞርኩትን አንድ ደጃፍ ቤት እንደዚሁም የግሌ የነበሩት የቀንድ ከብቶችን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል የማቻከል ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ  ይገባል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቄስ ታየ ምሕረቴ በሰጡት መልስ አምነው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ግን አከራካሪዎቹ ንብረቶች ከጋብቻችን የጋራ ንብረት ወጪ ተደርጎ የተገዙ በመሆኑ ንብረቶቹ የጋራ ሊባሉ ይገባል፣ የቀድሞ ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር እና የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች የተመለከተው ይሄው የወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪውን ቤት በገዛበት ወቅት ለአካለ መጠን ያልደረሰ መሆኑን በመጥቀስ በራሱ የሽያጭ ውሉን ሊዋዋል እንደማይችል በመጥቀስ ውሉ ከመሠረቱ  ፈራሽ ነው ብሏል፡፡ እንደዚሁም የሽያጭ ውሉ የ3ኛ ወገን መብት የነካ በመሆኑ ፈራሽ ነው ብሏል፡፡

እንደዚሁም አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመግዛት የሚያስችል ሀብት ኖሮት ንብረቱን ስለመግዛቱ አላስረዳም በማለት ንብረቱን ተጠሪ እና ከላይ በስም ተጠቃሹ የቀድሞ ባለቤታቸው በዕዳ ምክንያት ንብረታቸውን ባንክ ሲይዝባቸው በአመልካች ስም ከራሣቸው የጋራ ሀብት አውጥተው ያስገዙት የጋራ ንብረታቸው እንጂ የአመልካች የግል ሊባል አይችልም በማለት አከራካሪዎቹን የቀንድ ከብቶችም በተመለከተ ከተጠቃሹ ጋብቻ የጋራ ሀብት ወጪ ተደርጎ የተገዙ በመሆኑ የባልና ሚስቱ የጋራ ናቸው በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

በጉዳዩም ላይ በአመልካች ይግባኝ የቀረበለት የምሥራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያደረገውን የቤት ግዢ ውል በተመለከተ የደረሰበትን ድምዳሜ በመንቀፍ ውሉ ፈራሽ ሊሆን የሚችለው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ጥቅም በሚጎዳ መልኩ በተደረገ ጊዜ መሆኑን በመጥቀስ በሌላ በኩል አመልካች ባቀረባቸው በሰነድ ሆነ በሰው ማስረጃዎች በሚገባ ያስረዳ መሆኑን በመጥቀስ እንደዚሁም አከራካሪዎቹን የቀንድ ከብቶችም በተመለከተ አመልካች ባቀረባቸው ሁለት የውል ሰነዶች እና የሰው ማስረጃዎች በሚገባ ያስረዳ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ በተጠሪ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል በተጠሪ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር እና የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመግዛት የራሱን የሀብት ምንጭ የተጠቀመ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት አልተረጋገጠም፣ እንደዚሁም አንድ ሰው የንብረት ባለሀብት የሚሆነው በጉልበቱ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረት ያፈራ ሲሆን እንጂ በስሙ ስለተመዘገበ ብቻ የግሉ ሊሆን አይችልም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

ከላይ ጸንቶ ባለው ውሳኔ ላይ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ተጠሪ ከቁስ ታየ ምሕረቴ ጋር በነበራቸው የጋብቻ የንብረት ክፍፍል ክርክር በአማኑኤል ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጨረታ ገዝቼ ስመ ሀብቱንም በስሜ ያዞርኩት አንድ ደጃፍ ቤት እንደዚሁም የግል የነበሩት የቀንድ ከብቶችን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል የማቻከል ወረዳ ፍርድ ቤት ወስኖ ነበር፡፡

ውሳኔውን መብቴን ነክቷል በሚል በፍ/ሥ/ይ/ሕ/ቁ 358 ወደ ክርክሩ ገብቼ እንድከራከር ጠይቄ ብከራከርም አመልካች በወቅቱ ህጻን በመሆኑ ውል መዋዋል አይችልም እንዲሁም ንብረቶቹ የተገዙት በባልና ሚስቱ ገንዘብ ነው በማለት ንብረቶቹን የባልና ሚስቱ የጋራ በማድረግ የተሰጠው ውሣኔ በመጨረሻ በመጽናቱ በሕገ መንግሥቱ ያለኝን የንብረት መብት ይጥሳል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉባዔው በቀረበለት አቤቱታ መነሻ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፍ/ቤቶች በነበረ ክርክር ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ቤቱ በባንክ ዕዳ ምክንያት ሲሸጥ ወጪው ከቀድሞ ባለቤታቸው ቁስ ታየ ምሕረቴ ጋር ከነበራቸዉ የጋብቻ ሀብት ወጪ በማድረግ በአመልካች ስም ቤቱ የተገዛ መሆኑን እንደዚሁም በተመሳሳይ አከራካሪዎቹ የቀንድ ከብቶችም ከተጠቀሰው የጋብቻ የጋራ ሀብት ወጪ ተደርጎ የተገዙ መሆናቸውን በመጥቀስ ንብረቶቹን በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ስለሆነ የጋራ ይባሉልኝ የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቶችም ግራ ቀኙን አከራክረው በዋናነት አመልካች አከራካሪዎቹን ንብረቶች ከራሱ የሀብት ምንጭ ወጪ አድርጎ ስለመግዛቱ አላስረዳም በሚል ምክንያት ላይ በመመሥረት ንብረቶቹን የተጠሪና የቀድሞ ባለቤታቸው ቁስ ታየ ምሕረቴ በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ የጋራ ሀብት ናቸው በማለት መወሰናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን ፍ/ቤቶች ተጠሪ የቀድሞ ባለቤታቸው ቄስ ታየ ምሕረቴ በአንድ በኩል የሚፈለግባቸውን የባንክ ዕዳ መክፈል አቅቷቸው አከራካሪው ቤት በጨረታ ሊሸጥ የቻለ መሆኑን አረጋግጠው በሌላ በኩል አከራካሪውን ቤት ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ አቅም ኖሯቸው ከጋራ ሀብታቸዉ ወጪ አድርገው አከራካሪውን ቤት ገዝተዋል ሲሉ መደምደማቸውን ስንመለከት የተጠቀሰው ምክንያትና ድምዳሜ አብረው የሚሄዱ አለመሆናቸውን መረዳት የሚቻል ሲሆን ይልቁንም ፍርድ ቤት የተጠቀሱት አከራካሪው ቤት ከተጠቃሹ የጋብቻ ሀብት ወጪ ተደርጎ ያልተገዛ መሆኑን ያስረዳል ለሚል ድምዳሜ የቀረበ ነው፡፡

በተጨማሪም ፍ/ቤቶች በተለይ አከራካሪው ቤት ከተጠቃሹ ጋብቻ የጋራ ሀብት ወጪ ተደርጎ የተገዛ ነው ብለው እንደወሰዱት ግምት እንኳ ቢሆን ዕዳውን ቀድሞውኑ በቀጥታ መክፈል እየቻሉ ባለመክፈል ንብረታቸውን እንዲሸጥ በመፍቀድ በተዘዋዋሪ በአመልካች ስም ቤቱን የመግዛታቸው ድርጊት ተጠሪ ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር በመሆን ሕግን በተቃረነ መልኩ አንዳች ኃላፊነት ለመሸሽ ወይም ለሕገ ወጥ ዓላማ ሲሉ የከወኑት ተግባር ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር በመሆን በፈጸሙት ሕግን የተቃረነ ተግባራቸው ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባ አይደለም፡፡ ተጠሪና የቀድሞ ባለቤታቸው ሕግን ባልተቃረነ መንገድ አከራካሪዎቹን ንብረቶች በፈቃዳቸው ከጋራ ንብረታቸው ወጪ በማድረግ አካለመጠን ባልደረሰ በአመልካች ስም ገዝተዋል፡፡ ብሎ መነሳት ከምክንያታዊነት እና ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ካለው የሕጻናትን ጥቅም በቀደምትነት ከማክበር መርህ ጋር የሚቃረን ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በተለይ አከራካሪውን ቤት ስመ ሀብቱን በስሙ አድርጎ ማስረጃውን ይዞ የሚገኝ ሆኖ እያለ በዚህም በፍ/ሕ/ቁ 1195 መሠረት አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ስመ ሀብቱን በስሙ በማድረግ ማስረጃውን በእጁ ያደረገ ሰው የንብረቱ ባለቤት እንደሆነ የሚገመት ስለመሆኑ ተደንግጎ እያለ፣ እንደዚሁም ይህንኑ ድንጋጌ ተከትሎ በሚገኘው አንቀጽ 1196 መሠረት የቀረበ ግምቱን ሊያስተባብል የሚችል ክርክርም ሆነ ማስረጃ በሌለበት አልያም ሌላ ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ፍ/ቤቶች አከራካሪዎቹ ንብረቶች አንድ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ንብረት ከሚያፈራባቸው መንገዶች በአንዱ የተገኙ ንብረቶች ስለመሆናቸው መነሻ ግምት በመያዝ በተቃራኒው ሕግ በሚፈቅደው አግባብ ተጠሪ ማስተባበያ ማቅረብ አለማቅረባቸውን መመርመር ጉዳዩን መመልከት እየተገባቸው በተቃራኒው አመልካች ስለመብታቸው እንዲያስረዱ ግዴታን በመጣል መወሰናቸው የሕጻናት የተሻለ ጥቅም ለማስጠበቅ በሚረዳ መልኩ ውሳኔ የሰጡ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ በመሆኑ፣

ውሳኔው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 (2) ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወስዱበት ጊዜ መንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጊነት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕጻናት ደኅንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት በሚል የሰፈረው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ እንደዚሁም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 የሰፈረውን የንብረት መብት ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት**

**5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ጉባዔ**

**መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም**

**የመ/ቁ. 60/10**

---

## 2.4 አመልካች፡- ወ/ሮ ብርቱካን ኩማ ዘለቀ፣ ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ (2 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ይህ ጉዳይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 40 (1) እና (2) የተደነገጉትን ፍትሕ የማግኘት እና የንብረት መብቶችን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የላከው ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በግዥ ያገኙትን ቤት በተመለከተ (በአሁኑ ተጠሪዎች መካከል ይካሄድ በነበረው ክርክር) መብታቸውን ለማስከበር በመጀመሪያ ክርክሩን ላየው ለሰንዳፋ ወረዳ ፍርድ ቤት (አቤቱታ) ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በተጠሪዎች መካከል የነበረው የጋብቻ ክርክር ውሳኔ

አላገኘም በሚል ምክንያት አቤቱታቸው ውድቅ በማድረጉ ክርክራቸውን ሊቀጥሉ እንዳልቻሉ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ይህንኑ ቤት በተመለከተ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንብረታቸውን ለማስመለስ በተጠሪዎች ላይ ለመሠረቱት የመፋለም ክስ ፍርድ ቤቱ አቤቱታቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ሊያዝዝ ወይም የንብረት ክርክሩን ከማየት ባሻገር የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎች መካከል በነበረው የባልና የሚስት ይረጋገጥልን ክስ ጣልቃ ገብተው ነበር በማለት ይህንኑ ውሳኔ ተቃውመው ሳያሽሩ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካች ቤቱን በተመለከተ በፍርድ ቤቶች ተከራክረው መብታቸውን እንዳያስከብሩና ፍትሕ እንዳያገኙ ያደረጉ ውሳኔዎች መሆናቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህ በጉዳዩ ላይ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 ፍትሕ የማግኘት እና 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የንብረት መብቶች ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሃሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሃሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባዔውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡

በዚህ መሠረት አመልካች የመፋለም ክስ ያቀረቡት አስቀድሞ በተሰጠ ውሳኔ ለ1ኛ ተጠሪ በተላለፈ ቤት ነው፡፡ ቀድሞ ባደረጉት ክርክር አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብተው መከራከራቸውንና በተደረገውም ክርክር ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቶ ፍርዱም መፈፀሙን አመልካች ገልፀዋል፡፡ አስቀድሞ ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ሥልጣን ሳይኖረው የሰጠው ውሳኔ ነው የሚሉ ከሆነ አመልካች ሕጉ ባስቀመጠው አግባብ ስነ ሥርዓቱን ተከትለው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረብ መብታቸውን

ከሚያስከብሩ በቀር አስቀድሞ የተሰጠ ውሳኔ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ክስ ማቅረብ የሕግም ሆነ የስነ ሥርዓት ድጋፍ የለውም…" በማለት የፌ.መ.ደ. ፍርድ ቤት የአመልካችን የመፋለም ክስ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ይህ ብይን በይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤቶች እንዲፀና ተደርጓል፡፡

ፍርድ ቤቱ የአመልካችን የመፋለም ክስ አቤቱታ ውድቅ ለማድረግ በምክንያትነት የጠቀሰው ክስ የቀረበበት ጉዳይ አስቀድሞ በተሰጠ ውሳኔ ፍፃሜ ያገኘ ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ አይቻልም በማለት ሲሆን ይህ አስቀድሞ የተሰጠ የተባለው በኦሮሚያ ክልል፣ በሰሜን ሸዋ ዞን፣ በሰንዳፋ/በረህ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04956 በአሁን ተጠሪዎች መካከል በነበረውና የአሁኗ አመልካች በጣልቃ ገብነት ቀርበው በተከራከሩበት መዝገብ በቀን 18/04/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠውና በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁጥር 16365 በቀን 26/07/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲፀና የተደረገው ብይን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡

በዚህ ብይን የወረዳ ፍርድ ቤቱ የአሁኗ አመልካች የንብረት መብታቸውን ለማስከበር ለወደፊቱ ሊኖራቸው የሚችለውን አቤቱታ የማቅረብ መብት በመጠበቅ ያቀረቡትን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ሐተታ ዘምክንያት "…የጣልቃ ገቧ አቤቱታ ይህ ተከሳሽ (የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ አቶ መስፍን ገ/መድህን) ከከሳሿ (የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ) ጋር ያፈራውን ንብረት እንዲያካፍል ለማድረግ የቀረበ ክርክር መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው ስለሆነ ጣልቃ ገቧን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 418(1) እና 419(1) በሚያዘው መሠረት ከጣልቃ ገብነት አውጥተን ባልና ሚስት ንብረት ሲካፈል መብቷን የሚጋፋ ከሆነ ልትቀርብ ትችላለች እንጂ የቤተሰብ ጉባዔ ሽማግሌዎች የዕርቅ ውጤት ታውቆ ትዳራቸው ሳይፈርስ ልትቀርብ አይገባትም ብለን ብይን ሰጥተናል፡፡…" በማለት ሲሆን ይህ ብይን የአሁኗ አመልካች በቀጣይ መብታቸውን ለማስከበር ያላቸውን አቤቱታ የማቅረብ መብት የተጠበቀ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በዚሁ መሠረትም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁ.9 እንደተደነገገው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት እንዲሁም ለክርክር መነሻ የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገኝበት ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት በአሁኗ 1ኛ ተጠሪ

ያላግባብ ተያዘብኝ ያሉትና በአዲስ አበባ ከተማ፣ የካ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 10፣ ልዩ ስሙ አንቆርጫ በሚባለው ቦታ የሚገኘው የቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነው ቤት እንዲለቀቅላቸው ለመጠየቅ በአሁን ተጠሪዎች ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት የመፋለም ክስ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ከሳሽ (የአሁኗ አመልካች) አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ በተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረባቸው የሕግም ሆነ የስነ ሥርዓት ድጋፍ የሌለው ነው በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን የሰጠ ሲሆን ብይኑ እስከ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች እንዲፀና ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/2/ እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁ.9 እንደተደነገገው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት እንዲሁም ለክርክር መነሻ የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገኝበት ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት በአሁኗ አንደኛ ተጠሪ ያለ አግባብ ተያዘብኝ ያሉትና በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ልዩ ስሙ አንቆርጫ በሚባለው ቦታ የሚገኘው ቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነው ቤት እንዲለቀቅላቸው ለመጠየቅ በአሁኗ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተከሳሽ በነበሩት ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የካ ምድብ አንደኛ ፍትሐብሔር ችሎት የመፋለም ክስ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ከሳሽ ማለትም የአሁኑ አመልካች አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ በተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረባቸው የሕግም ሆነ የስነሥርዓት ድጋፍ የሌለው ነው በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን የሰጠ ሲሆን ብይኑ እስከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች እንዲፀና ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች በግዥ ያገኙትን ቤት በተመለከተ መብታቸውን ለማስከበር መጀመሪያ ክርክሩ መብቴን ሊነካ ይችላል ብለው ባሰቡትና በኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በአሁኑ ተጠሪዎች መካከል ይካሄድ በነበረው ክርክር ጣልቃ ገብተው ለመከራከር ቢያመለክቱም የተያዘው ክርክር ካለቀ በኋላ ከመቅረብ በቀር አሁን ጣልቃ ገብተሽ መከራከር አትችይም ተብለው አቤቱታቸው ውድቅ ስለተደረገባቸው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅና በፍ/ብሔር ስነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት አቤቱታቸውን

ቢያቀርቡም የፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ከዚህ ቀደም በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች ታይቶ ውሳኔ ተሰጥቶበት ፍርዱ የተፈፀመ ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን አናስተናግድም (አያስከስስም) በማለት አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠታቸው አመልካች የግል ንብረታቸውን የሚመለከተው ጉዳይ ለፍርድ ቤቶች አቅርበውና ተከራክረው መብታቸውን እንዳያስከብሩና ፍትሕን እንዳያገኙ ተደርገዋል፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተደነገጉት ፍትሕ የማግኘትና የንብረት መብቶች ጋር የሚጋጭ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ፣

ሚያዝያ 22 ቀን 2010 ዓ.ም

የመ/ቁ. 43/10

---

## 2.5 አመልካች፡- ወ/ሮ ሃይማኖት ሰብስቤ፣ ተጠሪ፡- አቶ አሸናፊ ዓለሜ

የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

አመልካቿ በ16/05/2008 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽፈው ባቀረቡት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36 እና 40 የተደነገገውን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይስጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የክሱ መነሻ በአመልካች ወ/ሮ ሃይማኖት ሰብስቤ እና በተጠሪ አቶ አሸናፊ ዓለሜ መካከል ጥር 29 ቀን 1991 ዓ.ም የተፈጸመው ጋብቻ በ11/04/2000 ዓ.ም በፍቺ ሲፈርስ የጋራ ንብረት ክፍፍልን

የሚመለከት ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር አዲስ ከጋብቻ አንድ ዓመት በፊት ጅምር ቤት በአሁን ተጠሪ በ1990 ዓ.ም የተገዛ ስለሆነ የአሁን ተጠሪ አቶ አሸናፊ ዓለሜ የግል ንብረት ነው ተብሎ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ይህ ውሳኔም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጸንቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው የአሁን አመልካች የተፈጸመው የሕግ ስህተት እንዲታረምላቸው የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱም አመልካቿ ከጋብቻ በኋላ ለቤቱ የግንብ አጥር ማሠራታቸውን፣ ግቢውን ሊሾ ያደረጉ መሆኑን፣ ለግቢው የብረት በር፣ ለቤቱ ፍሬንች በር ማስገጠማቸውን፣ እንዲሁም ሽንት ቤትና ኮርኒስ በጋራ ያሠሩ መሆኑን መከራከሪያ አቅርበው እያለ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ በመሀንዲስ ተገምቶ በጋብቻ ወቅት በጋራ ያወጡት ወጪን የአሁን ተጠሪ ግማሹን ለአመልካቿ እንዲሰጥ መወሰን ሲገባው ይህን ሳያደርግ መቅረቱ አግባብ አይደለም በማለት እንደገና ግምቱን በመሀንዲስ አስገምቶ እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ.343 መሠረት መልሶለት ከላይ የተዘረዘሩትን ማሻሻያዎች ለማድረግ የወጣው ወጪ በወቅቱ ዋጋ ተመን ብር 600,169.99 (ስድስት መቶ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ከዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም) መሆኑን አስገምቶ የአሁን ተጠሪ የግምቱን ግማሽ ገንዘብ ለአመልካች ሲሰጥ አመልካች ቤቱን ለአሁን ተጠሪ እንድታስረክብ ወስኖ ይህ ውሳኔ እስከፌ/ጠ/ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ መጽናቱን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

የአሁን ተጠሪ አቶ አሸናፊ ዓለሜ በ1990 ዓ.ም በብር 100,000 (መቶ ሺህ) ከጋብቻ በፊት ቤቱን የገዙ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ከጋብቻ በኋላ ለቤቱ ማሻሻያ የወጣው ወጪ ግምቱ ብር 600,169.99 (ስድስት መቶ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ከዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም) መሆኑ ሲታይ መጀመሪያ ቤቱ ከተገዛበት ዋጋ የበለጠ ስለሆነ አንድ መቶ ሺህ ብሩ ለአሁን ተጠሪ ተመልሶላቸው ቤቱ የጋራ እንዲሆን መደረግ ሲገባው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይህን አለማድረጉ የአመልካችን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 40 የተደነገገውን ሕገ መንግሥታዊ መብትን የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ለመጨረሻ ውሳኔ ለተከበረው የፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል፡፡

የአሁን ተጠሪ አቶ አሸናፊ ዓለሜ ከጋብቻ በፊት በ1990 ዓ.ም በብር 100,000.00 (በአንድ መቶ ሺህ ብር) የገዙት ጅምር ቤት የግል ንብረታቸው መሆኑን አረጋግጠው ለቤቱ ማሻሻያ በጋብቻ ወቅት ከጋራ ገቢ የተደረገው ወጪ በመሀንዲስ ተገምቶ ግማሹ ብር ለአሁኗ አመልካች ሲከፈል አመልካቿ ቤቱን ለአሁን ተጠሪ እንድታስረክብ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ተወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ባቀረቡት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መነሻነት የፌዴራል የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በጋብቻ ወቅት ለቤቱ የተደረገው የማሻሻያ ወጪ ከተገዛበት ገንዘብ የበለጠ መሆኑን ጠቅሶ የአሁን ተጠሪ ጅምር ቤቱን የገዙበት ገንዘብ ተመልሶላቸው ቤቱ የጋራ ንብረት ሊሆን ይገባል በማለት የአሁን አመልካች ወ/ሮ ሃይማኖት ሰብስቤ ያቀረቡትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በመቀበል የፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 35 (3) እና 40 የተደነገገውን መብት የጣሰ ነው በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን ምክር ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35 (3) ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡

በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው በማለት ተደንግጓል፡፡

ከዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ሴቶች በበታችነት እና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለያዩ መስኮች ማለትም በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ምንም እንኳን ጉዳዩ ከኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ባልና ሚስቱ በፍርድ ቤቶች ባደረጉት የንብረት ክፍፍል ክርክር አንደኛው ተጋቢ ወይም ባልየው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ንብረቱ ከጋብቻ

በፊት የተፈራ መሆኑን ባስረዳበትና ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ባረጋገጡበት ሁኔታ የአሁን አመልካች በሴትነታቸው የአዎንታዊ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አግባብ ሊኖር አይገባም፡፡ ሴቶች የአዎንታዊ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ጉዳዮች እንደ ትምህርት፣ የሥራ ስምሪት ወ.ዘ.ተ እንጂ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት ማስረጃ መሠረት ጉዳያቸው ተመርምሮ ውሳኔ በሚሰጥበት የፍትሕ መድረክ ላይ አይደለም፡፡

በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25 ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ እንደሚደረግላቸውና በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ ወዘተ. ልዩነት ማድረግ ክልክል መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ፣ የአሁን አመልካች ሴት በመሆናቸው በተለየ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አግባብ የለም፡፡ በጋብቻ ወቅት ለቤቱ ማሻሻያ የተደረገው ወጪ ግምት ግማሹን እንዲካፈሉ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 የተደነገገው የአመልካች የንብረት መብት ተጥሷል ማለት አይቻልም፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ዓላማ በመንግሥት አካላት ወይም ባለሥልጣናት ውሳኔ የዜጎች መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ሲጣሱ ለማስተካከል የሚፈጸም እንጂ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተጠቅመው ግራ ቀኙን አከራክረው ማስረጃ መዝነው የሰጡትን ውሳኔ በይግባኝ ማረም አይደለም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በፍሬ ነገር ደረጃ ቤቱ የአሁን ተጠሪ የግል ንብረት መሆኑ ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ እያለ ቤቱ የተገዛበትንና ለቤቱ ማሻሻያ የወጣውን ገንዘብ መጠን በማነጻጸር በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ  ሲያጣራ የአሁን ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ጅምር ቤቱን የገዙት 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ስለሆነ አመልካችና ተጠሪ ከተጋቡ በኋላ ለቤቱ ማሻሻያ የወጣው ወጪ 600,169.99 (ስድስት መቶ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ከዘጠና ሳንቲም) በመሆኑ ጅምር ቤቱ ከተገዛበት ዋጋ ስለሚበልጥ በሚል ምክንያት ብቻ 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ተመልሶላቸው ቤቱ የጋራ ንብረት ሊሆን ይገባል በማለት አቤቱታው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 ከተደነገገው የእኩልነት መብት ጋር የሚጣረስ በመሆኑ፣

በተጨማሪም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች  አጣሪ ጉባዔ በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 ከተሰጠው ኃላፊነት ውጪ ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ አጣርተው ውሳኔ የሰጡበትን

ጉዳይ በማስተካከል ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ባለመሆኑ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት የለውም፤ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ/ቁ.80/12

---

### 2.6 አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ብርሃኔ ዮሴፍ (2 ሰዎች)፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ የውብዳር ከበደ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሚያዝያ 03 ቀን 2009 ዓ.ም ለጉባዔው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የውርስና የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት የተጀመረ ክርክር ነው፡፡

አንደኛ አመልካች ለፍ/ቤቱ ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከሟች አቶ ዋቁማ በረደድ ጋር ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው በመኖር ህጻን የሚዩ ዋቁማ

የወለዱ መሆኑን በመግለጽ አቶ ዋቁማ ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ በመሆናቸው፣ ህፃኗ የወላጅ አባቷ ንብረት ወራሽ በመሆኗ የሟች ድርሻ እንዲወሰንላት፤ አመልካች ከሟች ጋር የጋራ ንብረታችን ነው ያሉትን በየካ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 670 የሚገኝ መኖሪያ ቤት ፣የሠሌዳ ቁጥር 2-71506 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ በኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ እና በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ በሟች ስም ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/145 መሠረት ፍ/ቤቱ በትእዛዝ ማስረጃውን በማስቀረብ አጣርቶ እንዲያካፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአሁን ተጠሪ ከላይ የተገለጸው ቤትና መኪና ምንም መብት ሳይኖራቸው የያዙ በመሆናቸው እንዲያስረክቧቸው ፍ/ቤቱ ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ለፍ/ቤቱ ጽፈው ባቀረቡት መልስ ህፃን የሚዬ የሟች ልጅ አይደለችም፤ ሟችም ከአመልካች ጋር እንደ ባልና ሚስት አብረው አልኖሩም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ከጥቅምት 27 ቀን 1989 ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት አብረው መቆየታቸው እና ከ2000 ዓ.ም በኋላም ጋብቻ መሥርተው ባልና ሚስት ሆነው መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰው መኖሪያ ቤትም የወላጆቼ ነው በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት አመልካች በተለያዩ ባንኮች ገንዘብ መቀመጡን የሚያስረዳው ሰነድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 145 መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት አልፎታል፡፡ አመልካች ከሟች ጋር የጋራ ንብረታችን ነው በማለት ፍ/ቤቱ እንዲያስረክባቸው የጠየቁት በየካ ክ/ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤትም የተጠሪ ወላጆች ነው ሲል ወስኗል፡፡ በክርክር ያለው መኪና በተመለከተ ተጠሪ ንብረቱ የሟች አይደለም በማለት በግልፅ ያልካዱ በመሆኑ እና ህፃን የምዬ የሟች ልጅ መሆኗ ከዚህ በፊት በፍርድ ቤት በመረጋገጡ፣ አመልካችም ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት ከ3 ዓመት በላይ መኖራቸው በማስረጃ ያረጋገጡ በመሆኑ፣ ተጠሪም የሟች ሚስት መሆናቸው በጋብቻ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ በመሆኑ መኪናው ለሦስቱ ተከራካሪዎች ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካችና ተጠሪ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡ አሁንም አመልካችና ተጠሪ በስር

ፍርድ ቤት ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት አቅርበው ችሎቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችን በመመርመር የግራ ቀኙን የሕግ ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በሟች ስም በባንክ የተቀመጠ ገንዘብና የአክሲዮን ድርሻ የሚመለከት ማስረጃ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145 መሠረት በፍ/ቤቱ በኩል በትእዛዝ እንዲቀርብላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱ ጥያቄያቸውን ሳይቀበል በማለፍ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት የስር ፍርድ ቤት ማስረጃው አስቀርቦ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት መልሶታል፡፡

እንዲሁም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት አብረን ነበርን ያሉት ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም በመሆኑና ተሽከርካሪው በ2000 ዓ.ም አመልካች ከሟች ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተቋርጦ በነበረበት ወቅት የተፈራ ስለሆነ፣ አመልካች በተሽከርካሪው ላይ ድርሻ አላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል ሲል ተሽከርካሪው ለህጻን የሚዩ እና ለተጠሪ ብቻ ለሁለት እኩል ሊካፈል ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል ችሎቱ ወስኗል፡፡ ችሎቱ ክርክር ያስነሳው ቤት በተመለከተ የተጠሪ ወላጆች ነው መባሉ የሚነቀፍ አይደለም ሲል በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡ ጉዳዩን የያዘው የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በባንክ የተቀመጠውን ገንዘብ እና የአክስዮን ድርሻ በተመለከተ አጣርቶ እንዲወስን በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145 አስፈላጊውን ትእዛዝ በመስጠት ያለውን ገንዘብ እና የአክስዮን ድርሻ አጣርቶ ገንዘቡ እና አክስዮኑ ለተጠሪ እና ለህፃን የሚዩ እኩል እንዲካፈል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ 1/ በኦሮሚያ ክልል የመርቲ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ሟች እስከ አረፉበት ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም የሟች ሚስት መሆኔን በሁኔታ አረጋግጦ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት የተጀመረውን የንብረት ክርክር በመጨረሻ የተመለከተው የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት በጋራ የቆዩት ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም ነው በማለት ከሟች ጋር ከ1993 ዓ.ም በኋላ ያፈራናቸው ንብረቶች እንዳልካፈል መወሰኑ የአመልካች በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠውን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ በመሆኑ 2/ በክርክር ያለው ቤት ሟች ከተጠሪ ወላጆች የገዙት መሆኑን እና በሟች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት የጽሑፍ

ማስረጃ ቀርቦ እያለ ፍ/ቤቱ መኖሪያ ቤቱ የተጠሪ ወላጆች ነው ማለቱ የህጻናን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልን በማለት ጠይቀዋል፡፡ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እና የምክር ቤቱን ባለሙያዎች አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኂላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት አመልካቾች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍርድ ቤት ውሳኔ የሕገ መንግሥት ጥሰት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም፣

1/ አመልካች በኦሮሚያ ክልል የመርቲ ወረዳ ፍርድ ቤት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ሟች እስከ አረፉበት ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም የሟች ሚስት መሆኔን በሁኔታ አረጋግጦ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት የተጀመረውን የንብረት ክርክር በመጨረሻ የተመለከተው የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት በጋራ የቆዩት ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም ነው በማለት ከሟች ጋር ከ1993 ዓ.ም በኋላ ያፈራናቸው ንብረቶች እንዳልካፈል መወሰኑ በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠልኝን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ነው በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በተመለከተ፣

አመልካች አያይዘው ባቀረቡት ማስረጃ በኦሮሚያ ክልል የመርቲ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 15013 ሰኔ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሠረት ከሟች ጋር ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ሟች እስከ አረፉበት ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም በጋብቻ አብረው የቆዩ መሆናቸው በሁኔታ አስረድቷል ሲል መወሰኑ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የንብረት ክርክሩ ለተመለከተው የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት ዳኝነት እንዲሰጥበት የጠየቁት ከሟች ጋር ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው መኖራቸውን ብቻ የሚመለከት እንጂ የሟች ሚስት መሆናቸውን በመግለጽ አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ አመልካች እንዲሰጣቸው በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ውሳኔ መስጠቱን አትቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በኦሮሚያ ክልል መርቲ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው የሟች ሚስት የነበሩ

መሆናቸውን በሁኔታ ያስረዱ ቢሆንም የንብረት ክርክር ባደረጉበት ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ከሟች ጋር ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን በመግለጽ በጋራ ያፈሩት ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በመሆኑ እና ፍ/ቤቱም አመልካች እንዲሰጣቸው በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ሕግንና ማስረጃን መሠረት በማድረግ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ውሳኔው የአመልካችን በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠላቸው መብት የሚጥስ አይደለም፡፡

2/ ክርክር የተነሳበት መኖሪያ ቤት ሟች ከተጠሪ ወላጆች የገዙት መሆኑን እና በሟች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት የጽሑፍ ማስረጃ ቀርቦ እያለ ፍ/ቤቱ መኖሪያ ቤቱ የተጠሪ ወላጆች ነው ማለቱ የህጻናን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ስለመሆኑ የቀረበው ጥያቄ በተመለከተ፣

በአመልካቾች ከቀረበው መዝገብ መረዳት እንደተቻለው በክርክር ላይ ያለው መኖሪያ ቤት ሟች ከተጠሪ ወላጆች በጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም የገዙት መሆኑንና የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤትም የቤ/ቁ 670 የሆነ ይዞታ በሟች ባለቤትነት ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ለፍ/ቤቱ ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት መኖሪያ ቤቱ በሟች ባለቤትነት ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ማረጋገጫ የቀረበለት ቢሆንም መኖሪያ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ተከሳሽ ወይም ጣልቃ ገብ በመሆን በመኖሪያ ቤቱ ላይ የባለቤትነት ክርክር በማንሳት ዳኝነት ላልጠየቁት ለተጠሪ ወላጆች ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ፍ/ቤቱ በመኖሪያ ቤቱ ላይ የሰጠው ውሳኔ ህጻን የምዬ በሕገ መንግሥቱ እና ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው የህጻናትን መብት የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንጻር ያለው አንደምታ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 24 መሠረት ህጻናት አካለ መጠን ባለመድረሳቸው ምክንያት የሚያጋጥማቸው የመብት ጥሰት ለመከላከል በቤተሰባቸው፣ በማኅበረሰቡ እና በመንግሥት አስፈላጊ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ ኢትዮጵያ ካጸደቀቻቸው ስምምነቶች መካከል አንዱ የሆነውን የዓለም አቀፍ የህጻናት መብቶች ስምምነት በመግቢያው ላይ ህጻናት በአካል እና አእምሮ ያልበሰሉ በመሆናቸው ምክንያት ልዩ ጥበቃ እና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያስገድዳል፡፡ በአንቀጽ 3/1/ መሠረትም የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች ህጻናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች በሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈጻሚው

እንዲሁም በፍርድ ቤት የሚወሰዱ እርምጃዎች የህጻናትን ጥቅም ቅድሚያ ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአፍሪካ ህጻናት መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች የህጻናትን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስፈልጉ እርምጃዎች ለመውሰድ ግዴታ ገብተዋል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 መሠረትም የመንግሥት ተቋማት ፍርድ ቤትን ጨምሮ ህጻናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች እርምጃ በሚወስዱበት ጊዜ የህጻናት ጥቅም በቅድሚያ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 41/5/ መንግሥት የህጻናትን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አቅም በፈቀደ ደረጃ እንክብካቤ ማድረግ እንደሚጠበቅበትም ያስገድዳል፡፡ ውርስ ህጻናት ንብረት ከሚያፈሩበት መንገዶች አንዱ በመሆኑም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 መሠረት ጥበቃ የሚደረግለት ነው፡፡

በመሆኑም ከሕገ መንግሥቱ እና ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ለመረዳት የሚቻለው የህጻናት መብት እና ጥቅም ማስከበር በሚመለከት ጉዳዩ ለሞግዚቶቻቸው ብቻ የሚተው ሳይሆን መንግሥትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚመለከታቸው መሆኑን ነው፡፡ በተለይ ፍ/ቤቶች የህጻናትን ጉዳይ የሚመለከት ክርክር የሚያስተናግዱ እና ውሳኔ የሚሰጡ በመሆናቸው በሚሰጡት ውሳኔ የህጻናትን ጥቅም እንዲጠበቅ የተቻላቸውን ማድረግ እንደሚገባቸው መረዳት ይቻላል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ መኖሪያ ቤቱ በህጻን የምዬ አባት ባለቤትነት ስም የተመዘገበ መሆኑን የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት የገለጸ በመሆኑ፣ በሟች እና በተጠሪ ወላጆች መካከል የቤት ሽያጪ ውል መደረጉ የሚያሳይ የውል ስምምነት በመኖሩ፣ የተጠሪ ወላጆችም በክርክሩ ተካፋይ በመሆን በመኖሪያ ቤቱ ላይ የባለቤትነት ክርክር በማንሳት ዳኝነት ሳይጠይቁና በአመልካቾች በኩል የቀረበውን ማስረጃ ሳያስተባብሉ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ወላጆች የመኖሪያ ቤቱ ባለቤት ናቸው በማለት መወሰኑ ሕገ መንግሥቱ የህጻኗን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር ለፍ/ቤቱ የሰጠውን ሚና ግምት ውስጥ ያላስገባና ህጻኗ በመኖሪያ ቤቱ ከሟች ሚስት የነበሩት ከተጠሪ ጋር ሟችን በመተካት ድርሻዋን እንዳትካፈል በመከልከል ተጠቃሚነቷን የሚያስቀር በመሆኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36፣ 40፤41/5/፣79/3/ ጋር የሚቃረን ውሳኔ ነው፡፡

በመሆኑም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት መኖሪያ ቤቱ የተጠሪ ወላጆች ነው የሚለው የውሳኔው ክፍል ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

### የኢ.ፌዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 4ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ጉባዔ፣

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ. 47/10

---

## 2.7 አመልካች፡- ወ/ሮ ሸዋዬ ሙላት፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ አረጋሽ ባዲ

የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የመኖሪያ ቤት ባለቤትነትና የውርስ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በአሁን አመልካች ላይ በመሠረቱት ክስ ከባለቤቴ አቶ ዓለማየሁ ታደሰ ጋር በ1985 ዓ.ም ተጋብተን ስንኖር ሞግዚት የሆንኩላቸውን ልጆች ወልደን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥሩ አዲስ

የሆነ ሰነድ አልባ ቤት ሰርተን እየኖርን እኔ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር በመሄዴ ተከሳሽ ወይም የአሁን አመልካች በቤት ሠራተኛነት ተቀጥረው እየሠሩ እያለ ባለቤቴ ሞቷል፡፡

ተከሳሽ ይህን ቤት ይዘው ከሚጠቀሙበት በተጨማሪ እኔ የሟች አቶ ዓለማየሁ ሚስት እና የልጆች ሞግዚት መሆኔን በፍርድ ቤት ባቀረብኩት አቤቱታ ላይ ተቃዋሚ በመሆን ቀርበው ስንከራከር ከቆየን በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚስት መሆኔን እና የልጆቹ አሳዳጊ መሆኔን በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ወይም የአሁን አመልካች ቤቱን እና በቤቱ ውስጥ የሚገኙትን ቁሳቁስ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ተከሳሽ በመሆን በሰጡት መልስ ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ከሳሽ የሟች ንብረት መስሏቸው እንዲጣራላቸው ለውርስ አጣሪ አቅርበው ቤቱ የሟች እንዳልሆነ ተረጋግጧል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ የሚስትነት እና የልጆች ሞግዚትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ አቅርበው እኔም ይህንኑ በመቃወም ስንከራከር ቆይተን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ፣ ውሳኔው እኔ በሚስትነቴና በወለድኳት ልጅ ሞግዚትነት የማቀርበውን የመብት ጥያቄ የማያግድ መሆኑ ተወስኖልኛል፡፡ በተጨማሪም ይህ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት በግሌ ያፈራሁት እንጂ የሟች አይደለም እንዲሁም የቤቱ አድራሻ በግልፅ ስላልተገለፀ ከሳሽ ለመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የሰው ምስክር ከሰማና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የቀረቡት የከሳሽ ወይም የአሁን ተጠሪ ምስክሮች ከአሁን አመልካች ምስክሮች በበለጠ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ሟች እና ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) በጋራ የሠሩት ነው በማለት የአሁን አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እና ለሟች ሦስት ልጆች አመልካች የወለደችውን ልጅ ጨምሮ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ከማስረጃ ምዘናና ከፍሬ ነገር ክርክር ጋር የተያያዘ ስለሆነ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሳኔ የእኩልነት እና የንብረት ሕገ መንግሥታዊ መብቴን የሚጋፋ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ ሲሉ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታም ከሚች አቶ ዓለማየሁ ታደሰ ጋር በሀገር ባህል በ1995 ዓ.ም ተጋብተን በጋራ ስንኖር አሁን ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ቀድሞ የነበረውን ሦስት ክፍል ቤት አፍርሰን በጋራ አዲስ 8 (ስምንት) ክፍል ቤቶችን በመጨመር ሠርተን ስንጠቀም የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም መጀመሪያ ለፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ላይ አሁን ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት እኔ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር ከሄድኩ በኋላ ተከሳሽ እኔ ሠርቼ የሄድኩትን ቤት አከራይተው በግላቸው ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችን ገንብተዋል በማለት ቤቶቹን እኔ ከሚች ጋር መሥራቴን አምነው እያለ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በክሳቸው ባላቀረቡት አዲስ ጭብጥ ላይ ማስረጃ በመስማት አዲስ የተሠሩት ቤቶች ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ የተሠራ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ አላግባብ ነው፡፡

ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ሲሠራ እኔ ከሚች ጋር በቤቱ ውስጥ ያለሁ መሆኔ በግራ ቀኛችን ያልተካደና በምስክሮች የተደገፈ ሆኖ ሳለ በአቀረብኩት ክርክር አግባብ ቤቱ የግሌ መሆኑ በምስክሮች ባይረጋገጥ እንኳ የሚች ሚስት መሆኔ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ በሚስትነቴ ማጣት የሌለብኝን ሕገ መንግሥታዊ የእኩልነትና የንብረት መብት ፍርድ ቤቶች እንዳጣ ስላደረጉኝ በውሳኔው ላይ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባዔው አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ከኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር የመረመረው ሲሆን አመልካችና ተጠሪ የሚች አቶ ዓለማየሁ ታደሰ ሚስቶች መሆናቸው በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ነገር ግን የንብረት ክፍፍልና የውርስ ሀብት ክፍፍልን በተመለከተ የአሁን አመልካች ምስክሮች አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የግላቸው መሆኑን በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ ተጠሪ ወደ ውጭ ሀገር ከመሄዳቸው በፊት ከሚች ጋር ከሠሩት ቤቶች በተጨማሪ እርሳቸው ወደ ውጭ ከሄዱ በኋላ ተጨምረው የተሠሩት ሌሎች ክፍሎችም የተሠሩት በአመልካችና በሚች ሳይሆን ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ መሆኑ በሰው ምስክሮች (በተጠሪ ምስክሮች) ስለተረጋገጠ የአሁን አመልካች ቤቱን መካፈል አይችሉም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በማፅናት ወስኗል፡፡

በዚህ ጉዳይ ውስጥ የአሁን አመልካች ለክርክር መነሻ የሆኑት ተጨማሪ ቤቶች ሲሠሩ ከሟች ጋር በቤት ውስጥ የነበሩት አመልካች እንደሆኑና ለሟችም ሚስት መሆናቸው ባልተካደበት እና በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ከሟች ጋር አብረው በሚስትነት ይኖሩበት ከነበረው ቤት ላይ ምንም ዓይነት መብት የላቸውም ወይም በቤቱ ሥራ ውስጥ ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ አላደረጉም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑ በዋና ጭብጥነት መታየት ያለበት ነው፡፡

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34(1) ሴቶች በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) እና (2) መሠረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል በማለት የተደነገገ ሲሆን ይህም ንብረት በጉልበታቸው በመፍጠር ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነ ዋጋ ያለው ውጤት ሊሆን እንደሚችል በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

አሁን በክርክር ላይ ባለው ጉዳይ አመልካች ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ከሟች ጋር ሟች እስከሞቱበት 2003 ዓ.ም ድረስ አብረው ይኖሩ እንደነበር ከፍርድ ቤቶች በተሰጣቸው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ ተጠሪ ደግሞ ከሟች ጋር በ1985 ዓ.ም ተጋብተው አብረው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር እንደሄዱና ሟች ከሞቱ በኋላ ሲመለሱ የአሁን አመልካች በቤቱ ውስጥ እንዳገኟቸው ከክርክራቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ከሟች ጋር በጋብቻቸው ጊዜ እንደሠሩና ነገር ግን የአሁን አመልካችም በፊት ተሠርቶ የነበረው ቤት ላይ ተጨማሪ ቤቶችን በግላቸው የሠሩ መሆኑን ተጠሪ በክሳቸውም የጠቀሱትና ያልካዱት ጉዳይ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ምስክሮች እንዳረጋገጠው ተጠሪ ወደ ውጭ ሀገር ከሄዱ በኋላ የተገነቡት ተጨማሪ ቤቶች የተሠሩት ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ ነው፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ መሠረት ለክርክር ምክንያት ከሆነው ቤት ውስጥ የተወሰነውን አመልካች የሠሩት መሆኑን እና የተጠሪ ምስክሮች ባረጋገጡት አግባብ ደግሞ ተጠሪ ወደ ውጭ ከሄዱ በኋላ የተገነቡት ቤቶች ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ የተገነባ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህንኑ እውነታ የሚያጠናክር ለክርክር

ምክንያት ለሆነው ቤት የመብራት አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልካች ያመለከቱበትና ሌሎች መረጃዎችም ለፍርድ ቤቱ ቀርበው የነበሩ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ለአሁን ተጠሪ ለመወሰን መሠረት ያደረጉት ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ የተሠራ ለመሆኑ ጉዳዩ በሰዎች ምስክር ስለተረጋገጠ ነው የሚል ሲሆን በሌላ በኩል የአሁን አመልካች የሰው ምስክሮች ግን አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግላቸው ወይም በግል የሠሩት መሆኑን አላረጋገጡም በሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች አመልካች ካቀረቡት አቤቱታ አንፃር ቤቱ በግላቸው የተሠራ መሆኑ ባይረጋገጥም እንዲሁም ቤቱ ተጠሪ በላኩት ገንዘብ የተሠራ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ አመልካች የሟች ሚስት ሆነው በቤት ውስጥ እየኖሩ ለተገነቡት ተጨማሪ ቤቶች የጉልበት ወይም የካፒታል አስተዋፅኦ የነበራቸው መሆን አለመሆኑን ግን በአግባቡ ያጣሩት ነገር አልነበረም፡፡ በተጨማሪም ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ራሳቸው ባቀረቡት ክስ አመልካች ቀድሞ የተሠሩትን ቤቶችን አከራይተው ተጨማሪ ክፍሎችን በግላቸው ያሠሩ መሆኑን መጥቀሳቸው በቤቱ ላይ የአመልካች የካፒታልና የጉልበት አስተዋፅኦ ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63 ላይ በግልፅ ተደንግጎ እንደሚገኘው አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ያፈሩት ሀብት የጋራቸው እንደሆነ በሕጉ ግምት የሚወሰድ ነው፡፡ ይህ የሕጉ ግምት አንድ ባል ከአንድ በላይ ሚስቶች ስላሉት ብቻ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ አይኖርም፡፡ አንድ ባል ከአንድ ሚስት በላይ ሲኖረው ብዙ ጊዜ በሚኖሩበት ቦታ ያፈራው ንብረት ቀጥታ ተሳታፊ በሆነችው ሚስት እና በሌላኛዋ ሚስት መካከል መኖር ስለሚገባው የሀብት ክፍፍል ፍርድ ቤቶች ተገቢውን እና ሕጋዊ መፍትሔ ከመስጠት ባሻገር አንደኛዋ ሚስት በንብረት ማፍራት ሂደቱ ላይ አስተዋፅኦ አላበረከተችም በሚል ከሀብት ክፍፍሉ ውጭ ማድረግ የሕጉን ዓላማ የሳተ ነው፡፡

ምክንያቱም በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት ከግል ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች የጋራ ሀብታቸው እንደሚሆን በቤተሰብ ሕጉ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን አንድ ሚስት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተጠቀሰውን ንብረት ለማፍራት አስተዋፅኦ ስለማድረጓ አላስረዳችም

ቢባልም በባሏ ጥረት በተፈራው ንብረት ላይ የጋራ ተጠቃሚ ለመሆን ሕጉ መብት ይሰጣታል፡፡

ከዚህም የሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው አመልካች ሚስት መሆናቸው እስካልተካደ እና ከባላቸው ጋር ይኖሩ እንደነበር ከተረጋገጠ የንብረት ክፍፍል ድርሻ ጥያቄያቸው ውድቅ መደረግ የለበትም፡፡

በዚህ መሠረት የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ሲሠራ በቤቱ ውስጥ ከሟች ጋር እንደነበሩ ያልተካደና በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ ራሳቸው ባቀረቡት ክስ ላይ የአሁን አመልካች ቀድሞ ራሳቸው የሠሩት ቤት አከራይተው ከኪራይ ባገኙት ገንዘብ ተጨማሪ ቤቶችን የገነቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም አመልካች ለቤቱ የመብራት አገልግሎት ለማግኘት ያመለከቱበት የጽሑፍ ማስረጃም በመዝገብ ውስጥ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ሁሉ መረዳት እንደሚቻለው ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ሲሠራ የአሁን አመልካች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋፅኦ ያደረጉ መሆኑን ነው፡፡

የአመልካች አስተዋፅኦ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የለበትም ቢባልም እንኳን ከላይ በተጠቀሰው አግባብ አመልካች በሟች ባለቤታቸው የተፈራውን የጋራ ሀብት መካፈል ሕጋዊና ሕገ መንግሥታዊ መብት ይኖራቸዋል፡፡

ሲጠቃለል የቤተሰብ ሕጉ ባልና ሚስት በትዳር አብረው በሚኖሩበት ጊዜ በጋራ ያፈሩት ሀብት የጋራ ሀብታቸው እንደሆነ ግምት መወሰድ እንዳለበት በግልፅ ከሚደነግገው መርህ ጋር ጉዳዩ ታይቶ ሁለቱም ሚስቶች (አመልካችና ተጠሪ) ከንብረቱ ላይ ማግኘት የሚገባቸውን ድርሻ እንዲያገኙ መወሰን ሲገባው ከሟች ጋር የነበሩት አመልካች ከቤቱ ላይ ምንም ዓይነት መብት የላቸውም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያርመው መቅረቱ የአመልካችን ከላይ የተጠቀሱትን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች የሚጥስ ነው፡፡

ስለዚህ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 135833 ላይ በቀን 27/11/2009 በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢፌዴሪ ሕገ

መንግሥት አንቀጽ 84(1) እና በአዋጅ ቁጥር 798 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ መርቶለት፣ ኮሚቴውም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም አመልካች ከሟች ዓለማየሁ ታደሰ ጋር በ1995 ዓ.ም በባህል ጋብቻ ተጋብተው አቶ ዓለማየሁ ታደሰ በሞት እስከተለየበት 2003 ዓ.ም ድረስ አብረው መኖራቸው ያልተስተባበለ ሲሆን በጋብቻ ወቅት በጋራ ያፈሩት ንብረት ታስቦ የድርሻቸውን ተካፋይ መሆን ሲገባቸው የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በጋብቻ ወቅት ያፈሩትን ንብረት ጨምሮ ለወ/ሮ አረጋሽ ባዲ እና ለሟች ልጆች እንዲያስረክቡ ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ለአመልካች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25፣ 34 እና 40 ንዑስ አንቀጽ/1 እና 2/ የተረጋገጡላቸውን መብቶች የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. የንብረት መብትን አስመልክቶ የተሰጡ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች

---

የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 4ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ. 63/10

---

## 3.1አመልካች፡- ወ/ሮ አሚና አብዱልቃድር፣ ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ከድር መሃመድ(4 ሰዎች)

የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ ሰውሂ ቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤት በመሠረቱት ክስ የወላጅ አባቴ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ በመቀሌ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኘውን ቤት ኪራይ እንድሰበስብ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ማኅበራዊ ፍ/ቤቱም ወራሽነታቸውን አረጋግጦ የቤት ኪራይ እንዲሰበስቡ የሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሰሜን ወረዳ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ቤቱ የእርሱ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም ማስረጃ ባለማቅረቡ አመልካች የቤቱን ኪራይ ከቀን 1/06/2000 ዓ.ም ጀምሮ ከተከራዮች እንዲሰበስቡ በማለት የማኅበራዊ ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የመቀሌ ከተማ ማዕከላዊ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ባለቤትነት የአመልካች መሆን አለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታና ተከራካሪ ወገኖች በቤቱ ላይ ምን ዓይነት መብት እንዳላቸው ሳይታወቅ በደፈናው የቤት ኪራይ ለወ/ሮ አሚና ይከፈል ተብሎ የተወሰነው አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ክርክር የተነሳበት ቤትና ቦታ የአመልካች አባት የሆኑት የአቶ አብዱልቃድር መሀመድ መሆኑ አመልካችም ወራሽ መሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት የቀበሌ ማ/ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህም ውሳኔ ለክልሉ ሰበር ችሎት ቀርቦ የተፈፀመ የሕግ ስህተት አለመኖሩ ተገልጾ ፀንቷል፡፡

በሌላ በኩል ሌሎች ሰዎች በዚሁ ቤት ላይ በሰሜን ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ክስ መሥርተዋል፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት አላግባብ ይዘዋል የሚል ነው፡፡ በክርክሩም ከሳሾች ለራሳቸው ካስወሰኑ በኋላ አመልካች ይግባኝ እያሉ እስከ ሰበር ቢከራከሩም ውሳኔው ጸንቷል፡፡

አመልካች ለቀበሌው ማኅበራዊ ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ መስርተው ማ/ፍ/ቤቱም ለአመልካች የተወሰነ ሊፈጽም የሚችል የጸና ውሳኔ የለም በማለት ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

በዚህም ምክንያት ለይግባኝ ፍ/ቤቶች ቀርቦ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ አመልካች ይህን የአፈጻጸም ክርክር ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ችሎቱም አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ በሌሎች ሰዎች ክስ ሲቀርብባቸው ጉዳዩ ቀድሞ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 5 መሠረት ተቃውሞ ማቅረብ ሲኖርባቸው ይህን ስላላደረጉ የሁለተኛው ውሳኔ ሊሻር አይገባውም በማለት ወስኗል፡፡ ውሳኔውም ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቢቀርብም የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ለጉባዔው ያቀረቡት ጥያቄ ከተጠሪዎች ጋር በነበረኝ የንብረት ክርክር በፍ/ቤቶች ባለመብት መሆኔ ተወስኖልኝ ሳለ ፍርዱ ሳይሻር በአፈጻጸም ወቅት የሚፈጸም ውሳኔ የለም በማለት ያስተላለፉት ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብቴ የሆነውን አንቀጽ 13፣ 40 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 እና 37 ስለሚቃረን ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ክርክሮች ተካሂደዋል፡፡ በመጀመሪያው ክርክር አመልካች የቤቱ ባለቤት ለሆኑት አባታቸው ሕጋዊ ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ የቤት ኪራይ እንዲሰበስቡ ተወስኖላቸዋል፡፡ ክርክር በተነሳበት ንብረት ላይ በአመልካች ላይ በተመሠረተ ሌላ ክስ አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር በመሆን ቤቱን ሽጠው እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡ ይህም ውሳኔ በቤቱ ላይ ሌሎች ሰዎች መብት ያላቸው ስለሆነ አመልካች ብቸኛ ባለመብት ያለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ ይህ ሁለተኛ ክስ በከሳሾቹ ይግባኝ ባይነት አመልካች ቀድሞ ተወስኖ ያደረ መሆኑን መቃወሚያ ባለማቅረባቸው ቤቱ ለእሳቸው አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

ጉዳዩ በጉባዔው ጽ/ቤት በኩል እንዲጣራ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት በሁለተኛው ክርክር ወቅት የክሱ ይዘት ምን እንደሆነ ለማወቅና ለመረዳት ማስረጃ እንዲቀርብ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠይቆ የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሰሜን ምድብ ችሎት ውሳኔ ያሳለፈበትን የመዝገብ ግልባጭ ተልኳል፡፡ በዚህ መዝገብ ላይ እንደተገለፀው አመልካች አንደኛ የአፈጻጸም ተከሳሽ የነበሩና የክሱ ይዘትም በመቀሌ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኘውን በሚች አቶ አብዱልቃድር መሃመድ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት አመልካች የሚችና የባለቤታቸው ወ/ሮ ለምለም ቀጥታ ተወላጅ በመሆናቸው ቤቱን ከ2ኛ

ተከሳሽ ከድር ሃጂ መሃመድ ጋር ለብቻቸው መያዛቸው አግባብ አይደለም፣ የአያቶቻችን ንብረት የሆነውን ቤት የድርሻችንን ለመውሰድ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የውርስ ሀብት የግራቀኙ በመሆኑና አመልካችም ከሳሾች የድርሻቸውን እንዲወስዱ የተስማሙ ስለሆነ፣ 2ኛ የአፈጻጸም ተከሳሽ አቶ ከድር ሐጂ መሃመድ ያላግባብ ቤቱን ወደ አባታቸው ወደ አብዱልቃድር መሃመድ ማዞራቸው አግባብ ስላልሆነ ቤቱ ለስምንቱ ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ መዝገብ መረዳት እንደሚቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የግራ ቀኙ የውርስ ሀብት መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ክርክር ይግባኝ ተጠይቆበት አመልካች በቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው ተወስኗል፡፡ በዚህ ክርክርና ውሳኔ አመልካች ቀድሞ የተወሰነላቸውን መብት አጥተዋል፡፡

በመጀመሪያው ክርክር በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት ቤቱ በአመልካች አባት ስም የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም የአባታቸው ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት አስወስነዋል፡፡ ይህ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ በሁለተኛው መዝገብ አመልካች የወራሽነት መብታቸውን አጥተዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ላይ በይግባኝ ለክልሉ ሰበር ችሎት ቀርቦ ችሎቱም ጉዳዩ ቀድሞ የተወሰነ መሆኑ በተቃውሞ መልክ ሁለተኛው ክርክር በአመልካች በኩል ስላልተጠየቀ በማለት አመልካች መብታቸውን እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ በሁለቱም ክርክር ወቅት ያሉት ግራ ቀኝ ወገኖች ዘመዳሞች መሆናቸው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ውሳኔዎቹ ላይ በግልጽ አይቀመጥ እንጂ መጀመሪያ በሌሎች ሰዎች እጅ የነበረን ንብረት በሕግ ወራሽነት አስወስነው ቤቱን ይዘው በዚሁ ቤት ላይ ሌላ ክርክር ሲነሳ ወራሽነታቸውን ቀድመው በፍርድ ማስወሰናቸው በክርክር ጊዜ አልቀረበም የሚለው አሳማኝ ነጥብ አይደለም፡፡ የክርክሩም ይዘት አንድ ዓይነት በመሆኑ መቃወሚያው አልተጠየቀም ማለት አይቻልም፡፡

ጉዳዩን ይበልጥ ለማጣራት ግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ጉባዔው ላይ በመቅረብ እንዲያስረዱ በታዘዘው መሠረት አመልካች ቀርበው እንደገለፁት ክርክር የተነሳበት በመቀሌ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኝ ቤት የውርስ ሀብት መሆኑን አመልካችም ከ8 ልጆች ውስጥ እርሳቸው አንድ ወራሽ መሆናቸውንና ቀድሞም ለእርሳቸው ብቻ ተወስኖላቸው የነበረ መሆኑን

አስረድተዋል፡፡ አመልካች በሰጡት ቃል ቤቱ የውርስ ሀብት መሆኑን ከማመን በተጨማሪ ለሁሉም 8 ወራሾች ተጠሪዎችን ጨምሮ ለመከፋፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰሜን ወረዳ ፍርድ ቤት የቀረበው ክስና ውሳኔ እንደሚያስረዳው ቤቱ የውርስ ሀብት መሆኑን ሟችም አመልካችን ጨምሮ 8 ልጆች ያላቸውና ሁሉም ልጆች መከፋፈል ያለባቸው መሆኑን ይገልጻል፡፡

የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የአመልካች አባት የነበረና በአባታቸውም ሞት ምክንያት ሁሉም ተወላጆች ባላቸው ሕጋዊ መብት ምክንያት የቤቱ ወራሽ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም አግባብ ፍ/ቤቱ ሁሉንም ተወላጆች የቤቱ የጋራ ወራሽ ማድረግ ሲገባውና እንዲሁም የፀና ውሳኔ እያለ አመልካችን ከውርስ ንብረት እንዲነቀሉ ማድረጉ የአመልካችን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ነው፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ በተደረገው ክርክር ቀድሞ ለአመልካች የተወሰነውንና አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ቤት እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች በሕገ መንግሥቱ የተከበረላቸው የንብረት መብታቸው በሕግ ከተደነገገው ውጭ የተነፈገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባዔው የውሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት ቋሚ ኮሚቴው የአጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎች ያቀረቡትን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባዔውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአመልካችን የንብረት ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔውና ቋሚ ኮሚቴው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1) እና (2) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት**

**5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ጉባዔ**

**መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም**

**የመ/ቁ. 76/11**

3.2. የጉዳዩ አቅራቢ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ተጠሪ፡- የለም

የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 150818 ሰኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም በአመልካች አቶ ዓለማየሁ ተሰማ እና በተጠሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ መካከል ሲካሄድ ከነበረው የኮንደሚኒየም ቤት ዕጣ ጋር የተያያዘ ክርክርን ሲመለከት ቆይቶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለተጠቃሚዎችና ለልማት ተነሺዎች ለማስተላለፍ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44 ሕገ መንግሥታዊነቱ እንዲመረመር በመላኩ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ በብይኑ እንዳሰፈረው የጉዳዩ አጀማመር ችሎቱ በያዘው መዝገብ ላይ አመልካች የነበሩት አቶ ዓለማየሁ ተሰማ ተጠሪ በሆነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት እናታቸው ሟች በለጡ መርሻ በአዲስ አበባ ከተማ የጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ዝርዝር ተመዝግበው አስፈላጊውን ክፍያ እየቆጠቡ ቆይተው የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣው ከመውጣቱ አስቀድሞ ጥቅምት 11 ቀን 2007 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ቢሆንም የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲ በ2008 ዓ.ም ለነዋሪዎቹ የ11ኛ ዙር የ20/80 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባለቤት ለማድረግ ባወጣው ዕጣ ሟች ወ/ሮ በለጡ መርሻ በምዝገባ መለያ ቁጥር BO 13Y0005202005 ቦሌ አራብሳ በተባለው የግንባታ ሳይት ውስጥ ብሎክ ቁጥር 041 የቤት ቁጥር 041/14 የሆነ ባለ ሦስት መኝታ የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ ወጥቶላቸዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት ከሟች እናታቸው የሚተላለፍላቸውን መብት ለመውረስ የወራሽነት ማስረጃ አውጥተው ለከተማ አስተዳደሩ ጥያቄ ሲያቀርቡ ለሕግ የሚቃረኑ መመሪያዎችን በመጥቀስ ሊፈፅሙላቸው አለመቻላቸውን ገልፀው የጋራ መኖሪያ ቤት ወራሽነት መብት ተከብሮ ለአመልካች ይተላለፍላቸው ዘንድ በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ መሆኑን ችሎቱ ጠቅሷል፡፡

ተጠሪም በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁ.35/2004 አንቀጽ 25 መሠረት ግንባታቸው የተጠናቀቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለተጠቃሚዎች የማስተላለፍ ሥልጣን ያለው ሲሆን ቤቶችን ለተጠቃሚዎች በማስተላለፍ ሂደት ሕግን መሠረት አድርጎ የሚሠራ ነው፡፡ በመሆኑም ቤት ፈላጊዎችን የመመዝገብ፣ የማጣራትና የቤት ርክክብ ሥርዓት እንዲሁም የማስተላለፍ ሂደቱ የሚመራው ለዚህ ተብሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 19/1997 እና መመሪያ ቁጥር 1/2008 መሠረት ነው፡፡ ስለሆነም መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44 የቤት ዕድለኛ በሞተ ጊዜ ዕድሜያቸው 18 ዓመት የሞላቸው የሟች ልጆች በሟች ስም የወጣውን ዕጣ አይወርሱም በሚል ይደነግጋል፡፡ ከዚህም አንጻር የአመልካች አቤቱታ ሕግን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ችሎቱ በብይኑ አስፍሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለትም የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠቃሹን መመሪያ አንቀጽ 44(ሠ) በመጥቀስ አመልካች የሟች እናታቸውን የጋራ የመኖሪያ ቤት ዕጣ ሊወርሱ አይችሉም ሲል ወስኖ በውሳኔው ላይ አመልካች ይግባኝ ቢያቀርቡም በይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት አለማግኘታቸውን እና በዚሁ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት መሆኑን ችሎቱ በብይኑ ጠቅሷል፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎቱም የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(1) እና 40(2) በመጥቀስ ከሕገ መንግሥቱ የንብረት ትርጓሜና የንብረት ማፍራት መብት አንፃር ጉዳዩን በመመልከት የአመልካች እናት ሟች በለጡ መርሻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ተርታ ተመዝግበው ገንዘባቸውን ሲቆጥቡ ቆይተው የሞቱ ቢሆንም ዕጣው ከሞት በኋላ የደረሳቸው መሆኑን በመጥቀስ ዕጣው እንደሟች ንብረት ተቆጥሮ በውርስ ሊተላለፍ እንደሚገባ አመልካች የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ከላይ የተጠቀሰውን መመሪያ መሠረት በማድረግ የኮንዶሚኒየም ቤት ዕጣ ከ18 ዓመት በላይ ለሆናቸው የሟች ልጆች እንደማይተላለፍ በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም 18 ዓመት የሞላቸው መሆኑን ሳይክዱ የዚህን መመሪያ ሕገ መንግሥታዊነት ጥያቄ ውስጥ በማስገባት መከራከራቸውን ችሎቱ ጠቅሷል፡፡

በመጨረሻም ችሎቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ያወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44 የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(1) የሚቃረን ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ላይ ተጣርቶ ትርጉም እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ እንዲላክ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመመሪያው ላይ የተጠቀሰው ይህ አንቀጽ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናል ወይስ አይቃረንም በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተመርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ተጠቃሹ መመሪያ ያካተተው ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የሟች ልጆችን የኮንደሚኒየም ዕጣ እንዳይተላለፍላቸው ያደረገውን ድንጋጌ ሕገ መንግሥታዊነቱን ለመፈተሽ 1ኛ የድንጋጌው ዝርዝር ይዘት ምንድን ነው? 2ኛ ኮንዶሚንየም ቤት ላይ የሚፈጠር የባለንብረትነት/ የባለቤትነት መብት በአፈጣጠሩ እና ከተፈጠረም በኋላ እንደማንኛውም ሌላ ንብረት ከባለቤቱ በቀር መንግሥት ሊያሳካው የሚሻው ፍላጎት የሌለበት መሆን አለመሆኑ፣ ፍላጎት ካለም ከየት እንደሚመነጭና ከግለሰቦች መብት ጋር እንዴት ተጣጥሞ ሊከበር እንደሚችል በመጨረሻም ሟች የሚጠበቅባቸውን ቁጠባ ሲቆጥቡ ቆይተው በመጨረሻ ዕጣው ሳይወጣ ሕይወታቸው ቢያልፍም ከህልፈታቸው በኋላ ዕጣው በወጣው የኮንዶሚንየም ቤት ላይ ለወራሾች ሊተላለፍ የሚችል መብት የላቸውም ወይስ አላቸው? የሚሉትን በመፈተሽ ለተያዘው ጉዳይ መቋጫ መስጠት ይገባል፡፡

ለእነዚህ ጉዳዮች መልስ ለመስጠት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበበትን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለተጠቃሚዎች እና ለልማት ተነሺዎች ለማስተላለፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44 መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፊደል ተራ 'ሀ' እስከ ፊደል ተራ 'ሰ' የተዘረዘሩ ሰባት ንዑስ አንቀጾች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡-

አንቀጽ 44 ዕጣ የማይወረስ ስለመሆኑ

ሀ) ማንኛውም ሰው በዕጣ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ ነው፤

ለ) የቤት ዕድለኛው ምዝገባ በባል ወይም በሚስት ስም ሲሆንና ባለዕድሉ በሞት ቢለይ ወይም ቢጠፋ በሕይወት ያለው ባል ወይም ሚስት በምዝገባ ቅፁ አማካኝነት ወይም ከፍርድ ቤት በሚያቀርበው ማስረጃ መሠረት ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው፣

ሐ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ “ሀ” ቢኖርም በምዝገባ ወቅት ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው የሟች ልጆች ወራሽነታቸውን በመደበኛ ፍርድ ቤት አረጋግጠው ሲመጡ ብቻ የዕጣው ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፤

መ) በፍርድ ቤት የወራሽነት መብት የተረጋገጠላቸው ግለሰቦች ተጠቃሚ የሚሆኑት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ድንጋጌዎች የሚያሟሉ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ በፊደል “ሐ” መሠረት ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ የሟች ልጅ (ልጆች) የዕጣውን ውርስ ተጠቃሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይኖሩበት የነበረውን የቀበሌ ቤት በምዝገባው ወቅት ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የሟች ልጆች ዕጣውን መውረስ ስለማይችሉ በመንግሥት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2007 መሠረት ቤቱን እንደያዙ ይቆያሉ፤

ረ) ባልና ሚስት በጋራ ምዝገባ አካሂደው ቤቱ ሳይደርስ በፍቺ ቢለያዩ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት ቁጠባው እንዲቀጥል ተደርጎ ቤቱ በዕጣ ሲደርስ በውሳኔው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ቅድመ ሁኔታውን አሟልተው ቤቱን ካልተረከቡ ዕጣው ይሰረዛል፤

ሰ) በፍርድ ቤት ክርክር ምክንያት መደበኛው የቤት ሽያጭ የውል ጊዜው ካለፈ በኋላ ዘግይተው ለሚመጡ ዕድለኞች ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ መሆኑን በቤት ማስተላለፍ ውል ጊዜ ገደብ ውስጥ ለኤጀንሲው አስቀድሞ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዳገኘ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀን ውስጥ በአካል ቀርበው ሊስተናገዱ ይችላል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

ከዚህ በላይ ተዘርዝረው ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው በፊደል ተራ ሀ፣ ሐ እና ሠ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ግልፅ ንባብ እንደሚያስረዳው የኮንዶሚንየም ዕጣ ከመውጣቱ በፊት የሞተ ሰው በምዝገባ ወቅት የሟች የ18 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆኑ ልጆች የዕጣው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መደረጋቸውን መረዳት የሚቻል ነው፡፡

ጉባዔው የከተማው አስተዳደር ቤቶች ኤጀንሲን አንድ ኃላፊና  አንድ ባለሙያ አስቀርቦ በመስማት ተጨማሪ ማብራሪያ ተቀብሏል፡፡ በዚህም የጋራ መኖሪያ ቤቶች በመንግሥት የሚሠሩና ቤት ለሌላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች የቀረበ ዕድል  ሲሆን ነዋሪዎቹ በምዝገባው ወቅት 18 ዓመትና ከዚያ በላይ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ዕጣን መውረስ እንደማይችሉ በመመሪያ መደንገግ ያስፈለገው በቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ወቅት መመዝገብና የእድሉ ተጠቃሚ መሆን ይችሉ ነበር ብለዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው የቤት ባለቤት የሚሆነው ዕጣ ስለወጣለት ብቻ ሳይሆን ከኤጀንሲው ጋር የሽያጭ ውል ሲገባ ስለሆነ ዕጣ ሀብት (ንብረት) ሊሆን አይችልም በማለት ገለፃ አድርገዋል፡፡

መንግሥት ለኮንዶሚንየም ቤቶች ወጪ በመመደብ ግንባታ ሲያካሂድ የገቢ አቅማቸው አነስተኛ የሆነ ዜጎችን የቤት ባለቤት ማድረግና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ማሳካት በዋናነት ታሣቢ ያደረገ በመሆኑ በዚህ ሀብት አፈጣጠር ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦና ፍላጎት ያለው መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ ቤቶች ላይ ዜጎች የባለቤትነት መብት በሚፈጥሩበት አግባብ ላይ ልዩ ልዩ ሕጎችን ማውጣቱ የሚጠበቅ በመሆኑ ለትርጉም የቀረበው መመሪያም የዚሁ አካል ነው፡፡ ዜጎች መንግሥት በገነባቸው ኮንዶሚንየም ቤቶች ላይ የባለቤትነት መብትን ለመፍጠር የሚችሉት ቤቶቹን በዕጣ ለማግኘት መንግሥት በሚያወጣቸው አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የሚጠበቅባቸውን ምዝገባ፣ አስፈላጊውን ቁጠባ እና መሰል ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው በመገኘት ነው፡፡

በሌላ በኩል ዜጎችም የኮንዶሚንየም ቤት ተጠቃሚ ለመሆን ቁጠባ የሚያካሂዱ በመሆኑ መጠነኛ በሆነ መልኩ በካፒታላቸው ሀብቱን ለራሳቸው ለመፍጠር ጥረት የሚያደርጉ መሆኑ ከግንዛቤ ሊወሰድ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም ዜጎች በኮንዶሚንየም ቤት ላይ የሚፈጥሩት ባለሀብትነት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(2) ስር ከተዘረዘሩት የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገዶች ከሆኑት በጉልበት፣ በመፍጠር ችሎታ ወይም በካፒታል የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገዶች ውስጥ ከሚቆጥቡት መጠነኛ ካፒታል በተጨማሪ የዚሁ አንቀጽ ተደማሪ የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገድ በሆነው የሕገ መንግሥቱ ክፍል በመታገዝ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ በምዕራፍ አስር ከሰፈሩት የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች ውስጥ በአንቀጽ 89 ስለ ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ሲደነግግ በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ (1)

“መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት” እና በንዑስ አንቀጽ (2) “መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት” ተብሎ መደንገጉ እንደዚሁም ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 90 ስለ ማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች ሲደነግግ በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት “የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁሕ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል” በሚል መደንገጉን ስንመለከት መንግሥት ያለበትን ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን የማረጋገጥ እና ለዜጎች አቅም በፈቀደ መልኩ የመኖሪያ ቤት የማቅረብ ግዴታውን ሲወጣ ለዜጎች አንዱ የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገድ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መነሻነት ዜጎች የሚፈጥሩት የግል ንብረት ባለቤትነት፣ መብቱን የፈጠሩትን ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማ ያከበረ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የሚፈጠር የንብረት ባለቤትነት የተጠቃሾቹን ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማ እስካሳካ ድረስ ባለቤትነቱን ለፈጠረው ዜጋ ሙሉ የንብረት መብት ሊፈጥር የሚገባ መሆኑ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ሙሉ የንብረት መብት ደግሞ ንብረት ማውረስን የሚጨምር መሆኑ አያከራክርም፡፡

በያዝነው ጉዳይ የንብረት ባለቤትነትን መብት ለመወሰን በመመሪያው የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት መብት የሚገኝበትን ወይም የሚጀምርበትን ሁኔታ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶችን የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 5(3) መሠረት በቤት ፈላጊነት የተመዘገበ ሰው ኤጀንሲው ባስቀመጣቸው መመዘኛ መሠረት አስፈላጊውን የማጣራትና የምርመራ ሥራ ከተሠራ በኋላ በቤት ፈላጊነት በጽሕፈት ቤቱ እንደሚመዘገብና ስሙ በማስታወቂያ ሰሌዳ ይፋ እንደሚደረግ፣ በዚህም የመኖሪያ ቤት የመግዛት መብት እንደሚያገኝ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህም የሚያሳየው የኮንዶሚኒየም ቤት ዕጣ መውጣት የሚያስፈልገው በሕግ አግባብ ተመዝግበው አነስተኛውን የገንዘብ መጠን ከቆጠቡ ነዋሪዎች መካከል በቅድሚያ ማን ያግኝ፣ በዕጣው ከተካተቱትስ የትኛውን ቤት ያግኝ (የት አካባቢ የተሠራውን ቤት፣ ብሎክ፣ ፎቅ፣… ወዘተ) እና መሰል ጉዳዮች ለመወሰን የሚረዳ እንጂ በሕጉ አግባብ

ሲቆጥብ የነበረ ነዋሪ ቤት ላያገኝ /ሊከለከል/ የሚችልበት መንገድ መኖሩን ለማሳየት ያለመ ሊሆን እንደማይችል መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ ቤት ፈላጊዎች ተገቢውን ቁጠባ መቆጠብ እስከቀጠሉ ድረስ ዕጣው እንደሚወጣላቸውና ቤቱን እንደሚያገኙ እርግጥ ነው፡፡

ሟችም በመጀመሪያ በቤት ፈላጊነት በሕጉ አግባብ ተመዝግበዋል፡፡ ኤጀንሲውም ባስቀመጣቸው መመዘኛዎች መሠረት አስፈላጊውን ማጣራት አድርጎና መዝግቦ የቤት ፈላጊ መታወቂያ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም ሟች በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ ከዕጣ ሊወጡ እንደማይችሉ እንዲያውም ሟች ቀድሞውኑ የጋራ መኖሪያ ቤት የመግዛት መብት እንዳገኙ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በኋላም ሟች  በሕጉ የሚጠበቅባቸውን ክፍያ ሲፈፅሙ ቆይተው ዕጣ ደርሷቸዋል፡፡ ከዕጣው መውጣት በኋላ የሚቀጥለው ግዴታ የሚጠበቅባቸውን ቅድመ ክፍያ በመክፈል ከኤጀንሲው ጋር የቤት ሽያጭ ውል መግባትና ቤቱን መግዛት ነበር፡፡ ስለሆነም ቤቱን የመግዛት ፍላጎትና አቅም እስካለ ድረስ ሟች የቤት ባለቤት ላይሆኑ የሚችሉበት አሠራር አለ ለማለት አያስችልም፡፡

በተጨማሪም ምንም እንኳን መንግሥት በራሱ ተነሳሽነት በጀት በመያዝና ገንዘብ ወጪ በማድረግ የጀመረው የቤት ልማት ፕሮግራም ቢሆንም ሟች ለቤት ብለው የሚያደርጉት ቁጠባ ሙሉ የቤት ባለቤት ለመሆን (በውርስ የማስተላለፍ መብትን ጨምሮ) በማሰብ ኢንቨስት እያደረጉት ያለው ገንዘብ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህም የተነሳ ሟች የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አሟልተው እስከተገኙ ድረስ ከላይ በተጠቀሱት አንቀጽ 89(1)(2) እና አንቀጽ 90(1) የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መሠረት የተፈጠረላቸው የንብረት መብት የድንጋጌዎቹን መሠረታዊ ዓላማ እስካሳካ ድረስ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ የተከበረ ሙሉ የንብረት መብት ተከብሮ የሟች ወራሾችም ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባ ነው፡፡ ወራሾች ሟች ያላቸውን የጋራ መኖሪያ ቤት የመግዛት መብት የተሟላ ለማድረግ ቀሪውን ግዴታ ማለትም ከዕጣው በኋላ የሚጠበቅባቸውን የቅድመ ክፍያ እስከፈጸሙ ድረስ የመብቱ ሙሉ ተጠቃሚ ከመሆንና ቤቱን ከመረከብ የሚከለክላቸው መሆን የለበትም፡፡ በተለይም ሟች ዕጣው ሳይደርሳቸው በመሞትና ዕጣው ከደረሰው በኋላ በመሞት መካከል የሚኖረው ልዩነትና የተለየ ውጤት በሌለበት ሁኔታ ከ18 ዓመት በታች እና በላይ የሚል ልዩነት መፍጠሩ ምክንያታዊ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

በመጨረሻም ከላይ ለማየት እንደተቻለው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ዓላማ መንግሥት ቤት የሌላቸውን የከተማዋ ነዋሪዎች ቤት እንዲኖራቸው ለማድረግ ያቀደ ቢሆንም

መመሪያው በኮንዶሚኒየም ቤት ምዝገባ ወቅት ያልተመዘገቡ የቤት ዕጣ መውረስ አይችሉም በሚል የያዘው አቋም አግባብነት የሌለው ነው፤ በወቅቱ በቤት ፈላጊነት ባይመዘገቡም ቤት የሌላቸው ግለሰቦች በውርስ መልክ ሊያገኙ ከሚችሉት የቤት ባለቤትንት መብት መነፈጋቸው በሕገ መንግሥቱ የተከበረላቸውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ በተጨማሪም መመሪያው ለሟች አካለመጠን ላልደረሱ ልጆች ክልከላ አለማድረጉ የሚደገፍ ቢሆንም በእድሜ ልዩነት በመፍጠር ሟች ከልጆቻቸው መሀከል አካለ መጠን ያልደረሱ ባይኖሩም አካለ መጠን የደረሰ ወራሽ የቤት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚፈቅድ አለመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) እና (2) የተደነገገውን የዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ የሟች ወራሾች መካከል ልዩነት መፍጠር በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸውን በሕግ እኩል ጥበቃ የማግኘት መብት የሚሸራርፍ ነው፡፡

ስለዚህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንደሚኒየም ቤቶች ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44(ሐ) እና (ሠ) የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋቸዋል በማለት ጉባዔው በአብላጫ ድምፅ በአንድ የልዩነት ሀሳብ ጉዳዩ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኤፌዲሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት እንዲተላለፍ የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሀሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባዔውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት ወራሾች ሟች ያላቸውን የጋራ መኖሪያ ቤት የመግዛት መብት የተሟላ ለማድረግ ቀሪውን ግዴታ ማለትም ከዕጣው በኋላ የሚጠበቅባቸውን የቅድመ ክፍያ እስከፈፀሙ ድረስ የመብቱ ሙሉ ተጠቃሚ ከመሆንና ቤቱን ከመረከብ የሚከለክላቸው መሆን የለበትም፡፡ በተለይም ሟች ዕጣው ሳይደርሳቸው በመሞትና ዕጣው ከደረሳቸው በኋላ በመሞት መካከል የሚኖረው ልዩነትና የተለየ ውጤት በሌለበት ሁኔታ ከ18 ዓመት በታች እና በላይ የሚል ልዩነት መፍጠሩ ምክንያታዊ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንዶሚኒየም ቤቶች ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44(ሐ) እና (ሠ) ድንጋጌ የኢ.ፌዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1)እና(2) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የኢ.ፌዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 3ኛ መደበኛ ጉባዔ

ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

3.3 ይግባኝ ባይ፦ ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ፣ ተጠሪ፦ የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት

የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በይግባኝ ባይ የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ይግባኝ ባይ ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ.ም ለምክር ቤቱ የጻፉት የይግባኝ ቅሬታ ጠቅለል ባለመልኩ ሲቀመጥ ለረጅም ዓመታት ከኢትዮጵያ ውጭ ያፈራሁትን ሀብት ወደ ሃገሬ ይዤ ከገባሁ በኋላ ለአካባቢው ሕብረተሰብም ሆነ ለመንግሥት እገዛ ያደርጋል በሚል እሳቤ በደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልላዊ መንግሥት፣ ካፋ ዞን፣ ቦንጋ ከተማ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ ተረክቤ ከ70% በላይ ከገነባሁ በኋላ የከተማው ማዘጋጃ ቤት የግንባታው ቦታ ላይ የኮንቴይነር ሱቆች በመደርደሩ የተነሳ የግንባታ እቃዎች ለማስገባት ባለመቻሌ ግንባታው እንዲቆም ተደርጓል፡፡

በዚሁ መነሻነት ማዘጋጃ ቤቱ ክስ አቅርቦ የተለያዩ ፍ/ቤቶች የተለያየ ውሳኔ የሰጡ ቢሆንም የፌዴራሉ ጠ/ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቀሪው ግንባታ መጠናቀቅ ያለበትን ጊዜ ወስኖ እንዲያሳውቅና ለግንባታ ሥራው እንቅፋት የሆኑትን የደረደራቸውን የኮንቴነር ሱቆች በየደረጃው በመለየት እንዲያፈርስ፣ በዚሁ ሁኔታ በሚሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ካላጠናቀቁ ማዘጋጃ ቤቱ ግንባታውን ባለበት ሁኔታ የመረከብ መብት እንዳለው ወስኗል፡፡

ይህ ቢሆንም ማዘጋጃ ቤቱ ግዴታውን ሳይወጣና ከ70% በላይ ግንባታ የተፈጸመበት በመሆኑ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 /7/ እና ስለኢንቨስትመንት ዋስትና የተቀመጠውን አዋጅ ቁጥር 280/94 አንቀጽ 21ን በመተላለፍ ለንብረቱ ካሣ እንዲከፍል ሳይደረግ መወሰኑ ኢሕገ መንግሥታዊ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አቤቱታ ባቀርብም ውድቅ በመደረጉ ያለአግባብ የተደረደሩት የኮንቴይነር ሱቆች ተነስተው ግንባታውን ተረክቤ እንዳጠናቅቅ ወይም ተገቢው ካሳ የማግኘት መብቴ እንዲጠበቅልኝ የሚል ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ክርክሩ የተጀመረው በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከሳሽ የነበረ ሲሆን የአሁኑ ይግባኝ ባይ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ማዘጋጃ ቤቱም ባቀረበው ክስ ይግባኝ ባይ ዘመናዊ ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ ጠይቀው 1931 ካ.ሜ ተሰጥቷቸው ግንባታውን ስላቋረጡ ውሉ ተሰርዞ ግንባታውን በራሳቸዉ ወጪ አፍርሰው ቦታውን እንዲያስረክቡ የቦታና የቤት ግብርም እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው ጠይቋል፡፡

የአሁኑ ይግባኝ ባይ ለክሱ በሰጡት መልስ ግንባታው የተቋረጠው በፕሮጀክቱ ሳይት ላይ ከሣሽ የኮንቴይነር ሱቆች በማቆሙና ይህም የግንባታ እቃዎች በመኪና ተጭነው እንዳይገቡና እንዳይራገፉ እንቅፋት በመሆናቸውና የግንባታው እቃ ዋጋም በመናሩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ የግንባታ እቃዎች ወደ ግቢው በመኪና ተጭኖ እንዳይገባ ያገደው ነገር የለም፡፡ ከዲዛይኑ አኳያ ከግማሽ በላይ የተከናወነ በመሆኑ ውሉ ተሠርዞ ለጅምር ግንባታው ግምቱን ከሣሽ ለተከሣሽ ከፍሎ ግንባታውን ከነይዞታው ይረከብ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ግራ ቀኙ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር ተመልክቶ ግንባታው የተቋረጠው ማዘጋጃ ቤቱ ባቆማቸው የኮንቴነር ሱቆች ችግር ስለመሆኑ እስከ ቦታው ድረስ ሄዶ ተመልክቶ እንዳረጋገጠ ገልጾ እና የግንባታ እቃ ዋጋ ጭማሪም ለግንባታ መቆሙ አስተዋጽኦ ስላለው ውሉ ሊሰረዝ ይገባል ቢባል እንኳን ከ55% በላይ ግንባታ ስለተከናወነ ወደ ነበረበት ለመመለስ አስቸጋሪ ስለሆነ ውሉ ሊሠረዝ አይገባም፡፡

ስለሆነም ማዘጋጃ ቤቱ ለግንባታው እንቅፋት የሆኑትን ኮንቴነሮች እንዲያነሳ፣ ግንባታውም እንዲቀጥል ሲል ወስኗል፡፡ ማዘጋጃ ቤቱ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል ይግባኝ ባይ ግንባታውን በወቅቱ ላለማጠናቀቅ በምክንያትነት ያቀረቡትን በሳይቱ መግቢያ የኮንቴነር ሱቆች ስላልተነሱ ነው የሚል መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ በመመርመር ይግባኝ ባይ ቦታውን ከተረከቡበት ከ1993 ዓ.ም እስከ 1995 ዓ.ም ድረስ ያለችግር ግንባታውን ሲያካሂዱ እንደነበርና በግንባታው እቃዎች እጥረት ምክንያት ግንባታውን አቋርጠው ቆይተው የኮንቴነር ሱቆች ተደረደሩ የሚል ምክንያት ያነሱት በ1997 ዓ.ም መጨረሻና በ1998 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ እንደሆነ በማረጋገጥ ቀሪ ግንባታውን ሊያጠናቅቁ የሚገባበት ጊዜ በተመለከተ ከክልሉ ደንብ ቁጥር 41/1997 በተመለከተው መሠረት ማዘጋጃ ቤት ወስኖ እንዲያሳውቃቸው፡፡

ማዘጋጃ ቤቱ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ማጠናቀቅ ካልቻሉ ውሉ ተሰርዞ ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውንና ግንባታውን ባለበት ሁኔታ የመረከብ መብቱን ጠብቆ ለግንባታ ሥራው እንቅፋት የሆኑት ኮንቴነር ሱቆች ማዘጋጃ ቤቱ በየደረጃው በመለየት እንዲያፈርስ በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ባዩ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ የሕግ ስሕተት ተሠርቷል በማለት ለሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የነበረ ቢሆንም የሰበር ችሎቱም የተፈጸመ የሕግ ስሕተት የለም በማለት ውሳኔውን አጽንቶታል፡፡

ከዚህ በኋላ ይግባኝ ባዩ መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ አቅርበው የነበረ ሲሆን በአቤቱታቸው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ስር የተመለከተውን በመጣስ የተሳሳተ ትርጓሜ የሰጡ በመሆናቸው ጉባዔው የፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ እንዲያርመው እና ግንባታውን ተረክቤ እንዳጠናቅቅ ወይም ተገቢም ካሳ የማግኘት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ በአብላጫ ድምጽ አመልካች በግንባታው ላይ ያላቸውን መብት ከማዘጋጃ ቤቱ ጋር በገቡት ውል ምክንያት የተጎናፀፉት በሁኔታ ላይ የተመሠረተ መብት ነው፣ ይህም ሁኔታው ቀድሞውኑ አመልካች በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ለማጠናቀቅ የማይችሉ ቢሆኑ ግን ውሉ ሲፈርስ በገደብ የተሠጠ መብት ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ መሠረት የመንግሥት አካል የዜጎችን ንብረት መውረስ የሚችለው በቅድሚያ ከግለሰብ ጥቅም ላቅ ላለ የማኅበረሰብ ጥቅም አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ግን ማዘጋጃ ቤቱ ከግማሽ ደርሶ ያልተጠናቀቀውን ግንባታ እንዲረከብ ሆነ እንጂ ከፍ ላለ የሕዝብ ጥቅም ሲባል ከባለሀብቱ ለመውረስ የሚያስገድድ ሁኔታ አልተከሰተም፡፡ ማዘጋጃ ቤቱ የባለሀብቱን ንብረት ለሕዝብ ጥቅም ለመውረስ አልወሰነም፡፡ ባለሀብቱ እንደውላቸው ግንባታውን ቢያጠናቅቁ ኖሮ ንብረቱ ከባለሀብቱ እጅ የሚወጣበት ሁኔታ አይኖርም ነበር፡፡ ማዘጋጃ ቤቱ ግንባታውን የተረከበው አመልካች እንደ ውሉ ባለመፈጸማቸው ምክንያት ግንባታው ከሚፈርስ ማዘጋጃ ቤቱ ቢረከበው ይሻላል ከሚል ሚዛን ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቹ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት ተመጣጣኝ የካሣ ክፍያ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

የጉባዔው አነስተኛው ድምጽም በበኩሉ በአመልካች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40/7/ መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው የሚለውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚጥስና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴንም የሚገታ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የልዩነት ሃሳቡን አስቀምጧል፡፡

ይግባኝ ባዩ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሰጠው ውሳኔ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለምክር ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን ምክር ቤቱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የግንባታውን ሁኔታ ለመረዳት እንዲቻል ሁለት ቡድኖች በተለያየ ጊዜ በቦታው በመገኘት ምልከታ አድርገው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በምልከታቸው ይግባኝ ባዩ የግንባታ ሥራ ጀምረውበት የነበረው ሕንፃ የከፋ ልማት ማኅበር ተረክቦት እየተጠቀመበት እንደሆነ፣ ማኅበሩ ሕንፃውን ሠርቶ ግማሹን ለተለያዩ ድርጅቶችና ባንኮች ያከራየ መሆኑን ቡድኑ ተመልክቷል፡፡ ቀሪውን ግንባታ የልማት ማኅበሩ እያከናወነ እንደሚገኝ አረጋግጧል፡፡ በወቅቱ ግንባታው ሲቋረጥ የሕንፃ ሥራው የነበረበት ደረጃ በተመለከተ ፕላኑ G+2 እንደነበረ፣ በወቅቱ ይግባኝ ባዩ መሠረት እና ኮለን እንዳቆሙ፣ የአንዱ ወገን ስላብ እንደተሠራና ሐምሌ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የርክክብ ሰነድ ቦታውንና ግንባታውን ማዘጋጃ ቤቱ ያለክፍያ ለከፋ ልማት ማኅበር እንዳስረከበ ከቡድኑ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ ምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን ከስር ጀምሮ ማለትም የይግባኝ ባይን አቤቱታ፣ የአጣሪ ጉባዔውን ውሳኔ፣ በተለያዩ ወቅቶች በተደረገው ማጣራት የተገኙ ጉዳዮችን፣ የሕገ መንግሥቱንና አግባብ ያላቸውን ሕጎች ድንጋጌዎች በማገናዘብ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በአግባቡ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የይግባኝ ባዩ ጥያቄዎች በዋነኝነት ሁለት ሲሆኑ እነዚህም ግንባታውን ተረክቤ እንድሠራ ይደረግ ወይም ተገቢውን ካሳ የማግኘት መብቴ ይጠበቅልኝ የሚሉ ናቸው፡፡

ምክር ቤቱ ከጉዳዩ አመጣጥ፣ በፍርድ ቤቶች ከተሰጡት ውሳኔዎችና ከይግባኝ ባይ አቤቱታ በመነሳት ሁለት ጉዳዮች ተከፋፍለው መታየት እንዳለባቸው ተገንዝቧል፡፡ አንደኛው የውሉ ይሰረዝ እና ለዚህ ጉዳይ በፍርድ ቤቶች የተሰጡት ምክንያቶች ከዚሁ ጋር ተያይዞ ይግባኝ ባዩ

ቦታውንና ግንባታውን ተረክቤ እንዳጠናቅቅ በሚል ያቀረቡት ጥያቄ ሲሆን ሁለተኛዉ ይግባኝ ባዩ በአማራጭ ተገቢውን ካሳ የማግኘት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ነው፡፡

አንደኛውን ጉዳይ በተመለከተ በይግባኝ ባይና በማዘጋጃ ቤቱ መካከል የነበረው ውል በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሠረት ይግባኝ ባዩ ማዘጋጃ ቤቱ ወስኖ በሰጣቸው የጊዜ ገደብ ግንባታውን ባለማጠናቀቃቸው ውሉ ተሰርዞ ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውን ከነግንባታው ተረክቧል፡፡ ለውሉ መሰረዝ ምክንያት ለሆነው የግንባታ መጓተት በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ትንታኔዎች የተሰጡ ሲሆን ውሉ የተሰረዘው በአግባቡ ነው አይደለም? ለውሉ መሰረዝ እና ለግንባታው በጊዜ ያለመጠናቀቅ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የሁለቱ ወገኖች ድርሻ ምን ነበር? ቀሪ የግንባታ ጊዜ ማዘጋጃ ቤቱ ወስኖ እንዲሰጥ መደረጉ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚሉት ሀሳቦች ከላይ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የውሳኔ ሐተታ የተረጋገጡ፣ ምላሽ ያገኙና ውሳኔ የተሰጠባቸው የሕግ እና የፍሬ ነገር ክርክሮች በመሆናቸው ምክር ቤቱ የሚመለከታቸው አይሆንም፡፡ ማዘጋጃ ቤቱም መሬቱን ሲረከብ ግንባታውንም አብሮ የተረከበበትን አግባብነትንም በተመለከተ ይህ ምክር ቤት የሚያየው ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህም በመነሳት ይግባኝ ባዩ ግንባታውን ተረክቤ እንድቀጥል በሚል ያቀረቡት ጥያቄ ይህን ምክር ቤት የሚመለከት ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተነሳው እና በይግባኝ ባዩም የተጠየቀው ተገቢው ካሳ የማግኘት ጥያቄን በተመለከተ ጥያቄው ሕገ መንግሥታዊ በመሆኑ በምክር ቤቱ በኩል የታየው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለምንም ተመጣጣኝ ክፍያ ማዘጋጃ ቤቱ መሬቱን ከእነ ግንባታው እንዲረከብ ውሳኔ ሲሰጥ በመሬቱ ላይ አመልካች የገነቡት ግንባታ ጉዳይ እንዴት ይታያል የሚለው ነው፡፡

በምክር ቤቱ በኩል ይህ ጥያቄ እንደታየው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ በግልጽ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያን የመጠየቅ መብትን ያካትታል በሚል ተደንግጎ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ እንደሚወሰን አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ለንብረት ካሳ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 455/1997 ዓ.ም አንቀጽ 7 የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ

የሚደረግ ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ መሻሻል ካሳ እንደሚከፈለው ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ ይግባኝ ባይ የመሬት ተጠቃሚነታቸው ተቋርጧል፡፡ ሆኖም በመሬቱ ላይ ግንባታ ማከናወናቸው የግንባታውን ደረጃ ጭምር በራሱ በማዘጋጃ ቤቱ የታመነ በመሆኑ ማዘጋጃ ቤቱ ያለምንም ክፍያ ንብረቱን እንዲረከብ ተብሎ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የቦታውንና ግንባታውን ርክክብ የተመለከተ ውሳኔ ሳይሆን ተመጣጣኝ ክፍያን በሚመለከት ምንም ነገር ያለማለቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ የተደነገገውን መብት የሚጻረር በመሆኑ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

በመሆኑም ይግባኝ ባዩ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው በሚለው ድንጋጌ መሠረት በመሬቱ ላይ የተገነቡትን ሀብት ግምት የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት ምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት**

**5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ**

**ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም**

3.4 አመልካች:- አቶ ክፍለ ጽዮን በርሄ ገ/ማርያም፣ ተጠሪዎች:- እነ አቶ ተሾመ አባመጋል (2 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈና ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ክርክሩ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማኅበር የተገኘ ቤት በውክልና ተሸጧል የተባለበት ውል የጥቅም ግጭት አለበት የሚል ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል መባልን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 07 ፈለገ ሰላም የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማኅበር ውስጥ በሚገኝ ቤት ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሚያዝያ 17 ቀን 1989 ዓ.ም ተፈፀመ የተባለው ውል በሌለሁበትና ፈቃዴን ሳልሰጥ ስለተደረገ፣ የሽያጭ ውል መኖሩን ያወቅሁት በ2005 ዓ.ም በመሆኑ ይፍረስልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግላቸው መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ውል መኖሩን ያወቅኩት በ2005 ዓ.ም ነው የሚለው ክርክራቸው በማስረጃ ስላልተደገፈ ተቀባይነት አላገኘም በማለት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሠረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ አቤቱታቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 244(2) (ሠ) ጠቅሶ ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

ብይኑ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክር ተደርጎበት ሲፀና፣ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር አያስቀርብም ተብሏል፡፡

ጉባዔውም የአመልካችን አቤቱታ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 እና 40 አንጻር መርምሮ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እና የምክር ቤቱን ባለሙያዎች አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍርድ ቤት ውሳኔ የሕገ መንግሥት ጥሰት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች ቅሬታ ከተጠሪዎች ጋር የተደረገውን ክርክር የተመለከተው ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን የሕገ መንግሥት ጥሰት ስለተፈፀመበት ትርጉም እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ከአመልካች አቤቱታና ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ መግቢያ ላይ መረዳት የተቻለው አመልካች የውክልና ሥልጣን በቀን 08/03/87 ዓ.ም ለ1ኛ ተጠሪ ሰጥቼ ንብረቱን እንዲያስተዳድርልኝ ወከልኩት እንጂ በቀጥታ ለ2ኛ ተጠሪ ያደረግሁት ሽያጭ የለም፡፡ ተጠሪዎች ባልና ሚስት በመሆናቸው ውክልናውን ሰበብ በማድረግ ቤቱን ከመያዛቸው በቀር አመልካች ውክልና እንደሰጠሁ ወደ ኤርትራ በመሄዴ እና የኢትዮ-ኤርትራ ግጭት በመፈጠሩ ወደ ኢትዮጵያ ባለመመለሴ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ በውክልና ሥልጣኑ እንደ መልካም አባት ማስተዳደር ሲገባው በሕገ ወጥ ተግባር ለባለቤቱ በመሸጥና እንደእማኝ በመፈረም ያለአግባብ ለመበልጸግና የንብረት ባለቤት ለመሆን ያደረገው ጥረት ነው፡፡

በሌላ በኩል የሕብረት ሥራ ማኅበሩን በመክሰስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 130494 በቀረበ ክስ ዝውውር ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የካቲት 25 ቀን 2005 ዓ.ም ማወቄ፣ 2ኛ ተጠሪ ባለቤቷን መወከሌንና ኤርትራ መሄዴን እያወቀች አሰጥታብኝ የነበረው የመጥፋት ውሳኔ መሻሩን፣ የሽያጭ ውሉ ሀሰተኛ ሰነድ እንጂ በአመልካች የተፈፀመ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ የፎረንሲክ ምርመራ ቢታዘዝም በዳኛ መቀየር ምክንያት ውጤቱ ሳይታወቅ ሂደቱ ተቋርጦ መወሰኑ፣ ከሕብረት ሥራ ማኅበሩ ማስረጃ ሳይጠየቅ እና ምስክሮች ሳይደመጡ በቀረበ መቃወሚያ ብቻ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት እንደሌለው እና ክሱ በይርጋ እንደማይታገድ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 43600 በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ክርክር ይርጋ የለውም ሲል ከሰጠው ውሳኔ ጋር ስለሚቃረን በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት የሚል ዝርዝር ቅሬታ አቅርበዋል፡፡

በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመፋለም ክስ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43600 አስገዳጅ ውሳኔ መስጠቱ ይታወቃል፡፡ ይህ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ ፍ/ቤቱ የአመልካችን ሁኔታና ማስረጃ ሳይመረምር በጠቅላላ ሕግ የተደነገገውን የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1845ን በመጥቀስ በይርጋ በብይን መዝጋቱ ተገቢነት የለውም፡፡

ተወካይ በተወከለበት ጉዳይ ላይ የወካዩን ጥቅምና ፍላጎት ማስከበር ያለበት መሆኑን የእንደራሴነት ሕግ ይደነግጋል፡፡ በዚህም ላይ ተወካይ የጥቅም ግጭት የሚያስነሱ ሁኔታዎችን ማስወገድ ያለበት መሆኑን የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 32241 ቅጽ 5 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ተወካይ ሲሆኑ፤ ለ2ኛ ተጠሪ ደግሞ ባል በመሆናቸው ተወካይ ከቤተሰቡ ጋር የሚያደርጋቸው ውሎች እና ሌሎች ተግባሮች የወካዩን ጥቅም ስለሚጎዳና የጥቅም ግጭት ስለሚኖርበት ይህንንም ለወካዩ ማሳወቅ ሲኖርበት ባለማሳወቁ ከቤተሰቡ ጋር የሚያደርገው ተግባር ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህንንም ፍ/ቤቱ ማጣራት ሲገባው ማለፉ ፍትሐዊነትን ያዛባል፡፡

አመልካች ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሄዱት ሁለቱ ሀገሮች መልካም ግንኙነት እያላቸው እንጂ በጦርነቱ ወቅት ወይም ከጦርነቱ በኋላ አይደለም፡፡

በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 /2/ መሠረት ማንኛውም ሰው በጉልበቱ፣ በዕውቀቱ ወይም በገንዘቡ የግል ንብረት የማፍራት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ንብረት ያፈራ ሰው ደግሞ በሕግ አግባብ በንብረቱ የመጠቀም እና የማስተላለፍ መብት እንዳለው በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ አንድ ሰው በሕግ አግባብ ያፈራው የግል ንብረት መብቱን ሊያጣ የሚችለው ሕግ በዘረጋው ሥርዓት ብቻ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ በፍርድ ቤት ደረጃ በሚደረገው ክርክር ደግሞ አንድ ሰው የንብረት መብቱን ሊያጣ የሚችለው በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 ሥር የተመለከተው ፍትሕ የማግኘት መብቱን ባስከበረ ሁኔታና በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት መከላከያ እና ተገቢ ክርክር በማቅረብ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ሕጋዊ ሂደት ውጪ ግን አንድ ሰው የንብረት መብቱን ያጣ እንደሆነ በሕገ መንግሥቱም ሆነ በዝርዝር ሕጎች የተመለከተውን የሚጥስና ሕግን ያልተከተለ ድርጊት በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

ይህ የፍርድ ቤት ብይን የአመልካችን አቤቱታ በፍሬ ነገር ላይ በጥልቀት ሳይመረምርና ሳያጣራ ጠቅላላ የይርጋ ሕግን መሠረት በማድረግ የተሰጠ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተሰጠ

ፍርድ የአመልካችን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገውን የመሰማትና ትክክለኛ ውሳኔ የማግኘት እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተደነገገውን የንብረት መብት በመቃረን የተወሰነ ነው፡፡

በመሆኑም የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ.86/12

3.5 አመልካች፡- ቄስ ወ/ጊዮርጊስ ኪዳኔ፣ ተጠሪዎች፡- እነ አቶ መረሳ ወ/ማርያም(2 ሰዎች) የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2011 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ የይዞታ ይገባኛል ክርክር ሲሆን ሲጀመር አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ከሳሽ ሆነው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱም ይዘት በትግራይ ክልል በታች ማይጨው በማይበራዝዬ ቀበሌ አዋሳኞቹ በክሱ በተጠቀሱት የኢንቨስትመንት ቦታ ላይ የሚገኝ ስድስት የእህል ወፍጮ ከነሙሉ መሣሪያው በብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) ለአመልካች ሸጠናል፡፡ ሆኖም አመልካች ወፍጮውን ከቦታው እንዲያነሱልን ብንጠይቅም እንዲሁም አስፈላጊውን ማስጠንቀቂያ ብንሰጥም ሊለቁልን ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ በመሆኑም በኢንቨስትመንት ቦታችን ላይ ምንም መብት ስለሌላቸው ወፍጮውን አንስተው ቦታውን እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ይህንኑ ክስ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ማቅረባቸውን፣ ጉዳዩን ዓይቶ የይዞታ ማረጋገጫ ለእኔ በመሰጠቱ ክሱ በተመሠረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ስለሌላቸው የመክሰስ መብት የላቸውም ብለዋል፡፡ በፍሬ ነገር መልሳቸው ተጠሪዎች ወፍጮውን ከእነ ይዞታው በመሸጣቸው ይዞታው ለአመልካች ይሰጥ በማለት በቀበሌ መስተዳድር በሦስት ምስክር ፊት በመፈረማቸው የመጠቀም መብት የይዞታ ማረጋገጫ በ40×30 ሜ መሬት ላይ በቀን 12/1/2007 ዓ.ም ማግኘታቸውን፣ ማረጋገጫው እንዳልተሰረዘ እና ተጠሪዎች በኢንቨስትመንት ያገኙት መሬቱን ከአምስት ዓመት በኋላ ማሳደስ ቢኖርባቸውም የታደሰ የኢንቨስትመንት ውል አለመኖሩ ይዞታውን ለእኔ እንዳስተላለፉት ያሳያል በማለት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገሩ ተጠሪዎች የሸጡት ወፍጮ ብቻ ነው ወይስ መሬቱንና ሌላ ንብረቶችንም ጭምር ነው? የሚል ጭብጥ በመያዝ በግራ ቀኙ የቀረቡትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ የሰው ማስረጃዎች ሽያጩ ወፍጮን፣ 4 ክፍል ቤት ከዙሪያ መለስ የግንብ አጥር ጋር ማካተቱን እና ውሉ በውልና ማስረጃ እንደጸደቀ በማስረዳታቸው፣ የጽሑፍ ማስረጃዎች፣ ተጠሪዎች ቦታውን ለኢንቨስትመንት እንደተረከቡት እና ወፍጮ ተክለው ሲሠሩበት ቆይተው ወፍጮውን እና ቤት እና ግቢውን በብር 270.000.00 (ሁለት መቶ ሰባ ሺህ) እንደሸጡት ያስረዳል፡፡ በመሆኑም ሽያጩ ይዞታውን በማጠቃለሉ አመልካች ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም «አያስቀርብም» ተብሎ መዝገቡ በትዕዛዝ ተዘግቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ሽያጩ የኢንቨስትመንት የኪራይ መሬቱን ያጠቃልላል? አያጠቃልልም? የሚለውን ከትግራይ ክልል የኢንቨስትመንት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ 239/2006 እና ከግራ ቀኙ ውል አንጻር መርምሮታል፡፡

በምርመራው ውሉ በግልጽ የወፍጮ ቋት ሽያጭ የተፈጸመ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 239/2006 መሠረት የእርሻ ኢንቨስትመንት የወፍጮ ሥራ ኢንቨስትመንትን የሚያካትት ነው፡፡ በአዋጁ ኢንቨስትመንት መብት ከሚተላለፍበት ሥርዓት ውጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ መሆኑን፣ በዚህም አግባብ የመሬት አስተዳደር ይህንኑ ለተጠሪዎች በመግለጹ በኪራይ ለኢንቨስትመንት ሥራ የተገኘን መሬት መሸጥ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የኪራይ መሬት ሽያጩ በውሉ ያልተመላከተ እና በአዋጁ አንቀጽ 22/5/ እና 26/4/ መሠረት በኪራይ ለኢንቨስትመንት ሥራ የተገኘ መሬት መሸጥ የተከለከለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ ሽያጩ የኢንቨስትመንት መሬቱን አያካትትም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ብሎ ሳይጠየቅ ቀሪ ይሁን ማለቱ

የክርክር ነጥብ ያልሆነ ጉዳይ አንስቶ ለመወሰን ሥልጣን ሳይኖረው መወሰኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25፣ 80(3) የተደነገገውን መብቴን ጥሷል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእጄ እያለና ካርታው ሳይመክን የእርሻ ኢንቨስትመንት መብት ከሥርዓት ውጪ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40/6/ እና /7/ እንዲሁም 79(3) መሠረት ንብረት የማፍራት እና የመጠቀም መብቴን የጣሰ ነው በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ጉባዔውም የአመልካችን አቤቱታ ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ እና ተጣሰብኝ ካሉት ሕገ መንግሥታዊ መብት አንጻር መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪዎች ቤቱን ለኢንቨስትመንት ብለው ከክልሉ መንግሥት ተረክበው ሲሠሩ ቆይተው ወፍጪቸውን ለአመልካች መሸጣቸውን ነው፡፡

በዚህ አግባብ በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች ሽያጩ የኢንቨስትመንት መሬቱን ያጠቃልላል ብለው ቢወስኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ሕግ አዋጅ ቁጥር 239/2006 ለኢንቨስትመንት የተሰጠን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ስለተከለከለ እና ውሉም የእህል ወፍጮ ሽያጭ ስለሚል ሽያጩ የወፍጮ ብቻ ነው በማለት መወሰኑን ነው፡፡ አመልካች ይህ ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉትን መብቶቼን ይጥሳል በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ሰበር ሰሚው አዋጁን እና ውሉን የተረጎመበትን መንገድ ሕገ መንግሥታዊነት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ አግባብ በፍርድ ቤት የነበረው ክርክር በግራ ቀኙ መካከል በቀን 18/11/2005 ዓ.ም በብር 20,000 (ሃያ ሺህ) የእህል ወፍጮ ሽያጭ ውል መደረጉን፣ በቀን 22/11/2005 ዓ.ም ግራ ቀኙ ባደረጉት የስምምነት ውል 40 ሜትር በ30 ሜትር የሆነውን የእህል ወፍጮ ቦታ፣ አራት ክፍል ቤት፣ መጋዘን፣ ግንብ አጥርና ብረት መዝጊያ ያለው ቦታ በብር 270,000.00 (ሁለት መቶ ሰባ ሺህ ብር) በመሸጥ ውሉን እንዳሻሻሉት ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ይህንን ተከትሎ ሐምሌ 28 ቀን 2005 ዓ.ም የወረዳ ታህታይ ማይጨው አስተዳደር ኮሚቴ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን 40 × 30 ሜትር የሆነ ቦታ የወፍጮ ድርጅት ስም ለአመልካች እንዲዛወርላቸው የድጋፍ ማስረጃ የጻፈላቸው ሲሆን መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ.ም የታህታይ ማይጨው ወረዳ አመልካች ወፍጮውን በውል እና ማስረጃ እንደገዙት በመጥቀስ እና የቀበሌው መሬት አስተዳደር ወፍጮ የነበረበትን 40×30 ሜትር የሆነው መሬት

ለአመልካች ሊዛወርላቸው ይገባል በማለት በመወሰኑ መሬቱን ለአመልካች መስጠታቸውን አረጋግጠው ጽፈውላቸዋል፡፡ ይህን ተከትሎ በአዋጁ አንቀጽ 17 /1/ መሠረት በክልሉ የገጠር መሬትን የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የትግራይ ክልል የአካባቢ ስነ ጥበቃ ኤጀንሲ የገጠር መሬት አስተዳደር በ04/04/2009 ዓ.ም የገጠር መሬት የይዞታ ካርታ ሰጥቷቸዋል፡፡ በቦታው ላይ ካርታ እንጂ የኢንቨስትመንት ፍቃድ አለመሰጠቱ ከኢንቨስትመንት ሕጉ አንጻር ሲታይ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12 የኢንቨስትመንት ፍቃድ ስለሚያስፈልጋቸው ባለሃብቶች ሲደነግግ በእርሻ ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ፍቃድ ከሚያስፈልጋቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ውስጥ አያካትታቸውም፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳን የእህል ወፍጮ ሽያጩ የተደረገው በግራ ቀኙ በተደረገው ውል ቢሆንም መሬቱን ለአመልካች ያስተላለፈው የወፍጮ ሽያጩን እና የተሻሻለውን ውል መሠረት አድርጎ የቀበሌው አስተዳደር እንጂ ቀጥታ ተጠሪዎች አለመሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ሰበር ሰሚው ችሎት በውሳኔው «ሽያጩ በውሉ ያልተመላከተ ነው» በማለት ለውሳኔው መነሻ ምክንያት ቢያደርግም በክልሉ ፍ/ቤቶች ማስረጃዎችን መዝነው ያረጋገጡት እና መዝገቡም የሚያስረዳው ግራ ቀኙ ውላቸውን በማሻሻል ተጠሪዎች ወፍጮውን እና ጊቢው ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች ለአመልካች እንደሸጡላቸው ነው፡፡

በዚህ አግባብ በሕገ መንግሥቱ «መንግሥት ለኢንቨስትመንት የሰጠውን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ሕገ መንግሥታዊነቱ እና የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለኢንቨስትመንት የተሰጠን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም» ብሎ የመወሰኑን ሕገ መንግሥታዊነት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 6 መሬት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለግል ባለሃብቶች የመሬት መጠቀምን መብት እንደሚያስከብርላቸው ደንግጓል፡፡ ይህም የሚያስረዳው የመሬት ባለቤትነት የሕዝብና የመንግሥት በመሆኑ ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል መሬትን የማስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሬት የመጠቀምን መብት ለባለሃብቶች ማስተላለፍ፣ ማከራየት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሕጋዊውን ስነ

ሥርዓት ተከትሎ የኪራይ ውሉን ማቋረጥ መሬቱን ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል፡፡

መሬቱን የተከራዩት ባለሃብቶች በአንጻሩ የመሬቱ ተጠቃሚ እንጂ ባለቤት ባለመሆናቸው ባለቤት ከሆነው ከመንግሥት ዕውቅና ውጪ የተከራዩትን መሬት ማስተላለፍ አይችሉም የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ የክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 22/5 እና 26/4/ ከመንግሥት የገጠር መሬት ተከራይቶ የሚጠቀም ባለሀብት የተከራየውን የእርሻ ኢንቨስትመንት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ መሆኑን እና ባለሀብቱ ከሚመለከተው አካል ዕውቅና ውጪ የተከራየውን መሬት ለሦስተኛ ወገን አስተላልፎ ሲገኝ የኪራይ ውሉ እንደሚቋረጥ ይደነግጋል፡፡

ይህም የሚያስረዳው ባለሀብቱ ለኢንቨስትመንት የተከራየውን መሬት ከሚመለከተው አካል ዕውቅና ውጪ ማስተላለፍ የማይችል መሆኑን እንጂ በአጠቃላይ ለኢንቨስትመንት የተሰጠ መሬት ለሦስተኛ ወገን አይተላለፍም የሚል አንድምታ አይኖረውም፡፡ አዋጁ ማስተላለፍን በጠቅላላው ባለመከልከሉ የግራ ቀኙን ስምምነት መነሻ በማድረግ የትግራይ ክልል የአካባቢ ስነ ጥበቃ ኤጀንሲ የገጠር መሬት አስተዳደር ታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለአመልካች መስጠቱ ለሽያጩ ዕውቅና የሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡

ባለሀብቱ ንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለውን መብት ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) አንጻር ስንመለከተው ንብረትን የመሸጥ መብት የሚገደበው የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ፣ ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር ሲቃረን ወይም በሕግ በተወሰነ ጊዜ ብቻ መሆኑን በድንጋጌው ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ሽያጩ በሕግ ያልተከለከለ፣ የሕዝብ ጥቅምን የማይጋፋ እና የሌሎችን መብት እና ጥቅምን የማይቃረን በመሆኑ ንብረቱን በጠቅላላው ማስተላለፍ አይቻልም ተብሎ መተርጎሙ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40 ድንጋጌ ይቃረናል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትርጓሜው በጠቅላላው መንግሥትም ሆነ ባለሀብቱ ለኢንቨስትመንት በኪራይ የተሰጠን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም ማለቱ በሕገ መንግሥቱ የመሬት ባለሀብትነት ለመንግሥት እና ለሕዝብ ከመሰጠቱ እና መንግሥት በባለቤትነት መብቱ የተለያዩ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ በመሬት የመጠቀም መብትን የሚያስተላልፍበትን አግባብ የሚገድብ ነው፡፡

በዚህም መሠረት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84(1) እና በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40/1/ ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

### 4. የገጠር መሬት አጠቃቀም አስመልክቶ የተሰጡ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 4ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ.57/10

#### 4.1አመልካች፡- አቶ ጀማል ሰይድ፣ ተጠሪ፡- አቶ ገራድ ጉዲሳ ቡሽራ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጉራጌ ዞን በሀላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የጉዳዩም አመጣጥ የአሁን ተጠሪ በ26/05/2007 ዓ.ም ለሀላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ከአመልካች ጋር በነበረን የጋብቻ ዝምድና ምክንያት በደርግ ዘመን ከታወጀው የመሬት ላራሹ አዋጅ ጊዜ ጀምሮ ስጠቀምበት የነበረውን 0.18 ሄክታር መሬት በጋራ ለመጠቀም ተስማምተንና ሰጥቻቸው ይዞታውን በስማቸው ሊያደርጉ ሲሉ ስለደረስኩበት ይዞታውን እንዲለቁልኝ በማለት ክስ በማቅረባቸው ነው፡፡ አመልካችም መሬቱን ከ20 ዓመት በላይ ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን፣ ጉዳዩም በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የኪራይ ውሉ በክልሉ የመሬት አስተዳደር አዋጅ መሠረት አለመሆኑ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑና ከወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተገኘን ማስረጃ መሠረት አድርጐ መሬቱ ለአመልካች ይገባል ብሎ ወስኗል፡፡

ግራቀኙ ተከራካሪዎች በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ እያቀረቡና በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች በደረጃ አንድ ጊዜ ለተጠሪ ሌላ ጊዜ ለአመልካች እየተወሰነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት ለተጠሪ ይገባል በማለት መወሰኑ፣ አመልካች ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ጊዜው በማለፉ ምክንያት ተጠሪ የአፈጻጸም መዝገብ ከፍተው ካስፈጸሙ በኋላ በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ የታዘዘውና ውሳኔ የተሰጠበት ነጥብ ስለሚለያይ ማለትም ውሳኔ የተሰጠው በ0.18 ሄክታር ላይ ሲሆን አፈጻጸሙ ግን በ2.5 ሄክታር ላይ ነው በማለት አመልካች የስር ፍ/ቤቱን ቢጠይቁም ፍ/ቤቱ እንደ ጥያቄያቸው ስላልፈጸመላቸው ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አመልክተዋል፡፡

ከፕሬዝዳንቱም በተጻፈ ደብዳቤ ሌላ የአፈጻጸም መዝገብ ተከፍቶ በዚህም የአፈጻጸም መዝገብ ሊፈጸም የሚገባው 0.18 ሄክታር እንጂ 2.5 ሄክታር አይደለም ተብሎ ስለተወሰነ ይህም ውሳኔ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ በክልሉና ሰበር ሰሚ ችሎት ስነ ሥርዓታዊ አካሄድ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡

የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በአፈጻጸሙ ሳቢያ ውሳኔ ያላረፈበት ይዞታዬ አብሮ ተወስዶብኛል የሚሉ ከሆነ በዚህ ረገድ ያላቸውን አቤቱታ በዚያው የአፈጻጸም

መዝገብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ/ 349 ድንጋጌ መሠረት አቅርበው መስተናገድ ይችሉ የነበረ ከመሆኑ ውጭ በፍርድ ኃይል ተገደው ያስረከቡትን ይዞታ ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በተጻፈ ደብዳቤ መነሻ አድርገው በሌላ አፈጻጸም መዝገብ መልሰው ሊረከቡ የሚችሉበት ስነ ሥርዓት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ሰኔ 3 ቀን 2008 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በእኔ እና በተጠሪ መካከል በነበረው መሬት ይዞታ ክርክር አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 113960 በቀን 28/7/2008 በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከ25 ዓመታት በላይ ስጠቀምበት ከነበረው የእርሻ መሬቴ የሚያፈናቅለኝ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የቀረበው አቤቱታ ከውሳኔው ጋር ሲመረመር አመልካች ክስ የቀረበበትና ክርክር የተካሄደበት ይዞታ በአፈጻጸም ከተፈጸመው ጋር የተለየ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህም መሠረት ክርክር የተካሄደበትና የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያረፈበት 0.18 ሄክታር መሬት ነው፡፡ ይሄው የክርክር ነጥብ በሌሎች ውሳኔዎችም ላይ የተለወጠ መሆኑ አይታይም፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያው የአፈጻጸም መዝገብ ውሳኔ ከተሰጠበት ይዞታ ጋር የተለየ ነው፡፡ ይህም በሁለተኛው አፈጻጸም ክርክር መዝገብ ላይ አልተስተባበለም፡፡ /ክርክር አልተካሄደበትም፡፡/ አመልካችም ከተወሰነባቸው 0.18 ሄክታር ውጭ ያለው የእርሳቸው ይዞታ መሆኑን እና ከአራት ቤቶች በላይ የሠሩበትና ብዙ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ይኸው ጉዳይ በጽሕፈት ቤቱ በኩል ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግበት ጉባዔው ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ማጣራት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የደቡብ ክልል ሀላባ ልዩ ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት በቁጥር 1048/2010 በቀን 11/04/2010 በላከው ደብዳቤ አመልካችና ተጠሪ 0.18 ሄክታር መሬት አብረው በጋራ ይጠቀሙ የነበረ መሆኑን፣ በፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪ ክሳቸው ላይ አቅጣጫ ሲጠቅሱ የአመልካች ይዞታን ጨምረው ጠቅሰውት ስለነበር በፍ/ቤቱ ውሳኔ አመልካች ከ2 ሄክታር በላይ ከሆነው ይዞታቸው ላይ ተነስተዋል፡፡

በዚህም ውሳኔ አመልካች ከነልጆቻቸው ከይዞታቸው የተነሱና በአሁኑ ጊዜም ሌላ ይዞታ የሌላቸው መሆኑን ጽሕፈት ቤቱ ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ መሆናቸውንና ተጠሪ ክርክር ከተነሳበት ይዞታ ውጭ

ሌላ ከ10 ሄክታር በላይ መሬት ያላቸው መሆኑን በደብዳቤው ላይ ተገልጿል፡፡ ከዚህ ማስረጃ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ክስ ሲመሠርቱ የአመልካችን የግል ይዞታ በመጨመር አቅጣጫ የጠቀሱ በመሆኑ ክርክሩ በተጨባጭ በ0.18 ሄክታር ላይ ቢሆንም የአመልካች ቀሪ ይዞታ በአፈጻጸም ወቅት የተወሰደባቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሠረት አመልካች ከነቤተሰባቸው ከይዞታቸውና ንብረታቸው የተፈናቀሉ መሆኑና ክርክር ከተነሳበትና በውሳኔው ከተወሰደባቸው ይዞታ ውጭ ሌላ ይዞታም አለመኖሩን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም በመጀመሪያው የአፈጻጸም መዝገብ ላይ የሚስተዋለው ችግር ፍ/ቤቱ በስነ ሥርዓት ሕጉ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉንና በተጨባጭ ያለውን ሀቅ ወደ ጎን በመተው ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ ውሳኔውም አርሶ አደርን ከሕግ ውጭ ከይዞታው የሚነቅልና ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 ጥበቃ የተደረገለትን ከይዞታ መሬት ያለመነቀል ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚነፍግ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለዚህ የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ መርቶለት ኮሚቴው የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የጉዳዩ መነሻ የእርሻ መሬት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ተከራካሪ ወገኖች ተከራክረው በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበትና በአፈጻጸም የአሁን ተጠሪ ሊረከቡት የሚገባ 0.18 ሄክታር መሬት መሆን ሲገባው በተፈጠረው የአፈጻጸም ስህተት የአሁን አመልካች ቤተሰቦቻቸውን ይዘው የሚተዳደሩበትና ውሳኔ ያልተሰጠበትን የእርሻ መሬት ጨምሮ ጠቅላላ 2.5 ሄክታር በአፈጻጸም እንዲያስረክቡ መደረጉ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/4/ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ስለሆነ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

ሚያዝያ 22 ቀን 2010 ዓ.ም

የመ/ቁ.44/10

---

### 4.2. አመልካቾች፡- እነ ከተፎ ገ/የስ (2 ሰዎች)፣ ተጠሪ፡- ወጣት በሱፍቃድ አየለ

የኢ.ፌዴሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካቾች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

አመልካቾች ዕድሜያቸው የገፋ በመሆኑና ጧሪ ስላስፈለጋቸው የይዞታ መሬታቸውን ታህሳስ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የስጦታ ውል ለተጠሪ ካስተላለፉለት በኋላ ተጠሪው ስጦታ አድራጊዎቹን ባለመጦሩ በዘመድ ቤት ተጠግተው እየኖሩ መገኘታቸውን ገልፀው የስጦታ ውሉ ፈራሽ ይሁንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው ጉዳዩን ያዩት ፍርድ ቤቶች የስጦታ ውሉ አይፈርስም በማለት በመወሰናቸው አመልካቾች ውሳኔው ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን የሚቃረን ነው በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥ አቤቱታ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አቅርበው ጉባዔው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በሆኑበት በአማራ ብ/ክ/መንግሥት በሰሜን ሸዋ ዞን በእንሳሮ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የክሱ ፍሬ ሀሳብም አመልካቾች እድሜያቸው የገፋ በመሆኑና ጧሪ ስላስፈለገን ለተጠሪ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ባዋሳኝ የተጠቀሰውን ይዞታ መሬታችንን ታህሳስ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ውል በስጦታ ካስተላለፍንለት በኋላ በስሙ የይዞታ ማረጋገጫ አውጥቶ እኛን ባለመጦሩ በዘመድ ቤት ተጠግተን እየኖርን ስለምንገኝ ስጦታው ፈራሽ ይሁንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በሰጡት መልስ ውሉ ከተደረገበት ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ከሁለት ዓመት በላይ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል መቃወሚያ እና በአማራጭ በሰጡት መልስ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ከግራ ቀኙ የቀረበለትን ክርክር ሰምቶ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 244 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በይርጋ ሊታገድ አይገባም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ማስረጃ በመስማት አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መዝገቡን መልሷል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት አከራክሮ አመልካቾች ለተጠሪው ያደረጉት የይዞታ መሬት ስጦታ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የሌለ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም፤ ተጠሪው በስጦታ ውሉ መሠረት እየተጠቀመ እስካሁን የሚያደርገውን እንክብካቤ ይቀጥል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾች በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ከአከራከረ በኋላ ተጠሪ በራሱ መኖሪያ ቤት ተቀምጦ እያለ ጦሬያለሁ እየተንከባከብኩ ነው ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካቾች ያደረጉት የይዞታ መሬት ስጦታ ውል ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ በቅሬታቸውም በስር ፍርድ ቤት ያቀረብኳቸው ምስክሮች አመልካቾችን እየጦርኩ መሆኔን በሚገባ አስረድተው እያለ የስጦታው ውል ግዴታዬን እንዳልተወጣሁ ተቆጥሮ ፈራሽ ነው በሚል የተወሰነው ውሳኔ አግባብ ባለመሆኑ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የይግባኝ ቅሬታውን መርምሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የስጦታ ውሉ ፈራሽ ይሆናል በማለት የሰጠው ምክንያት አሳማኝ ነው ወይ? ይግባኝ ባይ የውል ግዴታውን አልተወጣም ከተባለ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉትን ነጥቦች ለማየት ያስቀርባል በማለት መልስ ሰጪዎች መልስ እንዲሰጡ አድርጓል፡፡

በዚሁ መሠረት ተከራካሪ ወገኖች መልስ አቅርበው ፍ/ቤቱ ማስረጃ ከመረመረና የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ይግባኝ ባይ ስጦታ አድራጊዎችን እየጦረና እየተንከባከበ መሆኑን፣ ወደፊትም በዚሁ መልኩ ድጋፍ እንደሚያደርግ በስር ፍርድ ቤት ባደረጉት ክርክር መጠቀሱን በመግለፅ በስጦታ ውሉ ውስጥ ግዴታ ያለው ከሆነ ማስገደድ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2462/1/ ላይ የተደነገገ መሆኑን በመግለጽ የስጦታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፤ ይኸው ውሳኔ በአብክመ እና በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎቶች ፀንቷል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 22 ቀን 2008 ዓ.ም ጽፈው ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ባቀረቡት አቤቱታ በፍርድ ቤቶች የፀናው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔውም ጉዳዩን በጥልቀት ከመረመረ በኋላ አመልካቾች የመሬት ይዞታቸውን ሙሉ በሙሉ በስጦታ ውል ማስተላለፋቸው በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ እንደሆነ፣ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ሆኖ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ መሆኑን በመግለጽ አመልካቾች የመሬት ይዞታቸውን ሙሉ በሙሉ በስጦታ ወደ ተጠሪ እንዲተላለፍና ከይዞታቸው እንዲፈናቀሉ ያደረገው ውል ሊፈርስ አይገባም በማለት ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ከኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/3 እና 4/ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል የሚል የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ ልኳል፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ፣ ያጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሃሳብና ሕገ መንግሥቱን በማጣመር መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ተጠሪ የአመልካችን የመሬት ይዞታ በሥጦታ ውል በሕጋዊ መንገድ የተረከበ መሆኑን ተጠሪ አመልካቾችን በቅርብ በመሆን የማይጦራቸውና የማይንከባከባቸው በመሆኑ አመልካቾች የስጦታ ውሉ ይፍረስ በማለት ፍርድ ቤቱን መጠየቃቸውን፤ ተጠሪ በበኩሉ የስጦታ ውሉ ላይ ለመጦርና ለመንከባከብ ግዴታ አልገባሁም በማለት በመከራከሩ ብቻ ፍርድ ቤቶች የስጦታ ውሉ እንዲፀና ውሳኔ መስጠታቸው አርሶ አደሮች ከመሬት

ይዞታቸው ላይ አላግባብ እንዲፈናቀሉ የሚያደርግ ውሳኔ መሆኑን አጣሪ ጉባዔው ተገንዝቦ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40/3 እና 4/ ጋር ይቃረናል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሕገ መንግሥቱን የጣሰ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

### 4.3. አመልካች፡- አቶ አብዱራህማን ኡርጌሳ፣ ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሐሊማ ቶላ

የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዶዶታ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ የጉዳዩ ይዘትም የአመልካች ወላጅ እናትና አባት ሲሞቱ አመልካች የእንጀራ እናታቸው ከሆኑት ከተጠሪ ጋር ለክርክር ምክንያት በሆነው የገጠር ይዞታ መሬት ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ አብረው ሲጠቀሙ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን የእናትና አባታቸው መሬት ይዞታ ድርሻ እንዲያካፍሏቸው ተጠሪን ጠይቀው ፍቃደኛ ስላልሆኑ በሕግ ተገደው እንዲያካፍሏቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም በሰጡት መልስ የአመልካች አባት እና እናት ከሞቱ 25 ዓመት እና 50 ዓመት መሆኑን አመልካችም ራሳቸው ስላልካዱ ከዚህ ጊዜ በኋላ የውርስ ይዞታ መሬት ለመጠየቅ አመልካች በይርጋ ይታገዳሉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካች ወላጅ እናትና አባት ሲሞቱ አመልካች የእንጀራ እናታቸው ከሆኑት ተጠሪ ጋር ለክርክር ምክንያት በሆነው የገጠር መሬት ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ አብረው ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን የውርስ ንብረት ማጣራት ሳይደረግ አመልካች ከተጠሪ ጋር በይዞታው እየተጠቀሙ መቆየታቸው የአመልካች አባት ከሞቱ ከ25 ዓመት እና እናታቸው ከሞቱ ከ50 ዓመት በኋላ ይህንን ይዞታ ለመካፈል ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ከመሆን ስለማያግደው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ባለመቅረባቸው የአመልካችን ክርክር በመስማት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት ወስኗል፡፡ ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም ሲሉ መዝገቡን ዘግተዋል፡፡

አመልካች ለአጣሪ ጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ ለክርክር መነሻ የሆነውን የቤተሰቦቼን የገጠር ይዞታ መሬት ከተጠሪ ጋር በጋራ ስንጠቀም ከቆየን በኋላ ተጠሪ ያለ ምንም ምክንያት ይዞታውን እንዳልጠቀም ስላደረጉኝ ክስ ባቀርብም በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች ከሕግ ውጭ ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ ከኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3) ጋር የሚጋጭ እና ከይዞታዬ ያፈናቀለኝ ስለሆነ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባዔው የአመልካችን አቤቱታ ከፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ እና በንዑስ አጣሪ ጉባዔ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት በተደረገው ማጣራት ከተገኘው መረጃ እንዲሁም አመልካችና ምስክሮች በጉባዔው ስብሰባ ቀርበው ከሰጡት ቃል ጋር ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም ጉባዔው በሰጠው አቅጣጫ መሠረት በተደረገው ማጣራት የዶዶታ ወረዳ ገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በቁጥር WLBEN/675/9-1/2007 በቀን 26/10/2007 ዓ.ም ለወረዳው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ምላሽ እና በምክትል የወረዳው አስተዳደር እና የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ ሰብሳቢነት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙና ሌሎች የሚመለከታቸው ወገኖች ተገኝተው የሰጡት ቃል እና ቃለ ጉባዔ እንዲሁም የገጠር ይዞታ መሬት ማረጋገጫ ደብተር ተመልክተናል፡፡ እነዚህም ማስረጃዎች የሚያስረዱት ለክርክር ምክንያት የሆነው የገጠር ይዞታ መሬት የአመልካች ወላጆች ይዞታ እንደነበር ነው፡፡ የአመልካች ወላጅ እናት ቀድመው ሲሞቱ ወላጅ አባቱ ተጠሪን በማግባት በመሬቱ በመጠቀም አብረው እየኖሩ እርሳቸውም መሞታቸው ተረጋግጧል፡፡

የአመልካች ወላጆች ከሞቱ ረጅም ጊዜ እንደሆናቸው ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ ተጠሪም ባለቤታቸው የሆኑት የአመልካች አባት ከሞቱ በኋላ በ1996 ዓ.ም መሬቱን በስማቸው አስመዝግበው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዳወጡበት እና በዚህ ጊዜ አመልካች ደግሞ የቤተሰብ አባል ተብሎ መመዝገባቸውንም ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

በመሠረቱ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ 130/99 አንቀጽ 6 እና 9 መሠረት የገጠር መሬት የውርስ ጥያቄ ከሌላው ንብረት የውርስ ጥያቄ ይለያል፡፡

ለዚህም አንዱና ዋነኛው ምክንያት የመሬት ባለቤትነት መብት የሕዝብ እና የመንግሥት በመሆኑ ግለሰብ በመሬት ላይ ያለው መብት በመሬት የመጠቀም መብት ብቻ መሆኑ ነው፡፡

ይህንኑ የሕገ መንግሥቱን መርህ ለማስፈፀም በፌዴራልም ሆነ በክልል የወጡት ሕጎች ይህንኑ በመሬት የመጠቀም መብትን ብቻ መሠረት አድረገው የተቀረፁ ናቸው፡፡ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ እና ደንብ መሠረት የገጠር መሬት የውርስ ጥያቄ አውራሽ ከሞተ በኋላ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በግልፅ የደነገገው ጊዜ የለም፡፡ ከዚህ ባለፈ ወራሽ በሆነ እና ወራሽ ባልሆኑ ግለሰቦች መካከል በተለይም በይዞታው በጋራ አብረው ሲጠቀሙበት የነበሩ ሰዎች መካከል የውርስ ይዞታ መሬት ጥያቄን ለማቅረብ የይርጋ ጊዜ የሚያግድ ስለመሆኑ የሚደነግግ አንቀጽ የለም፡፡ ለመሬት ይዞታ የውርስ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የውርስ ጥያቄ አቤቱታዎች በተለይም ውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በውርስ ንብረቱ በጋራ ሲጠቀሙ በነበሩ ሰዎች መካከል የይርጋ ተፈጻሚነት ስለመኖሩ የውርስ ሕጉም የሚደነግገው ነገር የለም፡፡ በተለይም በንብረቱ በጋራ ሲጠቀሙ ከነበሩ ግለሰቦች መካከል አንዱ ግለሰብ ሌላኛው ግለሰብ በንብረቱ እንዳይጠቀም እገዳ ሲያደርግበት የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው አንደኛው ወገን በንብረቱ እንዳይጠቀም ከተከለከለበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠር የይርጋ ጊዜ ከሚሆን በቀር ወደ ኋላ ተመልሶ አውራሾች ከሞቱበት ጊዜ አንስቶ የይርጋ ጊዜ የሚቆጠርበት አግባብ አይኖርም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፍርድ ቤት በነበረው ክርክርም ሆነ በጉባዔው በተደረገው ማጣራት እንዲሁም በጉባዔው ቀርበው ከተሰሙት ምስክሮች ማረጋገጥ እንደሚቻለው አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ክስ እስከተመሠረተበት ጊዜ ድረስ ከተጠሪ ጋር በይዞታው አብረው ይጠቀሙ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች ሟች አባታቸው ከሞቱ በኋላ ከተጠሪ ጋር በይዞታው እየተጠቀሙ መኖራቸው የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ደግሞ አመልካች ይህን መብት ሊያገኙ የቻሉት ከላይ ከተጠቀሰው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ይህ ሕግ ያጎናፀፋቸውን መብት ለፍርድ ቤት አቅርበው የውርስ ሀብት እንዲጣራላቸው ወይም ክፍፍል እንዲደረግላቸው ባይጠይቁም በይዞታው ግን ለረዥም ጊዜ ሲጠቀሙ በመቆየታቸው ብቻ ከይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ነፃ እንደሚያደርጋቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ውስጥ አመልካች በቤተሰባቸው ይዞታ ረዥም ጊዜ ሲጠቀሙ እንደነበር ተጠሪ ራሳቸው ባልካዱበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የገጠር መሬት ይዞታን ሲጠቀም በቆየ ሰው ላይ ይርጋን ተፈጻሚ ማድረጋቸው በተለይም የፍ/ሕ/አንቀጽ 1000(3)ን ተፈጻሚ ማድረጋቸውና ሟች ከሞተበት ጊዜ አንስቶ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ውርስ እንዲጣራ አመልካች ለፍርድ ቤት ማመልከት ነበረባቸው በሚል ምክንያት ጉዳዩን በይርጋ መዝጋታቸው ሕገ መንግሥቱ ለአርሶ አደሮች ካደረገው ጥበቃና ይህንኑ ለማስፈፀም ከወጣው ከክልሉ ሕግ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

በመሠረቱ የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ የሚሆነው ከፈቃድ፣ ከውል ወይም ከሕግ ውጭ ንብረት ተይዞ በሚቆይበት ጊዜ እንጂ የንብረቱ ባለቤት በንብረቱ በጋራ እየተጠቀመ ከቆየና ፍቃዱ ባለበት ሁኔታ አይደለም፡፡ አንድ ሰው በይርጋ ምክንያት መብቱን የሚያጣው በንብረት መብቱ መጠቀም ሲያቆም እንጂ በንብረቱ እየተጠቀመ የቆየን ባለመብት ይርጋ የሚያግደው አይሆንም፡፡ ይህ መርህ ለሁሉም ንብረቶች ተፈጻሚነት ያለው ሲሆን ለመሬት ይዞታ የውርስ ክርክርም ተፈጻሚነት የሚያጣበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም በመሬት ይዞታ መብቱ ይጠቀም የነበረ ግለሰብ በይርጋ ምክንያት መብቱን ሊያጣ የሚችለው በይዞታው መጠቀም ሲያቆም እንጂ በመሬቱ እየተጠቀመ የቆየን ባለመብት ይርጋ የሚያግደው አይሆንም፡፡

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የይርጋ ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያርመው መቅረቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) ለአርሶ አደሮች የተረጋገጠው ከመሬት ይዞታ ያለመፈናቀል መብት ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

ስለዚህ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር አያስቀርብም ተብሎ የተዘጋው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰ/መ/ቁጥር 89385 ላይ በተመሳሳይ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ በትዕዛዝ የተዘጋው ይህ ጉዳይ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) ጋር የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባዔው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባዔውንና የምክር ቤቱ

ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባዔውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሮታል፡፡ በዚህም መሠረት የአመልካቹን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚቃረን መሆን አለመሆኑን በዝርዝር ለመመርመር የአመልካቹን አቤቱታ፣ የፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሁም በአጣሪ ጉባዔ በተጨማሪ የተደረገው የማጣራት ሥራ ተመልክቶ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የመሬት ይዞታ የአመልካች ወላጆች ይዞታ እንደነበርና የአመልካቹ ወላጅ እናት ቀድመው ሲሞቱ ወላጅ አባቱ ተጠሪን በማግባት በመሬቱ በመጠቀም አብረው እየኖሩ እሳቸው መሞታቸውን፣ ተጠሪም በ1996 ዓ.ም መሬቱን በስማቸው አስመዝግበው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዳወጡበትና በዚህ ጊዜ አመልካቹም የቤተሰብ አባል ተብለው መመዝገባቸው በፍ/ ቤቶች መረጋገጡን አጣሪ ጉባዔው ከተረዳ በኋላ የመሬት ባለቤትነት መብት የሕዝብና የመንግሥት በመሆኑ ግለሰብ በመሬት ላይ ያለው መብት በመሬት የመጠቀም መብት ብቻ ሲሆን ይህም መርህ የሕገ መንግሥቱ መርህ እንደመሆኑ መጠን በፌደራልም ሆነ በክልል የሚወጡ ማናቸውም ሕጎች የሕገ መንግሥቱን መርህ በተከተለ አግባብ መቀረጽ አለባቸው ሲል ተችቶ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ መሠረት የገጠር መሬት ውርስ ጥያቄ አውራሽ ከሞተ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በግልፅ የተደነገገ ጊዜ በሌለበት፣ በይዞታው በጋራ ሲጠቀሙ የነበሩ ሰዎች መካከል የውርስ ይዞታ ጥያቄን ለማቅረብ የይርጋ ጊዜ የሚያግድ ስለመሆኑ የሚደነግግ አንቀጽ በሌለበትና አመልካቹ በቤተሰባቸው ይዞታ ረዥም ጊዜ ሲጠቀሙ እንደነበረ ተጠሪ ራሳቸው ባልካዱበት ሁኔታ ፍ/ቤቶች የገጠር መሬት ይዞታን ሲጠቀሙ በቆዩት አመልካች ላይ ይርጋን ተፈጻሚ ማድረጋቸው በሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 40(4) ላይ ተደንግጎ ለአርሶ አደሮች ከተረጋገጠው መብት ጋር የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባዔውና ቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(4) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## 5. ፍትሕ የማግኘት መብትን አስመልክቶ የተሰጡ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች

የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

$5^{ኛ}$ የፓርላማ ዘመን፣ $5^{ኛ}$ ዓመት፣ $2^{ኛ}$ መደበኛ ጉባዔ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ/ቁ.78/12

### 5.1 አመልካች፡- ፶ አለቃ ግዛው ደንቤ ሳልልህ፣ ተጠሪዎች፡- እነ ኮሚቴ ኦፍ ኢንተለጀንስ ኤንድ ሴኪዩሪቲ ሰርቪስ ኦፍ አፍሪካ (CISSA)(2 ሰዎች)

የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 03 ቀን 2008 ዓ.ም ተጽፎ ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ ከሥራ ቅጥር ውል ጋር የተያያዘ ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ኛ የሥራ ክርክር ችሎት አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን በክርክሩ ተካፋይ ሆኗል፡፡

የጉዳዩ ይዘትም ከየካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ 1ኛ ተጠሪ በጥበቃ ሥራ በወር 1,633 የአሜሪካ ዶላር (አንድ ሽህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሦስት የአሜሪካ ዶላር) ደመወዝና ተያያዥ ክፍያዎች እየከፈለኝ እስከ ጥር 24 ቀን 2006 ዓ.ም ከሠራው በኋላ ካለምንም ምክንያት 1ኛ ተጠሪ በሕገ ወጥ መንገድ የሥራ ውል ሲያቋርጥ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን በ$1,192 (አንድ ሺ.ህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት የአሜሪካ ዶላር) የከፈለኝ ሲሆን ሊከፈለኝ የሚገባ ወይም ቀንሶ ያስቀረብኝ በአጠቃላይ ብር 1,945,600 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ሽህ ስድስት መቶ ብር) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ ገብ በመሆን ባቀረበው አቤቱታ በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ ደርሶት ከተመለከተ በኋላ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠውን ከለላ በመግለጽ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ላይ የሚጠይቁትን ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች መክፈሉን ቀሪ የሚጠይቁትን ገንዘብ በተመለከተ ደግሞ ክሱ ተዘግቶ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስማሚያ ክፍል በድርድር እንዲያልቅ ፍቃደኛ መሆኑን በጽሑፍ እንዳሳወቃቸው በመግለጽ፣ 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ነሐሴ 14 ቀን 2006 ዓ.ም ባደረገው የአስተናጋጅ አገር ስምምነት አንቀጽ 4(1) መሠረት በተሰጠው ከለላ ያለመከሰስ መብት ስላለው ክሱ ተቋርጦ ጉዳዩ በስምምነት እንዲያልቅ ጠይቋል፡፡

2ኛ ተጠሪ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ተግባርና ኃላፊነት ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 15(4) እና 10 መሠረት በስምምነቱ የተካተቱ መብቶች የማስከበርና መከበራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ ክሱን የማየት ሥልጣን የለውም፤ ክሱ ቢቀጥል ከለላ ባለመስጠት ኃላፊነት ስለሚያስከትልና 2ኛ ተጠሪ ጥበቃ ለመስጠት ያለመቻሉን ስለሚያመለክት ክሱ እንዲዘጋ ሲል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቹ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን ክስ ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ባቀረበው አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ባደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት አንቀጽ 4 ላይ የድርጅቱ ቅጥር ግቢ፣ የንብረቶቹ፣ ገንዘብና ሀብቱ ያለ መደፈር መብት ከለላ እንደተሰጠው አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥራ ውል በሕገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በማለት ገንዘብ እንዲከፈላቸው ቢያቀርቡም 1ኛው ተጠሪ ገንዘቡን እንዲከፍል ሊወሰንበት እንደማይገባ ከላይ በተጠቀሰው ውል ላይ ከለላ ስለተሰጠው ቢወሰንበትም ሊፈጸም የማይችል እና መብታቸው በማስረጃ ቢረጋገጥ እንኳን 1ኛ ተጠሪ ባለው ከለላ በፍርድ ቤት ውሳኔ መብት ሊያቋቁሙበት አይችሉም በማለት የአመልካች ክስ የክስ ምክንያት የሌለው ነው ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አያስቀርብም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለጉባዔው ባቀረቡት ዝርዝር ቅሬታ 1ኛ ተጠሪ ራሱ ያወጣውንና የአሠሪና ሠራተኞችን አዋጅ በመጣስ ሊከፈለኝ የሚገባውን ጥቅማጥቅም ስለከለከለኝ ለ2ኛ ተጠሪ

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 142 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ጉዳዩን በግልግል ክፍል በድርድር እንዲያይልኝ ያሉኝን ማስረጃዎች ከማመልከቻ ጋር አቅርቤ እንዲጣራ ለዲፕሎማቲክና መብቶች ከለላ ዳይሬክቶሬት ክፍል ተመርቶ በባለሙያዎች ከተመረመረ በኋላ 1ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ሁለት ጊዜ ተጠይቆ ለመደራደር ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጉዳዩ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን በቀን 13/06/07 ዓ.ም ለክቡር ሚኒስትሩ ካቢኔ ጽ/ቤት ቀርቧል፡፡ ካቢኔ ጽሕፈት ቤቱ ሁኔታውን በፕሮቶኮል ክፍሉ በኩል ተጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ እንዲቀርብ ስላዘዘ እንደገና ያሉኝን ማስረጃዎችና ማመልከቻ በማቅረብ ለ1ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ መጻፉን ሰምቼ የሚሰጠውን መልስ ብጠባበቅም መፍትሄ አላገኘሁም፡፡

ስለዚህ በ2ኛ ተጠሪ ለሚጻፉ ደብዳቤዎች 1ኛ ተጠሪ መልስ ባለመስጠቱ ጉዳዩን ሊዳኝ ለሚችልና ፍትሕ ከፍርድ ቤት እንደማገኝ በማመን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ባቀርብም ፍ/ቤቶች ጉዳዩ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ጉዳዩን ዘግተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በሕግ አግባብ የሚገባኝን ክፍያ ሊከፍለኝ ባለመቻሉ ጉዳዩ በ2ኛ ተጠሪ አደራዳሪነት እንዲያልቅ ቢጠየቅም ሊያልቅ ካለመቻሉም በላይ ፍርድ ቤቶችም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ያለመቻላቸው የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 ፍትሕ የማግኘት፣ 79(1-3) የዳኝነት ሥልጣን እና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ስምምነት አንቀጽ 86(1) እና (2) ላይ የተደነገገውን የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት መርሆዎችን የሚጥስ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በፍርድ ቤት ከተሰጠው ውሳኔና አመልካች ተጥሷል በማለት ከጠቀሷቸው የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ጋር በመመርመር የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክር ቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኋላ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሮታል፡፡ በዚህም መሠረት ይህ  የአመልካች ጉዳይ በ2ኛ ተጠሪ አደራዳሪነት በድርድር ክፍሉ እንዲታይ

ስለመጠየቁና እየታየ ከሆነ ጉዳዩ የደረሰበት ደረጃና ውጤት እንዲገለፅ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ተጠይቆ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ጠረሠ23/1/10 በቀን 13 መስከረም 2010 በተጻፈ ደብዳቤ መልስ ተሰጥቷል፡፡

ከዚህም ባሻገር ቀድሞ ጉባዔው ባደረገው ውይይት የለያቸው ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ 2ኛ ተጠሪ የሆነው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠይቆ በቁጥር IRO23/9/1/09 በቀን 04/05/09 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የተያዘውን ዓይነት ጉዳይ በፕሮቶኮል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄነራል የዲፕሎማቲክ መብት፣ ጥበቃና ከለላ ዳይሬክቶሬት የሥራ ክፍል የሚታዩ መሆናቸውን፤ አለመግባባታቸው በሥራ ውላቸው እና በተጠሪዎች መካከል በተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት በድርድር ለመፍታት ጥረት ይደረጋል ሲል 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያደረገውን ስምምነት የእንግሊዝኛ ቅጅ በማያያዝ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ ያለውን የቅጥር ውላቸውን እንዲያቀርቡ ተጠይቀው የመጀመሪያው አምስት ዓመታት ቅጥር ውል በቃል ስለነበር ለዚህ የማቀርበው ማስረጃ የለም በማለት ነገር ግን ከየካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ስለመቀጠራቸው በስንብት ደብዳቤው መገለጹን ጠቅሰው አቅርበዋል፡፡

አመልካች በአስረጅነት ያቀረቡት ማስረጃ ባይኖርም አለመግባባቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የግልግል ክፍል እንዲፈታ ጥያቄ አቅርበው ተጠሪ በፈቃደኛነት መልስ ሊሰጥ ባለመቻሉ እና ለግልግል ክፍሉ ጉዳዩ ከአቅሙ በላይ መሆኑ ስለተረጋገጠና የተሰጣቸውም መፍትሄ ስለሌለ በአማራጭ ወደ ፍርድ ቤት አምርተው ከላይ የተመለከተው ውሳኔ ስለመወሰኑ በአቤቱታቸው ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ለፍርድ ቤት በሰጠው መልስ 1ኛ ተጠሪ የፍ/ቤቱ ክስ እንዲዘጋና የአመልካች ክስ በውጪ ጉዳይ ሚ/ር ማስማሚያ ክፍል በድርድር እንዲያልቅ መጠየቁን ገልጿል፡፡ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃም በ2ኛ ተጠሪ በኩል ተልኳል፡፡

አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ሚያዝያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ያቀረቡትን አቤቱታ ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በጻፈው ደብዳቤ በዝርዝር የአመልካች አቤቱታና ቅሬታ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በደብዳቤ ቁጥር AU2-9/2/06 በቀን 13 ጁላይ 2014 (እ.ኤ.አ) በተፃፈ ደብዳቤ ተጠይቋል፡፡ 1ኛ ተጠሪም በቀረበለት ጥያቄ መሠረት በአመልካች ጉዳይ ላይ ለ2ኛ ተጠሪ በደብዳቤ ቁጥር CISSA/2/15/2015/34 በዝርዝር መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪ

የሰጠው መልስ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በፕሮቶኮል ክፍሉ በኩል ግልባጩ እንደደረሳቸው በመግለፅ እንደገና ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ 2ኛ ተጠሪ በድጋሚ ለ1ኛ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ወይም ተወካይ እንዲልክ መጠየቁን የሚገልፅ የደብዳቤ ግልባጭ ቀርቧል፡፡

2ኛ ተጠሪ ለጉባዔው በጻፈው በመጨረሻው ደብዳቤ አመልካች ሚያዝያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ለ2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት መሥሪያ ቤቱ 1ኛ ተጠሪን በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት እ.ኤ.አ. ሐምሌ 31 ቀን 2014 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሐምሌ 24 ቀን 2006 ዓ.ም) የጠየቀ ሲሆን 1ኛ ተጠሪም በጉዳዩ ላይ እ.ኤ.አ. ጥር 15 ቀን 2015 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር ጥር 7/2007) መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በድጋሚ ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ጉዳያቸው በድርድር እንዲታይ ለ2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት 2ኛ ተጠሪ በድጋሚ እ.ኤ.አ. ሐምሌ 30 ቀን 2015 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ.ም) ለ1ኛ ተጠሪ በጻፈው ደብዳቤ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት 1ኛ ተጠሪ ተወካይ ወደ ዳይሬክቶሬቱ እንዲልኩና በተለመደው አሠራር ጉዳዩን መፍታት እንዲቻል ተጠይቆ እያለ አመልካች በዚህ መሀል ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰዳቸው የድርድር ጥያቄው የተቋረጠ መሆኑን በመግለፅ ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ ያለና እልባት ያላገኘ እንደሆነ፡ በቀጣይ ጉዳዩን እንደገና በማንሳት ተጠሪውን ወደ ድርድር መድረክ እንዲቀርብ በማድረግ ጉዳዩን ለመፍታት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልጿል፡፡

አመልካች ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ በኩል ወደ ድርድር እንዲቀርብ የቀረበለትን ጥያቄ ለመቀበል ፍላጎት የለውም በማለት ያቅርቡ እንጂ አመልካች ጉዳያቸው በድርድር እንዲያልቅ ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ለ2ኛ ተጠሪ አቅርበው 2ኛ ተጠሪም ይህንኑ ጥያቄ ለ1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ.ም 1ኛ ተጠሪን ወደ ድርድር ጋብዞ የ1ኛ ተጠሪ የድርድር አቋም ሳይታወቅ አመልካች የጀመሩትን የድርድር ጥያቄ አቋርጠው ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በፍርድ ቤት ክስ እንደመሠረቱ መረዳት በመቻሉ በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከማቅረብ በፊት 2ኛ ተጠሪ በጻፈው ደብዳቤ አግባብ ጉዳዩን በድርድር መፍታት እንዲችል ጥረት መደረጉን ምክር ቤቱ ተረድቷል፡፡

በመሠረቱ በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት የዜጎች መብት እንዳይጣስ እና አለመግባባት ከተከሰተም በድርድር ለመጨረስ የተደረገው

ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(3) እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተለየ ደንብ ወይም መመሪያ እስካላወጣ ድረስ ክርክሩ በኢትዮጵያ ሕግ ሊዳኝ እንደሚገባ የተገለፀውን ተክቶ የሚሠራ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 85 እና 86 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት እና የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎች የዜጎችን እና የሀገሪቱን ጥቅምና ሉዓላዊነት ብቻ ሳይሆን ከመንግሥታትና ዓለም  አቀፍ ድርጅቶች ጋር በሚኖር ግንኙነት የጋራ ጥቅምን፣ እኩልነትንና መሰል ጉዳዮች እንዲያራምድ ያስገድዳል፡፡ ኢትዮጵያም በምታደርጋቸው መሰል ተግባሮች በተመሳሳይ ከለላ መብትና ጥቅም በማግኘት የሀገሪቱን እና የዜጎችን ጥቅም እያረጋገጠች በመሥራት ላይ የምትገኝበት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ነው፡፡ የሁለትዮሽ ስምምነት የሀገሪቱን ጥቅምና ሉዓላዊነት እንዲጥስ የማይፈቅድ፣ እንዳይጣስ የሚያስጠነቅቅ እና ተጥሶ ሲገኝ መብቶችን በስምምነት ለማስመለስ ማካተቱ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 86(1) የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት መርህ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ነገር ግን ይህ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው የሁለትዮሽ ስምምነት በሚፈቅደው መሠረት መንግሥት የዜጎች መብት እንዳይጣስ የማድረግና አለመግባባቶች በሚፈጠሩ ጊዜም ኃላፊነቱን ወስዶ የመፍታት ግዴታ አለበት፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለፍርዱ መሠረት ያደረገው አመልካች የውጭ ድርጅት የሆነውን ተከሳሽ በመክሰስ መብታቸውን በማስረጃ በማረጋገጥ መብት ሊያቋቁሙበት አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ተከሳሽ ያለመከሰስ መብት አላቸው በሚል ነው፡፡

የ1ኛ ተጠሪ ያለመከሰስ መብት የመነጨው ደግሞ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ከተገባው የሁለትዮሽ ስምምነት ነው፤ ነገር ግን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለፍርድ ቤቱም ሆነ ለጉባዔው በሰጠው መልስ መሠረት ጉዳዩን በድርድር መጨረስ የማይችል ከሆነ አመልካች ጉዳያቸውን ለፍርድ አካል በማቅረብ ፍርድ ወይም ውሳኔ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት ይኖራቸዋል፡፡

ስለዚህ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ ጋር ባደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት አለመግባባቶችን በስምምነት (በድርድር) መጨረስ እንደ አንድ የሙግት መፍቻ መንገድ የተቀመጠ ቢሆንም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉባዔው ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር (ለ2ኛ ተጠሪ) ማስማሚያ ክፍል ጉዳዩ በድርድር እንዲያልቅ አቅጣጫ ቢሰጥበትም በ2ኛ ተጠሪ በኩል

ሊፈፀም አልቻለም፡፡ በተጨማሪም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከተው ሚኒስቴር ዴኤታም በጉባዔው ስብሰባ ላይ ተገኝተው ጉዳዩን በድርድር ለመጨረስ አንድ ዕድል ለክፍሉ እንዲሰጥ በመጠየቃቸው ጉባዔው በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከመስጠቱ በፊት ይህንኑ ዕድል ቢሰጥም በዚህ መልክ ሊፈፀም አለመቻሉን ምክር ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያላቸውን ሕጋዊ መብት 2ኛ ተጠሪ በገባው ውል መሠረት በድርድር ማግኘት ወይም ማረጋገጥ ካልቻሉ ጉዳያቸውን ለዳኝነት አካል (ለፍርድ ቤቶች) በማቅረብ መብታቸውን የማስከበር ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል፡፡

ከዚህ ቀደም ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶችም ከላይ የተጠቀሰውን የውጭ ፖሊሲ እና የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት በማድረግ የድርድር ውጤቱ ሳይታወቅና በተለመደው አሠራር 2ኛ ተጠሪ አመልካችን እና 1ኛ ተጠሪን ለማደራደር አለመቻሉን ሳያረጋግጡ ወይም 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ለመደራደር ፍቃደኛ አለመሆኑ ሳይረጋገጥ በተለይም 2ኛ ተጠሪ በጊዜው ግራ ቀኙን ለማደራደር ፍቃደኝነቱን እየገለፀ ባለበት ሁኔታ የአመልካች ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው መጣሱን ማረጋገጥ ባይቻልም አሁን ግን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተቋረጠውን ድርድር በማስቀጠልና ግራ ቀኙን ወደ ድርድር ጋብዞ የጀመረውን የድርድር ሂደት በመቀጠል የደረሰበትን ውጤት ለጉባዔው እንዲያሳውቅ ጉባዔው በጻፈው ደብዳቤና በስብሰባው ላይ ከተገኙት የሚኒስቴሩ ኃላፊዎች ጋር ስምምነት ላይ ቢደረስም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለጉዳዩ እልባት ባለመስጠቱ አመልካች ፍትሕ ማግኘት አለመቻላቸው ሊረጋገጥ ችሏል፡፡

በመሠረቱ 1ኛ ተጠሪ የውጭ ድርጅት ሆኖ ከአመልካች ጋር ያለው ክርክር ከዲፕሎማቲክ መብትና ድርጊት ጋር የሚያያዝ ሳይሆን ጉዳዩ መደበኛ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ በውጭ ሀገር ድርጅቶች ወይም ዲፕሎማቲክ አካላት ጋር የሚሠሩ ሠራተኞች ከዲፕሎማቲክ ሥራና መብት ጋር ያልተገናኘ ነገር ግን መደበኛ የአሠሪና ሠራተኛ መብትን ብቻ በሚመለከት ክርክር ሲነሳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከድርጅቶቹ ጋር በገባው የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት ጉዳዩን በድርድር መፍታት ካልቻለ እንዲህ ዓይነት የአሠሪና ሠራተኛ መደበኛ ክርክርን ብቻ የሚመለከቱ ጉዳዮችን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ለማየት የሚያግዳቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ካለመኖሩም በላይ በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት መሠረት ሕግን መሠረት አድርገው የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች

ተግባራዊ የማድረግ ግዴታቸውን መወጣት የሚጠበቅባቸውና የዕለት ተግባራቸው ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ የሚጠይቁትን ሕጋዊ መብት፣ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በገባው የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት በድርድር ሊያስጠብቅላቸው ባለመቻሉ እንዲሁም ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን ለማየት አንችልም በማለታቸው የአመልካች ሕገ መንግሥታዊ ፍትሕ የማግኘት መብት የተጣሰ ስለሆነ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በማየት ውሳኔ ሊሰጡ ይገባል በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት**

**5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 4ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ**

**ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም**

**የመ/ቁ.72/11**

---

---

## 5.2 አመልካች፡- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት፣ ተጠሪዎች፡- እነ የኢ.ፌዲሪ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን(2 ሰዎች)

**የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት በ05/07/2009 ዓ.ም ለጉባዔው በላከው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ በአቶ አብዮት ዘለቀ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ለጉባዔው ልኳል፡፡

የጉዳዩ ይዘትም በፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባይ የሆኑት አቶ አብዮት ዘለቀ ተጠሪዎች በጋራ በመሆን ያስተላለፉት የዲስፕሊን የጥፋተኝነትና የሥራ ስንብት ቅጣት ውሳኔ ምንም ዓይነት ክስ ያልቀረበበትና በጉዳዩ ያልተከራከሩበት መሆኑን በመግለፅ በተጠሪዎች የተላለፈው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 20(4) ጋር ይጋጫል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 515/99፣ በደንብ ቁጥር 77/94 አንቀጽ 8 አንቀጽ 13 አንቀጽ 17(1) እና (5) በተዘረዘሩት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት አመልካች ለቅጣት ውሳኔ ያበቃውን ክስ የመመልከት፣ የመከራከር፣ የመከላከል፣ በጉዳዩ ላይ ማስረጃዎች ቀርበውም ከሆነ ማስረጃዎችን የማወቅ፣ የመመርመር እንዲሁም መስቀልኛ ጥያቄ የመጠየቅና በጉዳዩ የሕግ ባለሙያዎች የማማከር መብት ሕጉ ያጎናፀፋቸዋል፡፡

ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒው ተጠሪዎች በጋራ በመሆን በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 መሠረት መጋቢት 26 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር EA-164/2/08 በተፃፈ ደብዳቤ በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትና የሥራ ስንብት ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ፅንሰ ኃሳብ ጋር የሚጣረስ ስለሆነ ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ለኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ እንዲላክላቸው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የተደረገው በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 መሠረት ለ1ኛ መልስ ሰጪ መ/ቤት ዋና ዳይሬክተር በተሰጠ ልዩ ሥልጣን መሆኑን እና ሠራተኛውም በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ሥራ የመመለስ መብት የማይኖረው መሆኑን በመግለፅ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ሊዘጋ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ለአመልካች የሥራ ስንብት ውሣኔ መሠረት የሆነው ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 ጋር ተገናዝቦ ትርጉም እንዲሰጥበት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ ለሕገ መንግሥት ትርጉም በላከው የትርጉም ጥያቄ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር በሙስና የጠረጠረውንና እምነት ያጣበትን ማንኛውንም ሠራተኛ መደበኛውን የዲስፕሊን እርምጃ አፈጻጸም ሥርዓት ሳይከተል ከሥራ ማሰናበት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሥራ የተሰናበተው ሠራተኛም በተላለፈበት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ሥራ የመመለስ መብት የለውም፡፡ ይህ ድንጋጌ ከኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) እና ሃገራችን ከተቀበለቻቸው የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14(3)(ለ) እና (ረ) አንፃር ሲታይ ማንኛውም የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ክስ የመመልከት፣ የመከራከር፣ የመከላከል፣ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች የማወቅና ብሎም የመመርመር መብት አለው ከሚለው ድንጋጌ ጋር የማይጣጣም ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚሻው መሆኑን በማመን ለጉባዔው ልኳል፡፡

ጉባዔው ፍርድ ቤቱ የላከውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ለትርጉም ከተላከው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር

ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) እና 25 እንዲሁም ሃገራችን ከተቀበለቻቸው የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14(3)(ለ)(ረ) አንፃር መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) መሠረት ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚችል ማንኛውንም ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ በዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ፍርድ ወይም ውሳኔ ለማግኘት በሕገ መንግሥቱና በሕግ የተቀመጠውን የክርክርና የፍርድ ሂደትን በተከተለ አካሄድ ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ ወይም ፍርድ ማግኘት እንዳለበትም ከዚሁ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህን የፍርድ ወይም የክርክር ሂደትን ሳይከተል የሚሰጥ ውሳኔ ወይም ፍርድ ወይም ይህንኑ የክርክር ሂደት እንዲቀር የሚፈቅድ ሕግ፣ መመሪያ ወይም ደንብ ከዚሁ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡ በተለይም አንድ ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል እንዳያቀርብ የሚከለክል ወይም አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት እንዳይችል ክልከላ የሚያደርግ ማንኛውም ሕግ፣ መመሪያ ወይም ደንብ ከዚሁ ግልፅ ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሃገራችን ከተቀበለቻቸው የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) እና (ረ) መሠረት ማንኛውም የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ክስ የመመልከት፣ የመከራከር፣ የመከላከል፣ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ማስረጃ የማወቅና ብሎም የመመርመር መብት እንዳለውም ተደንግጓል፡፡

በተጨማሪም ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞችን የዲሲፕሊን የጥፋተኝነትና የሥራ ስንብት ቅጣት ውሳኔ አሰጣጥን ስንመለከት የሕገ መንግሥቱን መርህ የተከተለና የዜጎችን የመከራከር መብት የጠበቀ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 515/99፣ ከደንብ ቁጥር 77/94 አንቀጽ 8፣ 13፣ 17(1) እና (5) ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ማንኛውም ሰው የዲሲፕሊን ክስ ሲቀርብበት የቀረበበትን ክስ የመመልከት፣ የመከራከር፣ የመከላከል፣ በጉዳዩ ላይ ማስረጃዎች ቀርበውም ከሆነ ማስረጃዎችን የማወቅና ብሎም የመመርመር እንዲሁም መስቀልኛ ጥያቄ የመጠየቅና በጉዳዩ የሕግ ባለሙያዎችን የማማከር መብቶች እንዳሉት ይደነግጋል፡፡

ይህን የሕገ መንግሥቱን መርህ ተከትለው የወጡ ሕጎች በማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው ሲሆን ከዚህ በተለየና የሕገ መንግሥቱን መርህ ባልተከተለ መልኩ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኞች ብቻ ተብሎ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 የባለስልጣኑን የመንግሥት ሠራተኞች ከሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ጋር እኩል እንዳይደኙ ወይም በሕግ ፊት እኩል የመከራከር መብት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ የደንቡ ድንጋጌ መሠረት በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚሠራን ሠራተኛ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር በሙስና የጠረጠረውና እምነት ያጣበት እንደሆነ መደበኛውን የዲሲፕሊን እርምጃ አፈጻጸም ሥርዓት ሳይከተል ከሥራ ማሰናበት እንደሚችል መደንገጉና በተጨማሪም በዚህ ሁኔታ ከሥራ የተሰናበተው ሠራተኛም በተላለፈበት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ሥራ የመመለስ መብት እንደሌለው መደንገጉ ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሊሰጥበት የሚገባው ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) እና 25 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶለት ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት የቀድሞው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኛ አቶ አብዮት ዘለቀ ክስ ሳይቀርብባቸው፣ ራሳቸውን የመከላከል ዕድል ሳይሰጣቸውና ማስረጃ ሳያቀርቡ በዋና ዳይሬክተሩ ጥርጣሬ ብቻ ከሥራ እንዲሰናበቱ የሚፈቅደውና በየትኛውም ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ወደ ሥራ የመመለስ መብት እንደሌላቸው የሚደነግገው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25፣ 37(1) እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 14(3) /ለ/

እና /ረ/ ጋር የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ እና ቋሚ ኮሚቴው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25፣ 37(1) ጋር የሚቃረን በመሆኑ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1) መሠረት ድንጋጌው ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## 5.3 አመልካች፡- አቶ ጌታቸው ተድላ ኃ/ጊዮርጊስ፣ ተጠሪዎች፡- እነ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8(2 ሰዎች)

የኢ.ፌዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 20/11/2010 ዓ.ም ለጉባዔው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ አቤቱታውም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15468 ሰኔ 25 ቀን 2010 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.142430 ላይ የፀናው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ፍትሕ የማግኘት መብቴን ስለሚጥስ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልኝ የሚል አቤቱታ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ የአሁን አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪዎች የግል ቤቴን ይዘው ስለሚገኙ ይልቀቁልኝ የሚል የክስ አቤቱታ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ እንዲሁም በየደረጃው ላሉት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርቤ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለንም በማለት ስለወሰኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 35(2) መሠረት የትኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንዳለው ለይቶ ትእዛዝ እንዲሰጥልኝ በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎችም በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በሰጡት አስተያየት አመልካች ጉዳያቸውን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ

በመዝገብ ቁጥር 57680 ሥልጣኔ አይደለም በማለት መዝገቡን ሲዘጋው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሳይጠይቁ በቀጥታ ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸው ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ በከተማው አስተዳደር ያሉት ችሎቶችም ሥልጣን የለንም ቢሉም እስከ መጨረሻው የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በመሄድ በመብታቸው አለመጠቀማቸው የራሳቸው ስህተት ነው፤ ጉዳዩን እንደገና ለፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 44662 አዲስ ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ብይን በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይህ ብይንም በይግባኝ አልተሻረም፡፡ ስለዚህ አመልካች በተለያየ ጊዜ ያጡትን መብት ይግባኝ ጠይቀው ሳያሽሩ በሥልጣን ይለይልኝ ሰበብ እንደገና አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት ስለሌለው የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጠቅላይ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 35 (2) ድንጋጌ ሥር እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ፍ/ቤቶች ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በአሁኑ ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ሁሉም ፍ/ቤቶች ሥልጣን የለንም በማለታቸው ሳይሆን ለአንድ ፍርድ ቤት ጉዳያቸውን ሁለት ጊዜ በማቅረባቸው እና በጉዳዩ ላይ መብት እና ጥቅም ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የላቸውም ተብሎ በተሰጠ ብይን በመሆኑና በየጊዜው ፍ/ቤቶች በሰጧቸው ብይኖች ላይ ይግባኝ በመጠየቅ መብታቸውን እስከ መጨረሻ አሟጠው መጠቀም ሲገባቸው ይህንን ሳያደርጉ በመቅረታቸው ያጡትን መብት በሥልጣን ይለይልኝ ሰበብ ለማግኘት ያቀረቡት አቤቱታ በመሆኑ ጉዳዩ በሥልጣን ይለይልኝ ስር የሚሸፈን አይደለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

በአመልካች ቅሬታ አቅራቢነት ጉዳዩን በሰበር ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ የአመልካች ክርክርና ማስረጃ ታይቶ መብት እንዳላቸው አላሳዩም ተብሎ ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን የተሰጠበት ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይን በተመለከተው ፍርድ ቤት በተረጋገጠበት እና የስር ፍርድ ቤት ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለም በይግባኝ ማሳየት ሲቻል አመልካች በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት በመተው ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ይለይልኝ በማለት አቤቱታ ማቅረባቸው የአዋጅ ቁጥር

25/1988 አንቀጽ 35(2) ድንጋጌን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም በማለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

አመልካችም የሰበሩ ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብቴን ይጥሳል በማለት ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 በቀድሞ አጠራር ወረዳ 5 ቀበሌ 12 በአንድ ግድግዳና ጣራ ሥር በአራት ክፍሎች ተከፋፍሎ በቁጥር 1387፣ 1388፣1389 እና 1390 የሚታወቀውን አከራካሪውን ቤት በቀን 22/10/1968 በተጻፈ ቅፅ 004 እና በቁጥር 892/ቀ/12/68 ቀን 04/01/1969 ዓ.ም በተጻፈው ደብዳቤ የግል ንብረቴ መሆኑ ተረጋግጦ የቦታ ኪራይና የቤት ግብር እንዲከፍሉበት ተፈቅዶላቸው እንደነበር፤ አመልካችም በዚህ ንብረት ላይ ያለኝን መብት ለማስከበር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እና በየደረጃው ላሉት ፍ/ቤቶች አቅርቤ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት መልሶብኛል፡፡

በዚህ ምክንያት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የትኛው ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳለው እንዲለይልኝ አቤቱታ ባቀርብለትም ፍ/ቤቱ ግን ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ብሎ የወሰነውን ጉዳይ በድጋሚ ለዚያው ፍርድ ቤት ማቅረብ መብትና ጥቅም እንዳለኝ ተረጋግጧል በማለት ክርክሩን በይግባኝ መቀጠሉ ውጤት እንደማይኖረው በግልፅ እያወቀ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ አመልካች በይግባኝ መብት ሳይጠቀሙ የቀሩትን ጉዳይ በፍርድ ቤት ሥልጣን ሰበብ ለማግኘት መሞከር የሕግ አግባብነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 እና 40 የተደነገገውን የአመልካችን ፍትሕ የማግኘት እና የንብረት መብትን የሚጥስ በመሆኑ ለጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ተሰጥቶ አከራካሪው ንብረት ላይ ተከራክሬ ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብቴ እንዲከበርልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የጉዳዩ ፍሬ ሀሳብ እና የአመልካች ቅሬታ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤቱ ውሳኔ በጉባዔው ተመርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም:-

1ኛ አመልካች ተጠሪዎች ከሕግ ውጪ ቤቴን ይዘው እየተጠቀሙ ስለሆነ ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርበው ኤጀንሲውም በቀን 09/08/1999 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ‹‹አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት የመኖሪያ ቤት የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን ለመውረስ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 ውጭ በመመሪያ

በቀላጤ የተወሰዱ ወይም በአዋጅ አስፈጻሚ አካል ስለመፈቀዱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ የኤጀንሲው ሥልጣን አይደለም›› በማለት መመለሱን፣

2ኛ/ አመልካች ጉዳዩን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በመዝገብ ቁጥር 57680 በቀን 20/10/1999 ዓ.ም ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም፣ ሥልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው በማለት ክሱን በመጀመሪያ ተቃውሞ ውድቅ ማድረጋቸው፣

3ኛ አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አቅርበው ፍ/ቤቱም በመዝገብ ቁጥር 06179 በቀን 29/02/2009 ዓ.ም አመልካች ያቀረቡት ክስ የባለቤትነት ጥያቄ ስለሆነ ይህ ፍርድ ቤት አከራክሮ ጉዳዩን ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት ክሱን መሰረዙን፣

4ኛ አመልካች የአሁን ተጠሪዎች እና ሌሎች 12 ሰዎች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በድጋሚ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ በዚህ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57680 ላይ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት የተወሰነ ውሳኔ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ. 5 መሠረት የአመልካችን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ አመልካች አከራካሪው ንብረት ላይ መብት እና ጥቅም የለውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 33 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት ሌላ አማራጭ ውሳኔ በመስጠት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎ መወሰኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በዚህ ምክንያት አመልካች የክስ አቤቱታ ያቀረቡላቸው ሁሉም የዳኝነት አካላት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለንም በማለት ክሳቸውን ስላልተቀበሉት አመልካች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የትኛው ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳለው ለይቶ እንዲወስንላቸው አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ፣ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም ሳይሆን አመልካች አከራካሪው ቤት ላይ መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት ስለወሰነ ይህ የፍርድ ቤት ሥልጣን የሚለይበት ጉዳይ አይደለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

ከፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት እንደሚቻለው ፍ/ቤቱ ሁለት ጭብጦች ላይ ውሳኔ በመስጠት የአመልካችን ክስ ውድቅ እንዳደረገው ያመለክታል፡፡ የመጀመሪያው ጭብጥ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚል

ሲሆን ሁለተኛው ጭብጥ ደግሞ አመልካች አከራካሪው ንብረት ላይ መብት እና ጥቅም አለው? ወይስ የለውም? የሚሉ ናቸው፡፡

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ፣ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያሳየው አመልካች አሁን ያቀረቡት ጉዳይ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚህ ፍርድ ቤት አቅርበው ይህ ፍርድ ቤትም ሥልጣን የለኝም በማለት የዘጋው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት ሥልጣን የለኝም በማለት የተወሰነውን ጉዳይ በድጋሚ ያቀረቡ ስለሆነ የአመልካች ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 5 መሠረት ውድቅ አድርገናል በማለት ወስኗል፡፡ ይህም በሌላ አረዳድ ፍ/ቤቱ አመልካች ከዚህ በፊት ጉዳዩን ለዚህ ፍርድ ቤት አቅርበው የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል በማለት የወሰነው ቀድሞ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለኝም በማለት የወሰነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ለሁለተኛ ጊዜ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካች አከራካሪው ንብረት ላይ መብት እና ጥቅም አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ፣ የክስ አቤቱታው ለ2ኛ ጊዜ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም ካለ በኋላ እንደገና አመልካች ንብረቱ ላይ መብት እና ጥቅም አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ንብረቱ ላይ መብት እና ጥቅም የለውም በማለት በዋናው የፍሬ ነገር ላይ የዳኝነት ውሳኔ እንደሰጠ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ይህ ደግሞ አንድ የዳኝነት አካል ጉዳዩን ለማየት በሕግ ሥልጣን አልተሰጠኝም የሚል ከሆነ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን እንደሌለው ጠቅሶ መዝገቡን መዝጋት ሲገባው እንደገና በአንድ በኩል ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን እንዳለው አድርጎ የጉዳዩ ፍሬ ነገር ውስጥ በመግባት የመጨረሻ የዳኝነት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲሁም የመጀመሪያው የውሳኔ ክፍል እና የሁለተኛው ውሳኔ ክፍል እርስ በርስ የሚጣረስ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የወሰነው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተግባራዊ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከዚህ ውሳኔ እና ከአጠቃላይ መዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች የክስ አቤቱታውን ያቀረቡላቸው ሁሉም የዳኝነት አካላት ማለትም የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት እና ለ2ኛ ጊዜ ክሱ የቀረበለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ

ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን ክስ እንደመለሱት ያመላክታል፡፡

በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነት ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 35(2) ስር እንደተደነገገው ‹‹አንድ ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የክልል ወይም የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ነው ብለው የያዙት ወይም ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የትኛው ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳለው በመለየት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ይችላል›› በማለት ደንግጓል፡፡

አመልካችም በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክሳቸውን ያቀረቡባቸው ሁሉም የዳኝነት አካላት ሥልጣን የለንም በማለት ክሱን ስላልተቀበሉት የትኛው ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳለው እንዲለይላቸው አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ግን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ይህ ደግሞ አመልካች ተከራክረው ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው እንዲጣስ ያደረገ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች የክስ አቤቱታ ያቀረቡባቸው ሁሉም የዳኝነት አካላት ማለትም፣ የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለንም በማለት የአመልካችን ክስ ስላልተቀበሉ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካች ቅሬታ እና ከላይ በተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የትኛው ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳለው መለየት ሲገባው የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ መወሰኑ አመልካች በአከራካሪው ንብረት ላይ ተከራክረው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 የተደነገገውን ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን የጣሰ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ አንድ እና በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም አመልካች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 የተደነገገውን ፍትሕ የማግኘት መብታቸው መጣሱን በመግለጽ ያቀረቡት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ተቀባይነት አግኝቶ ትርጉም ያስፈልገዋል መባሉ

በአግባቡ ስለሆነ የአጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሀሳብ በመቀበል ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

6. የኪራይ ውልን አስመልክቶ የተሰጠ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ

---

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 4ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ.65/11

---

## 6.1 አመልካች፡- አቶ አብርሃም ኃ/ጊዮርጊስ፣ ተጠሪዎችዎች፡- እነ አቶ መሃሪ መኮንን (4 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የንብረት ኪራይ ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካች ለአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 146 የሆነውን የንግድ ቤት ከወረዳው አስተዳደር ላይ ተከራይቼና የንግድ ሥራ ፈቃድ አውጥቼ የምሠራበትን የንግድ መደብር የወረዳው አስተዳደር ለሌላ ሰው አከራይተሀል በሚል መነጠቁ አላግባብ ነው፡፡

መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ቤቱን ከፋፍዬ የተለያየ በር አድርጌ ባዶውን ክፍል ያላከራየሁ በመሆኑ በመመሪያው ስለማይሸፈን ቤቱ እንዲመለስልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበረን ግንኙነት በሽርክና ተስማምተን ከሚገኘው ጥቅም በወር ብር 4500 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ የሚሰጠኝ እንጂ ግንኙነታችን የአከራይና ተከራይ አይደለም፡፡

በተጨማሪም ዕድሜዬ 65 /ስልሳ አምስት/ ዓመት በላይ የሆንኩ አዛውንት ስለሆንኩና በአዋጁ ስለማልሸፈን ቤቱ ሊወሰድብኝ አይገባም በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ ባቀረቡት መልስ አመልካች ቤቱን በመከፋፈል ለራሳቸው ሌላ መውጪያና መግቢያ በር በማበጀት ለእኔ ሌላ በር አዘጋጅተው ያከራዩኝ ስለሆነ በመመሪያው ተጠቃሚ መሆናቸውን፣ ቤቱን በወር ብር 4500 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ያከራዩኝ በመሆኑና የሽርክና ውሉ ከዚህ በፊት በፍርድ ቤት ክርክር ተደርጎበት በፌዴራል መጀ/ደ/ፍርድ ቤት ሕጉን ተከትሎ ያልተፈፀመ ስለሆነ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ቤቱ ለእኔ መከራየቱ በመመሪያው መሠረት አግባብ ስለሆነ ከክሱ በነጻ ልሰናበት በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ግንኙነት የአከራይና ተከራይ ሳይሆን የሽርክና ግንኙነት መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ አመልካች አዛውንት በመሆናቸው መመሪያው አዛውንቶችን ስለማያጠቃልል ተጠሪዎች ያደረጉትን የኪራይ ውል አቋርጠው ቤቱን ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች ከአሁኑ ክርክር በፊት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ በሽርክና ውሉ መሠረት ያልከፈለኝን ብር እንዲከፍለኝ የሚል ሲሆን ክሱን የተመለከተው ፍርድ ቤት የሽርክና ውሉ ሕገ ወጥ ነው የሚል ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ ይህም ውሳኔ ፀንቶ ያለ በመሆኑ የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ግንኙነት የሽርክና አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በ23/02/2009 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 98003 የሰጠው

ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብቱ የሆኑትን አንቀጽ 40/1፣ 37፣ 41/5/ የሚጥስ ስለሆነ ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም እንዲሰጥ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱን ያላከራዩና እድሜያቸውም አዛውንት መሆኑ ተጠቅሶ ውሳኔ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ይህም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ጸንቷል፡፡

አመልካች አከራይተው በመገኘታቸው ምክንያት ፍ/ቤቱ መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6ን መሠረት በማድረግ በጊዜው ለተከራየው 1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ ተገደዋል፡፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/1/ እንደተገለፀው ራሱ ሳይሠራበት ለ3ኛ ወገን ቤቱን በማከራየት በሚገኘው ገቢ ብቻ የሚተዳደር ተከራይ አቅመ ደካማ አዛውንት ወይም ወላጅ ያጡ ህጻናት፣ የኤች አይ ቪ ህመምተኞችና የአልጋ ቁራኛ የሆኑ በሽተኞች ከሆኑና ሌሎች የገቢ ምንጮች እንደሌላቸው በሚመለከተው በመመሥረት ተቋም ማስረጃ ካቀረቡ እንደ ቤቱ ሁኔታ ታይቶ በልዩ ሁኔታ ተከራይነታቸው ሊረጋገጥላቸው ይችላል በማለት ተደንግጓል፡፡
አመልካች ባያያዙት የልደት የምስክር ወረቀት የተወለዱበት ቀን ነሐሴ 28 ቀን 1937 ዓ.ም መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ በመነሳት የአመልካች ዕድሜ መመሪያው እስከወጣበት ህዳር 7/2004 ድረስ እንኳ 67 /ስልሳ ሰባት/ ዓመት የሞላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ዕድሜ ደግሞ አዛውንት ወይም ደካማ የሚባል ነው፡፡

ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 41/5/ መንግሥት የአካል እና የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መንግሥት ባለው የኢኮኖሚ አቅም ለአረጋውያን አስፈላጊውን ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው መመሪያ ይህን የሕገ መንግሥት ድንጋጌ የሚያስከብርና ወደ አፈጻጸም የሚያመጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ውሳኔው አመልካች አዛውንት መሆናቸውን ግምት ውስጥ ሳያስገባ የተሰጠና አመልካች በዚህ እድሜያቸው ለአረጋውያን በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውን ክብርና እንክብካቤ

እንዳያገኙ ያደረገ ነው፡፡ ውሳኔው ለአመልካች በመመሪያውና በሕገ መንግሥቱ የተከበረላቸውን ከመንግሥት እንክብካቤ የማግኘት መብት ያገናዘበ አይደለም፡፡ ክርክር የተነሳበት ቤት የመንግሥት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ውሳኔው አመልካችን በአረጋዊነታቸው የተከበረላቸውን ከመንግሥት እንክብካቤ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጻረር ነው፡፡ በዚህም የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 41/5/ ድንጋጌ በመተላለፍ የተወሰነ ነው፡፡

ስለዚህ የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 5 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል አጣሪ ጉባዔው ለኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት ቋሚ ኮሚቴው የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎችን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባዔውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ግራ ቀኙ በስር በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባደረጉት ክርክር የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት የአከራይ ተከራይ ሳይሆን የሽርክና ግንኙነት መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን፣ አመልካች 67 (ስልሳ ሰባት) ዓመት የሞላቸው መሆኑን፣ ይህ ዕድሜ ደግሞ አዛውንት የሚያስብል መሆኑን በመግለጽ እንዲሁም መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6(1) የሚደግፋቸው መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪዎች ያደረጉትን የኪራይ ውል አቋርጠው ቤቱን ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በጥልቀት በመመርመርና የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጠናከር ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባዔውና ቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 41(5) ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

7. የንግድ ጉዳይን አስመልክቶ የተሰጠ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ

---

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 4ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ

ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ.66/11

---

### 7.1 አመልካች፡- አቶ ንጉሤ ሀድጎ፣ ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል አቃቤ ሕግ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

አመልካች ነሀሴ 5 ቀን 2008 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔው ያቀረቡት አቤቱታ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰሜን ወሎ ዞን የጅምላ ንግድ ፍቃድ እያለኝ ቅርንጫፍ መ/ቤት ስትከፍት ለዞኑ ንግድ መምሪያ ሳታሳውቅ፣ የንግድ ፈቃድ ኮፒ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ኮፒ ሳትሰጥና ፈቃድ ሳትጠይቅ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በቁለም ወለጋ ዞን ዳሌ ወበራ ወረዳ አካባቢ በርበሬ ገዝተሀል በማለት በወንጀል ተከስሼ የንግድ ፈቃዴን አሳይቼ እያለ ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ በማለት በሰጡት ውሳኔ 3 ዓመት እሥራትና የብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲሁም የጫንኩት 169 ኬሻ ሚጥሚጣ እንዲወረስ የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን በሕገ መንግሥቱ

የተሰጠኝን ተዘዋውሮ የመሥራት መብት የሚጥስ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከሳሽ አቃቤ ሕግ ሆኖ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32 (1) /ሀ/ እና የንግድ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6 (4) እና 60 (3) በመተላለፍ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በቄለም ወለጋ ዞን ዳሌ ወበራ ወረዳ ቂጮ መንደር 11 እና 12 ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ለወረዳው ንግድ ጽ/ቤት ማሳወቅ እያለበት ሳያሳውቅ 169 ኩንታል ሚጥሚጣ ግምቱ ብር 82,000 (ሰማንያ ሁለት ሺህ ብር) ገዝቶ ጭኖ ሊወጣ ሲል የተያዘ ሲሆን ለሚመለከተው አካል ሳያሳውቅ ቅርንጫፍ በመክፈት የንግድ ሥራ ላይ የመሰማራት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካችም ለዚሁ የወንጀል ክስ ባቀረበው የመከላከያ መልስ አመልካች ቅርንጫፍ አልከፈትኩም፤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ወሎ ዞን የሰጠኝ የንግድ ፍቃድ ግዢውን ለመፈጸም በቂ ነው ሌላ ፍቃድ ማውጣት አይጠበቅብኝም፤ ሽያጭ አልፈጸምኩም በማለት የተከሳሽነት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ አመልካችን ጨምሮ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የበርበሬ ግዢውን መፈጸሙን ለፍርድ ቤት አሳውቀዋል፡፡ በተጨማሪም ከወረዳው ንግድ ጽ/ቤት በተጻፈ የጽሑፍ ማስረጃ አመልካች ቅርንጫፍ የመክፈት ንግድ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ገልጸዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች እና የጽሑፍ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ በአማራ ክልል የተሰጠው የንግድ ፍቃድ አመልካችን ከዚህ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት ሊያድነው ይችላል ወይስ አይችልም? ይህ የወረዳ ንግድ ጽ/ቤት ለአመልካች ፈቃድ ስለከለከለው ያለፈቃድ መግዛት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉትን ሁለት ጭብጦች ይዞ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች አሁን ንግድ እያካሄደ ያለው በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ውስጥ በመሆኑ ቅርንጫፍ ለመክፈቱ ለጽሕፈት ቤቱ ማሳወቅ ነበረበት፣ ያለፈቃድ መግዛት አይችልም በማለት በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6(4) መሠረት አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በ3 ዓመት ጽኑ እሥራትና በብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ተጠሪ ለኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠይቆ አመልካች የጫነው 169 ኬሻ ሚጥሚጣ ከወንጀል ፍሬ የተገኘ ነው በማለት እንዲወረስ ተወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ በመጨረሻ ጉዳዩን የተመለከቱት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች የማስፈቀጃ ማመልከቻውን ከመረመሩ በኋላ አያስቀርብም ሲሉ መዝገቡን ዘግተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በእጄ ላይ የንግድ ፍቃድ እያለ ከሌላ ክልል የገዛሁት በርበሬ ፍቃድ ሳትጠይቅ መግዛትህ ወንጀል ነው ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ እኔ አመልካች ሀገር አቀፍ የንግድ ፍቃድ ኖሮኝ እያለ በሕገ መንግሥቱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ተዘዋውሬ የመሥራት መብቴን የሚጥስ ነው የሚል ነው፡፡

አጣሪ ጉባዔው የአመልካችን አቤቱታ አያይዘው ካቀረቧቸው የፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣ ከአዋጅ ቁጥር 686/2002 አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ከሕገ መንግሥቱ አንጻር መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም ጉዳዩን በድጋሚ የተመለከተው የዳሌ ወበራ ወረዳ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት አመልካች በተጠሪ የተከሰሱት አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6(4) እና 60(3) እንዲሁም የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1) /ሀ/ በመተላለፋቸው ነው የሚል ሲሆን አመልካችም የበርበሬ ግዢ ፈጸምኩ እንጂ አልሸጥኩም፤ ለመግዛት ፍቃድ አያስፈልገኝም፣ የጅምላ ነጋዴ ስለመሆኔ የንግድ ፈቃድ መያዜን በመግለጽ በርበሬ ገዝቼ ብሸጥ ኖሮ ቅርንጫፍ መክፈት ያስፈልገኝ ነበር አሁን ግን ግዢ ብቻ ስለሆነ ቅርንጫፍ መክፈት አያስፈልገኝም የሚል ነው፡፡ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ውስጥ የተካተተው ለጉዳዩ የዳሌ ወበራ ወረዳ ንግድ እና ገበያ ልማት ጽ/ቤት በቁጥር 334 በቀን 26/07/2006ዓ.ም የሰጠው የጽሑፍ ማስረጃ አመልካች የንግድ ፍቃድ የሌለው መሆኑን ይገልጻል፡፡

አመልካች ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰሜን ወሎ ዞን ተሰጠኝ በማለት ያቀረቡት የንግድ ፈቃድ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የተሰጠ የበርበሬ ጅምላ ንግድ ፍቃድ ሲሆን በዚሁ አዋጅ የጅምላ ሻጭ ማለት የንግድ እቃዎችን ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ሲሆን አመልካች በዚሁ መሠረት ተመዝግቦ የበርበሬ ጅምላ ንግድ ለመነገድ የንግድ ፈቃዱን የወሰደ መሆኑን እንረዳለን፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እንደተገለጸው አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ዜጎች በሀገራቸው ውስጥ በማናቸውም ሁኔታ ተዘዋውሮ የመሥራት፣ የመንቀሳቀስ እና ንብረት የማፍራት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

አመልካች ግዥ በመፈጸም የተከሰሱበት አዋጅ የወጣበት ዋነኛው ዓላማ የንግዱ ዘርፍ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚደግፍበትን ሁኔታ በማጠናከር የንግድ ምዝገባና የንግድ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን በአግባቡ በማደራጀት የንግዱን ዘርፍ ጎጂና ተገቢ ካልሆነ እንቅስቃሴ የመከላከል፣ በንግዱ ዘርፍ መንግሥት ሊኖረው የሚገባውን መረጃ በአግባቡ ለመያዝ የሚያስችል ሁኔታ ለማመቻቸትና ለንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6 መሠረት ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው ዋናው መሥሪያ ቤት ባለበት ስፍራ ነው፡፡ በተለያዩ ክልሎች የተለያዩ የንግድ ሥራ ቢሠራም በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑንና ይህም የሚሆነው በዋናው መ/ቤት ባለበት ስፍራ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ነገር ግን በዚሁ አዋጅ ቁጥር 6(4) በብዙ ስፍራዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት የሚከፍት ማንኛውም ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቅርንጫፍ መ/ቤቱ በሚገኝበት ስፍራ ላለው መዝጋቢ መሥሪያ ቤት አግባብነት ያለውን ማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ በማያያዝ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን አድራሻ እና ልዩ የምዝገባ መለያ ቁጥሩን ሊያሳውቅ እንደሚገባ አስቀምጧል፡፡

አመልካች የተከሰሱበት ቅርንጫፍ መ/ቤት ለመክፈት ሳያሳውቁ የንግድ ሥራ ሠርተዋል በማለት የአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6(4) በመተላለፋቸው የተመሠረተባቸውን ክስ መሠረት በማድረግ በዚሁ አንቀጽ 6(4) እና 60(3) መሠረት ጥፋተኛ የሚል ሲሆን አጣሪ ጉባዔው አመልካች በክሱ ላይ የተጠቀሱትን አንቀጾች በመተላለፍ የተሠራ ወንጀል አለ በማለት ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ነው አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምሯል::

የዳሌ ወበራ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ለተከሰሱበት ቅርንጫፍ ሳይከፍቱ ግዢ መፈጸም ክስ አመልካችን ጥፋተኛ የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቻለው አመልካችን ጨምሮ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የበርበሬ ግዢውን መፈጸሙን ለፍርድ ቤት በሰጡት ምስክርነት ነው፡፡ በተጨማሪም በወረዳው ንግድ ጽ/ቤት የተጻፈው የጽሑፍ

ማስረጃ አመልካች ቅርንጫፍ ከፍቶ የመሥራት ንግድ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ጠቅሰው የጻፉትን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22(1) ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ እና አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡

አመልካች በኦሮሚያ ክልል ዳሌ ወበራ ወረዳ በርበሬ ግዢ መፈጸማቸውን እሳቸውም አምነው የሰጡትን ቃል የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ግዢውን ተዘዋውረው ሲፈጽሙ ማየታቸውን እንጂ ሲሸጡ እንዳላዩ መስክረዋል፡፡ አመልካች ነጋዴ ለመሆናቸው ከአማራ ክልል የተሰጠ የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ አመልካች በተከሰሱበት የአዋጁ ድንጋጌዎች የንግድ ሥራ ለመሥራት ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚፈልግ ነጋዴ ቅርንጫፍ ሊከፍት በሚፈልግበት ቦታ ለሚገኝ የንግድ ጽ/ቤት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የንግድ ፍቃዱንና ቲን ኮፒ በማቅረብ ማሳወቅ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

ሆኖም የአመልካች ድርጊት ግዢ ሲሆን በተከሰሱበት አዋጅ ድንጋጌ ላይ የሚወድቅ የወንጀል ድርጊት አይደለም፡፡ የአመልካችን ድርጊት ስንመረምር ከኦሮሚያ ክልል ግዢውን መፈጸሙ የወንጀል ድርጊት ለመሆኑ በአዋጁ /በሕግ/ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የፍ/ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22 እና 32 የተደነገጉትን ማንም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም የሚለውን ድንጋጌ እንደዚሁም የአመልካችን ተዘዋውሮ የመሥራት ነጻነት ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጋፋ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት ቋሚ ኮሚቴው የአጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት በማጣመር የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባዔውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት የዳሌ ወበራ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ለተከሰሱበት

ቅርንጫፍ ሳይከፍቱ ግዢ መፈጸም ክስ አመልካችን ጥፋተኛ የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቻለው አመልካችን ጨምሮ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የበርበሬ ግዢውን መፈጸሙን ለፍርድ ቤት በሰጡት ምስክርነት ነው፡፡ በተጨማሪም በወረዳው ንግድ ጽ/ቤት የተጻፈው የጽሑፍ ማስረጃ አመልካች ቅርንጫፍ ከፍቶ የመሥራት ንግድ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ጠቅሰው የጻፉትን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22(1) ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ እና አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡

አመልካች በኦሮሚያ ክልል ዳሌ ወበራ ወረዳ በርበሬ ግዢ መፈጸማቸውን እሳቸውም አምነው የሰጡትን ቃል የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ግዢውን ተዘዋውረው ሲፈጽሙ ማየታቸውን እንጂ ሲሸጡ እንዳላዩ መስክረዋል፡፡ አመልካች ነጋዴ ለመሆናቸው ከአማራ ክልል የተሰጠ የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ አመልካች በተከሰሱበት የአዋጁ ድንጋጌዎች የንግድ ሥራ ለመሥራት ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚፈልግ ነጋዴ ቅርንጫፍ ሊከፍት በሚፈልግበት ቦታ ለሚገኝ የንግድ ጽ/ቤት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የንግድ ፍቃዱንና ቲን ኮፒ በማቅረብ ማሳወቅ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

ሆኖም የአመልካች ድርጊት ግዢ ሲሆን በተከሰሱበት አዋጅ ድንጋጌ ላይ የሚወድቅ የወንጀል ድርጊት አይደለም፡፡ የአመልካች ድርጊት ሲመረመር ከኦሮሚያ ክልል ግዢውን መፈጸሙ የወንጀል ድርጊት ለመሆኑ በአዋጁ/ በሕግ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የፍ/ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22 እና 32 የተደነገጉትን ማንም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም የሚለውን ድንጋጌ እንደዚሁም የአመልካችን ተዘዋውሮ የመሥራት ነጻነት ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጋፋ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባዔውና ቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 22 እና 32 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

8. የጡረታ መብትን አስመልክቶ የተሰጠ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ

---

የኢ.ፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ.81/12

---

8.1 አመልካች፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ ተጠሪዎች፡- እነ አቶ እርገጤ መድበው ጆፌ (22 ሰዎች)

የኢ.ፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የጡረታ መብት ተጠቃሚነትን የተመለከተ ጥያቄ ሲሆን የተጀመረውም 1ኛ ተጠሪ በሆኑት አቶ እርገጤ መድበው የሰው ለሰው መረዳጃ ዕድር ም/ሊቀመንበር የዕድሩን አባላት በመወከል ለአመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መነሻነት ነው፡፡

ተጠሪዎች ለአመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ቀደም ሲል በመንግሥት ሠራተኛነት ተቀጥረው ከ10 ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በፅኑ እሥራት ምክንያት አገልግሎታቸውን ያቋረጡ በመሆኑ አሁን የጡረታ መብታቸው እንዲከበር ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የካቲት 9 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቀደም ሲል በጽሑፍ እና በቃል ምላሽ የሰጠ መሆኑን በማስታወስ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 27 እና በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63 ተራ ቁ 3 መሠረት አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የሚወሰንላቸው የአንድ ጊዜ የዳረጎት አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ወይም የዘለቄታ ጡረታ አበል የለም ሲል ወስኗል፡፡

በውሳኔው ላይ ይግባኝ የቀረበለት የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ከላይ በተጠቀሱት የጡረታ ባለመብት በሆኑት 1ኛ ተጠሪ አማካኝነት በተከፈተ ማኅደር የቀድሞ የመንግሥት ሠራተኛ የነበሩ በመንግሥት ለውጥ አብዛኛዎቻችን ከአስር ዓመት በላይና እስከሞት ተፈርዶብን የነበረ ለእያንዳንዳችን የዕድሜ ልክ ጡረታ ተፈቅዶልን የምንኖር ሲሆን ከማረሚያ ቤት ከወጡ አባሎቻችን የተወሰኑት የዘለቄታ የጡረታ መብት አጥተው የሞት ጥላ ያጠላባቸውና ለልመና ጎዳና የወጡ አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች አሉን፤ በአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5(2) መሠረት ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ ዕድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል በሚል ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን ኤጀንሲው አዋጁ ከ20 ዓመት በላይ ያገለገሉትን ብቻ የሚመለከት ነው በሚል መወሰኑ ተገቢ እንዳልሆነና ብዛታቸው ከ150-200 የሚሆኑ ከ18-19 ዓመት አገልግሎት ያላቸው ጭምር ያሉበት ቢያንስ 10 ዓመት አገልግሎት ያላቸው አባላት የዘለቄታ ጡረታ መብት እንዲከበርልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ከ20 ዓመት በታች አገልግሎት ያላቸው ሰዎች መብታቸው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ቢሆንም በአዋጅ ቁ 907/2007 መሠረት የሚወሰንላቸው አበል የለም በማለት የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

በይግባኝ ሰሚው ጉባዔ በተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ አመልካችም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ ለውሳኔያቸው መሠረት ያደረጉት መሠረታዊ ነጥብ የተጠሪዎች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል ይገባቸዋል አይገባቸውም? የሚለውን ከአዋጅ ቁ 907/2007 አንቀጽ 5(2) አንፃር ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በምርመራውም አመልካች ለችሎቱ ባቀረበው መልስ በአዋጅ ቁጥር 209/55፣ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 5/67 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ የተደነገገውን ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት እያነሳ የተከራከረ መሆኑን በመጥቀስ በእነዚህ አዋጆች ላይ የተደነገገው እና የአሁኑ ተጠሪዎች ስለመብታቸው የሚከራከሩበት የአገልግሎት ዘመን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 መተካቱን ገልጸዋል፡፡

በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2 ላይ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 /1/ በተደነገገው መሠረት የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልክ ይከፈለዋል ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር ዓመት ማገልገል ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 18/1/ መሠረት የጡረታ እድሜ መድረስ ነው፡፡ የአመልካቾች እድሜ ከ60 ዓመት በላይ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ሲከራከር የነበረው አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ ጡረታ አበል አይገባቸውም በማለት ነው፡፡

ይህ ክርክር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19/2/ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ ደግሞ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5/2/ የተተካ በመሆኑ የአመልካች የ20 ዓመት አገልግሎት ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63/3/ ድንጋጌም ቢሆን አዋጁን ሊጻረር አይችልም፡፡ ምክንያቱም መመሪያው አዋጁን ማስፈጸሚያ እንጂ በአዋጁ የተደነገገውን ድንጋጌ ሊቃረን የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

ሌላው የአመልካች ክርክር የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5/2/ አዋጁ በሚወጣበት ጊዜ በሥራ ላይ ያሉትንና ከአዋጁ በኋላ የጡረታ እድሜያቸው ሲደርስ ጡረታ የሚወጡትን የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ክርክር የማሻሻያ አዋጁን አንቀጽ 5/2/ 'ን' መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ የአሁኑ አመልካቾች የዘለቄታ የጡረታ አበል እየጠየቁ ያሉት በገዛ ፈቃዳቸው ሥራ ለቀው ሳይሆን ታስረው በመቆየታቸውና እድሜያቸው ለጡረታ የደረሰ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 11/9 አንጻር ሲታይ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል በማለት ተጠሪ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከፀናበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የጡረታ አበል ክፍያ ለአመልካቾች እንዲከፍላቸው ሲል ወስኗል፡፡

ከላይ ፀንቶ ባለው ውሳኔ ላይ የአመልካች ቅሬታ ፍሬ ሃሳብ ሁሉም ተጠሪዎች ከስር ጀምሮ አልተከራከሩም፣ የተጠሪዎች አገልግሎት ከ10-19 ዓመት በመሆኑ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ.714/2003 (በአዋጅ ቁ 907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 59(9) መሠረት የዘለቄታ የጡረታ አበል ለማግኘት አይችሉም፣ በዚህ ማሻሻያ ተጠቃሚ የሆኑት የዘለቄታ የጡረታ አበል በመጠቀም ላይ እያሉ በጽኑ እሥራት ምክንያት የጡረታ አበላቸው ተቋርጦባቸው ለነበሩና ከመታሰራቸው በፊት 20 ዓመትና በላይ አገልግሎት የነበራቸውን የሚመለከት ሆኖ ሳለ ይህን ግልጽ አዋጅ በመተው ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሠጠው ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 79(3) ይቃረናል የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከሕገ መንግሥቱና ከፍ/ቤቱ ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡ በጽኑ እሥራት ምክንያት የጡረታ አበል የተቋረጠባቸው ወይም ደግሞ የጡረታ አበል ሳይወሰን አገልግሎታቸው 20 ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት የሰጡ፣ በፅኑ እሥራት ምክንያት አገልግሎታቸው ውድቅ የተደረገባቸው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የጡረታ አበል የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ደንግጓል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከ20 ዓመት ያላነሰ 25 ዓመት ያልሞላ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ወይም ደግሞ በተለያየ ምክንያት አገልግሎቱን ካቋረጠ፣ እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አበል ተጠቃሚ ይሆናል የሚል ነበር፡፡ ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 907/2007 የተሻሻለ ሲሆን አዋጁ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በመንግሥት

ሥራ ላይ ያሉና አዋጁ ከፀና በኋላ ከመንግሥት ሥራ ለሚለቁ ሠራተኞች አገልግሎቱ 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነና እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አበል ይወሰንለታል በሚል ተሻሽሏል፡፡ ነገር ግን ይህ ማሻሻያ ወደ ኋላ እንዳይሄድ ተደርጎ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በመንግሥት ሥራ ላይ የነበረ ሠራተኛ ሥራውን የሚለቅ ከሆነ የጡረታ እድሜው ሲደርስ የዘለቄታ የጡረታ አበል ያገኛል በሚል ተደንግጓል፡፡ አዋጁ ላይ እንደተጠቀሰው ቀደም ሲል በነበሩ አዋጆችና መመሪያዎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል ይላል፡፡ የተጠሪዎች ጉዳይም በዚሁ መሠረት መታየት አለበት፡፡

ጉባዔው አመልካች ጉዳዩን ቀርቦ እንዲያስረዳ ባዘዘው መሠረት የኤጀንሲው ተወካዮች ቀርበው ስለሁኔታው አስረድተዋል፡፡ በዚህም መሠረት "ጉዳዩ በዚህ መልኩ ተፈጻሚ ከሆነ በትክክል የፖሊሲ መናጋትን እንደሚያመጣ፣ በተሻሻለው ድንጋጌ መሠረት ድሮ በጽኑ እሥራት ታሰሩ ተብሎ መከልከል ጥሩ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ሁሉንም እንቀበል ብንል የጡረታ መዋጮው ውስጥ ልንሸከመው የማንችለው ችግር ይፈጠራል፡፡ በአዋጁ መሠረት ከ2007 ሐምሌ በኋላ ያሉትን መንግሥት ዘላቂ የጡረታ አበል መክፈል እንደሚችል ታስቦ የወጣ አዋጅ ነው፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ ሕግ ብቻ ሳይሆን ፖሊሲም ነው፣ ውሳኔው የተወሰነው ሕግን መሠረት አድርጎ አይደለም፤ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ ሕግንና ሕገ መንግሥትን ጥሷል" በማለት ለጉባዔው አስረድተዋል፡፡

ማሻሻያ አዋጁ ሥራ ላይ የሚውለው አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ የ10 ዓመት አገልግሎት የተሰጠው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሚሆነው ሠራተኛ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በራሱ ምክንያት ወይም ደግሞ በሌላ ምክንያት ሥራን ለሚለቅ ሠራተኛ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ሥራ መልቀቅን አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ እንደ አንድ ግዴታ ስለሚያስቀምጥ ከዚያ በፊት የለቀቀን ሠራተኛ አያካትትም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ሥራ የለቀቁት አዋጁ ከመታወጁ በፊት ነው፡፡ ከአዋጁ መታወጅ በፊት የለቀቀ ሠራተኛ ደግሞ ከአዋጁ የ10 ዓመት አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

---

የጡረታ አበል በፖሊሲና በሕግ መሠረት መመራት አለበት፡፡ በዚህ ውሳኔ መሠረት ሁሉም 10 ዓመት ያገለገለ ሠራተኛ አበል የሚሰጠው ከሆነ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ የሰበር ሰሚ ውሳኔ መሠረት ጉዳዩ ተፈጻሚ ቢሆን የጡረታ ፈንዱ

ከሚሸከመው በላይ ስለሚሆን ኤጀንሲውና መንግሥትን ብሎም መላውን የጡረታ አበል ተጠቃሚዎች ችግር ውስጥ ያስገባቸዋል፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን ደግሞ ለአገሪቱ ችግር ይፈጥራል፡፡ በዚህ መሠረት የፖሊሲ መቃወስ ያስከትላል፡፡ ስለዚህ በውሳኔው ሕግ በትክክል ባለመተርጎሙ የፖሊሲ ችግር ስለሚያመጣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 79(3) ዳኞች ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም በማለት ደንግጓል፡፡ ግልፅ የሆነ ሕግ እያለ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ሕግ ተላልፏል፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቶች መሥራት ያለባቸው በሕግ መሠረት ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 907/07 በግልጽ ያስቀመጠው ሠራተኛው አዋጁ ከጸደቀ በኋላ ሲለቅ ብቻ የዘለቄታ የጡረታ መብት ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የአዋጁን አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተረጎመበት መንገድ ትክክል አይደለም፡፡ ማንኛውም ሠራተኛ 10 ዓመት ካገለገለ የጡረታ መብት ይከበርለታል ብሎ ውሳኔ መስጠት ከአዋጁ ድንጋጌና እሳቤ ውጭ ነው፡፡ በዚህም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በትክክል ሕጉን ያላከበረና ዳኞች ከሕግ በስተቀር በሌላ አይመሩም የሚለውን የሕገ መንግሥት ድንጋጌ ያከበረ አይደለም፡፡ በዚህም ውሳኔ ዳኞች በሕግ መሠረት እንዲመሩ የሚያዘው የሕገ መንግሥት ድንጋጌ ተጥሷል፡፡

ስለዚህ የፍ/ቤቱ ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 3፣ የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

---

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 (3) ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 (1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡